የነብስ አድን ክትባት ዘመቻ
ገጽ 9

ውሳኔ ብቻውን ውሳኔ ነው?
ገጽ 14

የክረምት ጨንቃዎች
ገጽ 16

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 299 ሰኔ 29 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን በድንበር አካባቢ የሚከሰቱ ግጭቶችን በጋራ ለመፍታት ስምምነት አደረጉ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን የድንበር አካባቢዎች የሚከሰቱ የጎሳ ግጭቶች፣ ከብት ዘረፋዎችና ሌሎች ችግሮችን በጋራ ለመፍታት የሚያስችል አቅጣጫ መቀመጡን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ለሁለት ቀናት ሲካሄድ የነበረው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ-ደቡብ ሱዳን የጋራ ድንበር አስተዳዳሪዎች የምክክር መድረክ ትናንት የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም ተጠናቋል።

የኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን የድንበር አካባቢዎች የጎሳ ግጭቶች ከብት ዘረፋዎችና በማህበረሰብ ግጭት ዙሪያ የነበሩ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት የሚያስችል አቅጣጫ ተቀምጧል።

በሁለቱ ሀገራት መካከል የድንበር ልማት ንግድና ኢንቨስትመንት የመሠረተ ልማት ትስስርን የጋራ ደህንነትን ለማጠናከር አይነተኛ ሚና ይጫወታል ያሉት አምባሳደሩ ስብሰባው በሁለቱ ሀገራት መካከል የሁለትዮሽ ትብብርን ለማጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል።

"በመዲናዋ የተካሄደ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ ሀዱሽ አብርሃ
መንዲይ ሰማያ ኩምባ እና አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ




## የግብርና ቆጠራ በመጪው ዓመት ይካሄዳል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በ2017 ዓ.ም በ16 ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ወጪ የግብርና ቆጠራ ለማከናወን ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን

የግብርና ቆጠራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ አዩብ ተፈሪ
አቶ ጥላሁን ከበደ

## የክልል መዋቅራዊ ጥያቄዎች ሕዝብን ባሳተፈ መልኩ በለውጡ መንግሥት ምላሽ አግኝተዋል

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- የክልል መዋቅራዊ ጥያቄዎች ሕዝብን ባሳተፈ መልኩ በለውጡ መንግሥት ምላሽ አግኝተዋል ሲሉ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ ገለጹ፡፡

የክልል መዋቅራዊ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# "በመዲናዋ የተካሄደው የምክክሩ አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት በተለያዩ ከተሞች ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል"

- የጋሞ የሀገር ሽማግሌ አባቶች

ጌትነት ተስፋማርያም

አርባ ምንጭ፡- በመዲናዋ በተሳካ ሁኔታ የተካሄደው የሀገራዊ ምክክር የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት በተለያዩ ከተሞችም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ሲሉ የጋሞ የሀገር ሽማግሌ አባቶች ጥሪ አቀረቡ።

የጋሞ የሀገር ሽማግሌ የሆኑት ሰዲቃ ስሜ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ለችግሮቻችንን መፍትሄ እንደሆነ የታመነበት የሀገራዊ ምክክር መድረክ በተለያዩ አካባቢዎች እንዲስፋፋ ጽኑ ፍላጎት አለ።

የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፉን በሀገር አቀፍ ደረጃ በይፋ ያስጀመረው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ለአንድ ሳምንት ያከናወነው የአዲስ አበባ መድረክን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቁን አስታውሰዋል።

የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱ በተጀመረበት ፍጥነት ሳይቋረጥ በተመሳሳይ በሌሎች ከተሞችና የክልል አካባቢዎችም ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የአዲስ አበባው መድረክ በያገባኛልና የሃላፊነት መንፈስ መካሄዱ በቀጣይ ለሚከናወኑ ሥራዎች መሠረት

"በመዲናዋ የተካሄደው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


የጋሞ የሀገር ሽማግሌዎች ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት እንደሚሠሩ አሳውቀዋል



# "የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር ለተመድ ዘላቂ የልማት ግብ ከፍተኛ ሚና አለው"

- አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘላቂ የልማት ግብን ዕውን ለማድረግ ከፍተኛ ሚና አለው ሲሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ ገለጹ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከተጠሪ ተቋማት እና ከሀገራት ዲፕሎማቶች ጋር በመሆን ትናንት በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በመገኘት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር አከናውኗል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ በወቅቱ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘላቂ የልማት ግብ ዕውን ለማድረግ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

መርሃግብሩ ኢትዮጵያ የዓለም ሥነምህዳር ለመጠበቅ ያላትን ቁርጠኝነት በተግባር ያሳየችበት ነው ያሉ ሲሆን፤ ችግሩን ለመመከትም በጀት መድባ እየሠራች ትገኛለች ብለዋል፡፡

የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎትና አረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር ለሀገሪቱ የወደፊት መጻኢ ጉዞ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው ያሉት አምባሳደር ታዬ፤ የአረንጓዴ ዐሻራ የሀገሪቱን ሥነምህዳር ከመጠበቅ አልፎ ለሌሎች ጠቀሜታ እያስገኘ እንደሚገኝ አብራርተዋል።



የአየር ንብረት ለውጥ ወቅታዊ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ከሆነ ውሎ ቢያድርም ባለድርሻ አካላት ችግሩን ለመቅረፍ ያለው ተግባራዊ ቁርጠኝነት እምብዛም መሆኑንም ነው አምባሳደር ታዬ ያስረዱት።

አምባሳደር ታዬ አክለውም፤ ሀገሪቱ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተቀናጀ የክረምት ሠብዓዊና ማህበራዊ በጎ ፈቃድ አገልግሎት እያጠናከረች ትገኛለች ያሉ ሲሆን፤ በተጨማሪም በአረንጓዴ ልማት እየሠራች ያለችው ሥራ ለሠብዓዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ያላትን ለዘመናት ያልተዛነፈ ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ታዬ ገለጻ፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከዚህ በፊት አጣዬ፣ ሞጆ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረር እና አዲስ አበባ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች የክረምት በጎ ፈቃድና የችግኝ ተከላ አከናውኗል። በዚህ ዓመትም በአዲስ አበባና በአርባ ምንጭ ያከናውናል።

አምባሳደር ታዬ፤ በየዓመቱ የሚተከለው ችግኝ የተራቆቱ ቦታዎች ደን እንዲለብሱ በማድረግና የአፈር መሸርሸርን በመከላከል ተፋሰሶች እንዲጠበቁ ከማድረግ አኳያ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ጠቅሰዋል። ይህም የውሃ አካላት እንዲጎለብቱ እያደረገ ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ የዛንቢያ አምባሳደር ሮዝ ሳካላ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አየር ንብረት አወንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከተች እንደምትገኝ ጠቁመው፤ ታንዛኒያም አረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር እያከናወነች እንደሆነ ገልጸዋል።

የአፍሪካ አህጉር በየጊዜው በድርቅ የምትጠቃ በመሆኑ አረንጓዴ ልማት በእጅጉ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

በአረንጓዴ ዐሻራ ኢኒሼቲቭ ኢትዮጵያ በአህጉሪቱ የመሪነት ሚና እየተወጣች እንደምትገኝም ነው አምባሳደር ሮዝ ያመላከቱት።



ፎቶ አሸናፊ ጉደታ

አምባሳደር ብርቱካን አያና

# ዳያስፖራው
## ለሀገራዊ ልማቱ እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ አጠናክሮ መቀጠል አለበት

**አዲሱ ገረመው**

<u>ሐረር</u>፡- ኢትዮጵያ ባላት ከፍተኛ የዳያስፖራ ቁጥር ልክ ለሀገራዊ ልማቱ የሚደረገው አስተዋጽኦ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተመላከተ።

26ኛውን የሐረር ቀን ምክንያት በማድረግ "ለሀገራችን ሰላምና ብልጽግና የዳያስፖራው ሚና" በሚል መሪ ሃሳብ በሐረር ከተማ ሲምፖዚየም ተካሂዷል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ መርሃግብሩን ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር፣ የክልሉ ተወላጆች ለክልሉ ብሎም ለሀገራዊ ልማት እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ የሚበረታታ እንደሆነ ገልጸዋል። ካለው ከፍተኛ የዲያስፖራ ቁጥርና አቅም አንጻር የተገኙ ውጤቶች እንዲያድጉና እንዲስፋፉ መሥራት እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

ዳያስፖራችን ባዳበረው ጠንካራ የመደራጀት ባህል ምክንያት እንደ ሀገር በርካታ ጥቅሞችን አግኝተናል ብለዋል ሚኒስትር ዴኤታዋ፡፡

በሀገሪቱ ላይ ተፈጥረው የነበሩ ያልተገቡ ጫናዎችን ማለዘብ የተቻለው፤ ለሀገራዊ ፕሮጀክቶችና ወቅታዊ ጥሪዎች ባለፉት ስድስት ዓመታት የአይነትና የገንዘብ ድጋፍ የተሰባሰበው የተደራጀ ዳያስፖራ በመኖሩ እንደሆነ ገልጸዋል።

በዳያስፖራ አደረጃጀት ጠንካራ ከምንላቸው መካከል የሐረሪ ዳያስፖራ በዋነኝነት ይጠቀሳል ያሉት አምባሳደሯ፤ በውጭ የሚኖሩ ሐረሪዎችና የሐረር ተወላጆች ላለፉት 26 ዓመታት ዓለም አቀፍ የሐረር ቀንን ማክበር መቻላቸውም የመዋቅሩን ጥንካሬና ውጤታማነት ያሳያል ሲሉ ገልጸዋል።

በውጭ የሚኖሩ ሐረሪዎች በጠንካራ አደረጃጀታቸው ብቻ ሳይሆን በተሳትፏቸውም ይታወቃሉ ሲሉ አድንቀዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፣ የክልሉ ዳያስፖራዎች በቤት ልማት ዘርፍ የዳያስፖራ መንደርን በመመሥረት አርአያነታቸውን ማሳየት ችለዋል፡፡ በበጎ አድራጎትና የልማት ሥራዎችም ክልሉን በማገዝ ላይ ይገኛሉ፡፡

የሐረሪ ዳያስፖራዎች ባህላዊ ቁሳቁሶችን በሚኖሩባቸው አካባቢዎች በመጠቀምም የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘታቸውም በላይ ለክልሉ ባህል መጠበቅ አበርክቷቸው ትልቅ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

"ክልሉና በውጭ የሚኖሩ የክልሉ ተወላጅ ዳያስፖራዎች እስካሁን ያዳበሩትን ተሞክሮ ተጠቅመውና አዳዲስ የአሠራር ሥርዓቶችን አበጅተው መንቀሳቀስ ከቻሉ ለሀገራዊም ሆነ ክልላዊ ዕድገት አስተዋጿቸው የጎላ ይሆናል" ሲሉ ተናግረዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም የሚያስተዳድራቸው የኢፌዴሪ ሚሲዮኖችንና ተጠሪ ተቋሙን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎትን በማስተባበር ክልሉ ዳያስፖራውን በስፋት ለማሳተፍ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ለመደገፍ ያለውን ቁርጠኝነትም ገልጸዋል።

በመድረኩ ዳያስፖራው ሁነኛ የልማት አማራጭ እየሆነ መምጣቱ የተገለጸ ሲሆን፣ ይህንን ተረድቶ አደረጃጀቱን በማጠናከር ለልማት መጠቀም እንደሚገባ፣ እንዲሁም ዳያስፖራው ለሀገራዊ ልማቱ እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተነስቷል።




# ቴሌ ቲቪ የፈጠራ ባለቤቶችን ተጠቃሚ ያደርጋል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ቴሌ ቲቪ የተሰኘ በዓይነቱ አዲስ የፊልም ኪራይ መተግብሪያ ይፋ መደረጉ የፈጠራ ባለቤቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ሲሉ በኢትዮ ቴሌኮም የኮምኒኬሽን ዋና ኦፊሰር አቶ መሳይ ውብሸት ተናገሩ።

መተግበሪያውን ኢትዮ ቴሌኮም ከኤግልላየን ሲስተም ቴክኖሎጂ ጋር በመሆን ይፋ አድርገውታል።

በኢትዮ ቴሌኮም የኮምኒኬሽን ዋና ኦፊሰር አቶ መሳይ በወቅቱ እንደገለጹት፤ የፊልም መተግበሪያው የፈጠራ ባለቤቶችን ተጠቃሚ ያደርጋል።

ከፈጠራ ባለቤቶች ባለፈ ደምበኞች ሲኒማ ቤት ሳይሄዱ እቤታቸው ቁጭ ብለው የፈለጉትን ፊልም በማውረድ መጠቀም የሚችሉበትና የፊልም ኢንዱስትሪውንም የሚያሳድግ ነው ብለዋል።

በዝግጅቱ ላይ በርካታ አንጋፋ አርቲስቶች፣ ፕሮዲውሰሮች እንዲሁም ዳይሬክተሮች የተገኙ ሲሆን፤ በመተግበሪያው አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ላይ ተወያይተዋል።

የፊልም ዳይሬክተር ሄኖክ አየለ እንዳለው፤ የፊልም ሥራ በብዙ ልፋት የሚመጣ ነው። በመሆኑም ምርቱ በአግባቡ የሚሰበሰብበት አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ነው። እንደነዚህ ዓይነት ጠንካራ መተግበሪያዎች መጠቀም ውጤታማ የሚያደርግ ነው ብሏል።

የኤግልላየን ሲስተም ቴክኖሎጂ መሥራች እና ሥራ አስኪያጅ አቶ በሱፈቃድ ጌታቸው በበኩላቸው፤ ከዚህ ቀደም በርካታ መተግበሪያዎች ሥራ ላይ ማዋላቸውን ጠቅሰው፤ ይህም መተግበሪያ ፊልሞችን በቀላሉ ከአፕስቶር እና ከፕሌይ ስቶር በማውረድ መከራየት ይቻላል ብለዋል።

የፊልም መተግበሪያው የፈጠራ ሥራዎች በቀላሉ የመሰረቅ ኪሳራ እንዳይደርስባቸው ሁነኛ መፍትሄ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዓለማችን ታዋቂ የሆኑት ኔትፍሊክስ እና አማዞን የፊልም መተግበሪያዎች የደረሱበት እድገት ለማድረስ የባለድርሻ አካላት ትብብር ያስፈልጋል ብለዋል።

እንዲሁም አርቲስቶች ፊልም ፕሮዲዩስ ከማድረግ ባለፈ ለገበያ ቀርበው እንዲሸጡ የማርኬቲንግ ሥራ መሥራት አለባቸው ብለዋል።

በአሁኑ ሰአት ትልቅ ተቀባይነት ያገኙ ሁለት ፊልሞች "6 ሰዓት ከሌሊቱ" እና "ትዝታ" ተመልካቾች ቀድመው በመከራየት በአንድ ወር ውስጥ አንድ ሚሊዮን እይታ እንዲያገኙ ይሠራል ብለዋል።

አዲሱ መተግበሪያ ፊልሞች በአማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ፣ ሶማልኛ እና ሌሎችም ቋንቋዎች ይገኙበታል ብለዋል።

# በአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ ከ28 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት እንዳይሸረሸር እና አረንጓዴ እንዲለብስ ተደርጓል

**ኤፍሬም አንዳርጋቸው**

አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ በየዓመቱ በምታከናውነው የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ ከ28 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ እንዳይሸረሸር እና አረንጓዴ እንዲለብስ መደረጉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ፕሮፌሰር እያሱ ኤልያስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ እንደገለጹት በኢትዮጵያ በዓመት ከ20 እስከ 25 ሚሊዮን ሕዝብ በነቂስ በመውጣት ከ30 እስከ 40 ቀን የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን በመሥራት ከ2 እስከ 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንዳይሸረሸር እና አረንጓዴ እንዲለብስ ተደርጓል።

ይህ ሀገሪቱ በየዓመቱ የምታከናውነው የተፈጥሮ ሀብት ፣ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ከ28 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት እንዳይሸረሸር የማዳን ሥራ መሥራት እንዲቻል አድርጓል ብለዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ የሚሠራው የአፈር እና የውሃ ጥበቃ ሥራ በመላው ሀገሪቱ በተለይም በምስራቅ እና በምዕራብ ሀረርጌ የአየር ንብረትን ለመከላከል እና ህብረተሰቡ በምግብ እራሱን እንዲችል የሚያደርጉ ተጨባጭ ለውጦች ማስመዝገብ ተችሏል።

ሀገሪቱ በአፈር እና በውሃ ጥበቃ ሥራ ለአካባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረትን ለመከላከል ያለውን ትልቅ ፋይዳ እና ትልቅ ድል መሆኑን በመገንዘብ ሳይንሳዊ በሆኑ ዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ ለማሳተም እና ለዓለም ለማሳወቅ እንቅስቃሴ ተጀምሯል ሲሉ ተናግረዋል።

መንግሥት በመላው ሀገሪቱ የአፈርን ለምነት እና መሸርሸር ለመጠበቅ፣ ምርትና ምርታማነት ለመጨመር አሲዳማ አፈርን የማከም ሥራ በስፋት እየሠራ ነው። በተለይም የአፈርን ለምነት ለመጠበቅ እና አሲዳማነትን ለመከላከል አርሶ አደሩ የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲያዘጋጅ፣ የእቀባ እርሻ እንዲተገበር፣ ሕይወት ያለው እጽዋት በእርሻ ላይ እንዲቀር የማድረግ ሥራ በስፋት እየተተገበረ ነው ሲሉ አስታውቀዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዝናብ ወቅት እንዲቀያየር፣ በተደጋጋሚ ድርቅ እንዲከሰት፣ የውሃ መጠን እንዲቀንስ እና የተፈጥሮ ሚዛን እንዲዛባ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው ሀገሪቱ በግብርናው መስክ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በመቋቋም እና በምግብ እራስን ለመቻል በየዓመቱ የምትሠራው የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራዎች ጉልህ ሚና እየተጫወቱ ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

ከአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ በተጓዳኝ የትናንሽ የመስኖ ልማት ሥራ፣ ትላልቅ የመስኖ አውታሮችን በየዓመቱ የመገንባት፣ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የመስኖ ሥራዎች የማሳለጥ ሥራ እየተሠሩ ሲሆን ይህም ሀገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም ብቻ ሳይሆን በበጋ የመስኖ ልማት ሥራ ውጤት እንድታስመዘግብ ረድቷል።

በዚህም ሀገሪቱ ከዚህ በፊት ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባውን የስንዴ ምርት በሀገር ውስጥ አምርታ መተካት ችላለች። በተጨማሪም የፍራፍሬ ምርት በስፋት ማምረት የተቻለ ሲሆን የቢራ ገብስን ከውጭ ማስገባት በመተው ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ የመተካት ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል።

ሀገሪቱ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ እንዲሁም የመስኖ ልማት ሥራን በማጠናከር የሩዝ ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት አቅዳ እየሠራች እንደሆነም አብራርተዋል።



ፕሮፌሰር እያሱ ኤልያስ



አቶ ጌቱ ገመቹ



አቶ በሪሶ ፈይሳ

# የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች በእርሻ ልማት ሥራ ስኬታማ እየሆኑ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች ከእንስሳት እርባታ ጎን ለጎን በእርሻ ልማት ዘርፍ አበረታች ውጤት እየተመዘገበ መሆኑ ተገለጸ።

የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና ዞኖች በመገኘት የተለያዩ የግብርና ልማት እንቅስቃሴ ጎብኝተዋል።

የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በጉብኝቱ ወቅት እንደገለጹት፤ በደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች ከእንስሳት እርባታ ጎን ለጎን በእርሻ ልማት አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ነው።

በደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች አብዛኛው ማህበረሰቡ የአኗኗር ዘዬ በከብቶች እርባታ ብቻ የሚተዳደር ተደርጎ ይቆጠር እንደነበር ያነሱት አቶ ጌቱ፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የእርሻ ሥራው ተጠናክሮ በመቀጠሉ የተለያዩ ሰብል ልማት፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የተለያዩ የካሽ ክሮፕ ምርቶች በሰፊው እየተመረቱ ይገኛሉ ብለዋል።

በዞኖቹ ያለው የኩታ ገጠምና ጥምር ግብርና የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት በከፍተኛ ሁኔታ እያሳደገው እንደሚገኝም ነው አቶ ጌቱ የገለጹት።

አቶ ጌቱ አክለውም፤ በዞኖቹ ያለው የግብርና ልማት እንቅስቃሴ በአጭር ጊዜ የቤተሰብ ብልጽግናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ እንደሆኑ ጠቁመዋል።

በሄክታር እስከ ስምንት ኩንታል ቡና ይገኝ የነበረው በአሁኑ ሰዓት በሁለቱ ጉጂ ዞኖች እስከ 12 ኩንታል እየተገኘ ነው ያሉት አቶ ጌቱ፤ ይህንንም በማስፋፋት ይበልጥ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ በዞኖቹ የተሠሩ የተለያዩ የግብርና ሥራዎች ህብረተሰቡ ከብቶችን ከማርባት ጎን ለጎን በእርሻው ዘርፍ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል የሚያሳዩ ናቸው። በተለይ በኩታ ገጠም የተዘሩ የተለያዩ ሰብሎች በሌሎች አካባቢዎችም ለማስፋፋት ምሳሌ መሆን ይችላሉ።

አቶ ጌቱ፤ ቡና ወደ ውጭ ልኮ የውጭ ምንዛሪ ለማምጣት ጥራትን ማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ በክልሉ ቡና በበርካታ ቦታዎች ቢመረትም በጉጂ ዞን የሚመረተው ከፍተኛ ጥራት ያለው እንደሆነ አብራርተዋል።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ በሪሶ ፈይሳ በበኩላቸው በዞኖቹ በእርሻው ዘርፍ ያለው እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪና ከታሰበው በላይ ምርታማ መሆን የሚቻልበት ነው ያሉ ሲሆን በክልሉ ግብርና ቢሮ ሥልጠናና በድጋፍ ሲሰጥ እንደነበር አስታውሰዋል።

አቶ በሪሶ አክለውም፤ በዞኖቹ የተለያዩ የግብርና ግብዓት ማቅረብና በመካናይዜሽን ዘዴ የሚያርሱበት መንገድ በመመቻቸቱ ተጨባጭ ውጤት እያስገኘ ይገኛል ብለዋል።

እንደ አቶ በሪሶ ገለጻ፤ በደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች የአርሶና አርብቶ አደሩ ምርትና ምርታማነት የበለጠ ለማሳደግ የግብርና ግብዓት ማሟላቱ ላይ የሚደረገው ትኩረት ተጠናክሮ ይቀጥላል።

# ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በአሲድ የተጠቃን አፈር በኖራ የማከም ሥራ እየተሠራ ነው

## - ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ለኖራ መግዣ ከመንግሥት ተፈቅዷል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የ2016/17 የመኸር እርሻ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና የታቀደውን ምርት ለማግኘት በአሲድ የተጠቃን መሬት በኖራ የማከም እንቅስቃሴ መጀመሩን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በአሲድ የተጠቃን መሬት በኖራ በማከም ዳግም የተሻለ ምርት እንዲሰጥ ለማድረግ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ በጀት ከመንግሥት መፈቀዱንም አስታውቋል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2016/17 በመኸር እርሻ የ2016/17 የመኸር እርሻ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና የታቀደውን ምርት ለማግኘት በአሲድ የተጠቃን መሬት በኖራ የማከም እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

የ2016/17 የመኸር እርሻ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በአሲድ የተጠቃን መሬት በኖራ ማከም ያስፈልጋል ያሉት አቶ ከበደ፤ በአሲድ የተጠቃን መሬት በማከም ዳግም ምርት እንዲሰጥና ምርታማነት እንዲያድግ ለማድረግ ለኖራ መግዣ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ከመንግሥት ተፈቅዷል ብለዋል፡፡

አብዛኛው ምርት የሚሰጥ አፈር ወደ አሲዳማነት እየተቀየረ በመሆኑ በኖራ ለማከምና አሲዳማነቱን በማከም ምርትና ምርታማነቱን ለመመለስ ኖራ ከሚያመርቱ ፋብሪካዎች ግዥ የመፈፀም ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

"ኖራን ከፋብሪካዎች በመግዛት ለአርሶ አደሮች ተደራሽ የማድረግ እቅስቃሴ እየተደረገ ነው፤ አርሶ አደሮች ኖራ ተደራሽ ከተደረገላቸው አሲዳማ መሬታቸውን አክመው ምርታቸውን እንዲያሳድጉ ያግዛል" ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ መሬታቸውንም በኖራ እንዴት እንደሚያክሙት የባለሙያ እገዛ እንዲያገኙ ማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በ2016/17 የመኸር እርሻ የአፈር አሲዳማነትን ለማከም እየተሠራ ባለው ሥራ በአምስት ክልሎች ማለትም በአማራ፣ በኦሮሚያና በሌሎች ሶስት ክልሎች ለሰርቶ ማሳያ የሚሆን 100 ሺህ ሄክታር መሬት የማከም ሥራ እየተከናወነ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡



የአፈር አሲዳማነትን በኖራ የማከም ሥራ

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ምርትን የሚያበዙና የሚያሳድጉ ግብዓቶችን ማለትም የአፈር ማዳበሪያ፤ ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ፣ ሰብሉን ከአንበጣና ከተለያዩ በሽታዎች መጠበቅ፣ መካናይዜሽንና ምርጥ ዘር የመጠቀም ሥራ በሰፊው እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ ጎን ለጎንም የአፈር አሲዳማነትን በማከም ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የአፈር አሲዳማነትን ለማከም ከፍተኛ በጀት የሚጠይቅ በመሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከማዕድንና ከገንዘብ ሚኒስቴሮች ጋር በቅንጅት እየሠራ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ እየተሠራ ባለው ቅንጅታዊ ሥራም ገንዘብ ሚኒስቴር ለኖራ መግዣ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ለግዥው ፈቅዷል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የምርትን ብዛትን፣ ጥራትን የሚያሳድጉና የሚጨምሩ ምርጥ ዘሮችን የመጠቀም ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ ያለው የአፈር አሲዳማነትን የማከም ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# “ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስመምህራን የሰጡት እውቅና ይበልጥ እንድንሠራ የሚያበረታታ ነው”

**- የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መምህራን በትውልድ ግንባታ ለሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የሠጡት እውቅና ይበልጥ እንድንሠራ የሚያበረታታ ነው ሲል የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አስታወቀ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባካሄደው 36ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ በመገኘት ከአባላቱ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት፤ ኢትዮጵያን ከሚያስቀጥሉ ምሰሶዎች መካከል አርሶ አደር፣ ወታደርና መምህር ወሳኝ ናቸው ብለዋል።

አርሶ አደሩ እያመረተ በኑሮ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣ መሆኑን ጠቅሰው፤ መምህራንና ወታደር ደግሞ ለኢትዮጵያ እና ለትውልዱ ቀጣይነት ዋጋ የሚከፍሉ፣ እውቀታቸውንና ሕይወታቸውን ሳይሰስቱ የሚሰጡ መሆናቸውን አንስተዋል፤ በመሆኑም ክብር ይገባቸዋል ሲሉ እውቅና ሠጥተዋል፡፡

የኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስ በንቲ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለመምህራን የሰጡት እውቅና ትውልድን የመቅረጽ ተግባራችንን አጠናክረን እንድንቀጥል ተነሳሽነት የፈጠረ ነው ሲሉ ለኢዜአ ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሀገሪቱ የመጨረሻው ሕግ አውጪ አካል በሆነው ምክር ቤት ፊት የሰጡት እውቅና ህብረተሰቡ ለመምህራን ዘወትር ክብር መስጠት እንዳለበት የሚያስገነዝብ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ መምህራን ሁሌም ሀገርና ትውልድን አስቀድመው እንደሚሠሩ ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ለዘመናት ባለፈችባቸው የትውልድ ግንባታ ሂደት ውስጥም ትልቁን ሚና እንደሚይዙ ጠቁመዋል፡፡

በቀጣይም ይህንን ሚናቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉም ነው የገለጹት፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ መምህራን ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች አቅም በፈቀደ አግባብ መንግሥት ምላሽ ለመስጠት እንደሚሠራ መግለጻቸውንም አድንቀዋል፡፡



ክተር ዮሐንስ በንቲ

# “በመዲናዋ የተካሄደው...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የሚጥል መሆኑን አንስተው፤ ኮሚሽኑ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሆነ ስለምረዳ የምክክር ሂደቱም በተለያዩ ከተሞች በቅርቡ እንደሚከናወን እጠብቃለሁ ብለዋል።

ሌላኛው የጋሞ አባት አቢጤ አደሬ በበኩላቸው፤ ሀገራዊ ምክክሩ ከመነሻው ለሀገርና ለሕዝብ ቅድሚያ መስጠት፣ ችግሮች ተፈተው ዘላቂ መፍትሄ እንዲገኝላቸው በጥብቅ የመሻት ውጤት መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባ አስረድተዋል።

በአጀንዳ ማሰባሰብ ምዕራፉ በአዲስ አበባ የተከናወነበት አግባብ አስተማሪና ለብዙዎች ተስፋ የሰጠ ነው ያሉት የጋሞ አባት፤ ኮሚሽኑ አጋር አካላቱን ፣ ተባባሪዎቹንና መላውን ህብረተሰብ በማስተባበር በተለያዩ ከተሞችም ተመሳሳይ ሂደቶች እንዲከናወኑ የጀመረውን ጥረት ማጠናከር አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

“እኛ የጋሞ አባቶች በምክክር እናምናለን፤ ለዚህም ግጭቶች በተነሱ ወቅቶች በአካባቢያችን ባህል መሠረት ሳር ይዘን በመለመን ለንግግርና ለሰላም በር እንዲከፈት እንጥራለን” ያሉት የጋሞ አባት፤ በሠለጠነ መንገድ መወያየት ለሁላችንም የሚበጅ ጉዳይ በመሆኑ የኮሚሽኑን ሥራ መደገፍና ሂደቱን ማፋጠን ይገባል ብለዋል።

በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚገኙ ዜጎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምክክሩ መድረክ ዕውን መሆን እስከዛሬ ሲያደርጉ የነበረውን ተሳትፎና ድጋፍ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

የምክክር ኮሚሽኑ በበኩሉ የአጀንዳ ማሰባሰብና ቀሪ ሥራዎችን በተቻለ ፍጥነትና አሳታፊ በሆነ መልኩ በዋና ዋና አስተዳደሮች በማካሄድ ሕዝቡ ተስፋ ያደረገበትን ሂደት በባለቤትነት ስሜት እንዲመራው ማድረግ አለበት ብለዋል።

“በምክክር ኮሚሽኑ ሥራዎችም ሆነ በተለያዩ የምክክር መድረኮች ላይ ተሳትፎ አድርገናል፤ አሁንም ሂደቱ እንዲሳካ የበኩላችንን እንወጣለን” የሚሉት ደግሞ ሌላኛው የጋሞ አባት ካኡሙሩጌታ ሜንሳ ናቸው።

በቀጣይ ዓመት ሊጀመር ለታቀደው የሀገራዊ ምክክር መድረክ የሚከናወኑ ሥራዎች ግልጽና አሳታፊ መሆናቸው መልካም ተግባር መሆኑን ጠቁመዋል።

ምክክሩ ለችግሮቻችን ቁልፍ መሆኑን ካመንን ሂደቱ በተጠናከረ መንገድ እንዲቀጥል ሃሳብ መስጠትና ድጋፋችንን ማጎልበት አለብን ያሉት የጋሞ አባት፤ ኮሚሽኑም ከአዲስ አበባ በመቀጠል በሌሎች አካባቢዎች እንዲሁም በውጭ ሀገራት ያለውን ኢትዮጵያዊ ባሳተፈ መልኩ የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱን በወቅቱ ማከናወን እንዳለበት አንስተዋል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በአዲስ አበባ ያካሄደውን መድረክ በመገምገምና በቀጣይ ሊሻሻሉ የሚገባቸውን አፈጻጸሞች በማሻሻል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፉ በተመሳሳይ መልኩ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርና በ12ቱ ክልሎች እንዲሁም በፌዴራልና በዳያስፖራ ደረጃ እንደሚቀጥል ማሳወቁ የሚታወስ ነው።

# የግብርና ቆጠራ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ቆጠራውን በበላይነት ለመምራት የተቋቋመ አብይ ኮሚቴ አስታወቀ።

የፕላንና ልማት ሚኒስትርና የአብይ ኮሚቴው ሰብሳቢ ፍፁም አሰፋ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የግብርና ቆጠራ ከዚህ በፊት የተካሄደው ከ22 ዓመት በፊት ነበር። ባለፉት ዓመታት በግብርናው ውስጥ በሚመረቱ የምርት አይነቶች፣ በምርት ወቅት፣ በግብዓት አጠቃቀም በጥቅሉ ከግብዓት ጀምሮ እስከ ግብይት ድረስ ለውጦችን አስተናግዷል።

በበጋ በማምረት ልምድ፣ በግብርና ማዘመንና በእንስሳት ሀብት ልማት ላይም ትልልቅ ስኬቶች ተመዝግበዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ቆጠራው በመዘግየቱ ምክንያት በግብርናው ዘርፍ የመጡ አዳዲስ ጉዳዮችን ለማካተት አዳጋች ሆኖ ቆይቷል ብለዋል።

የነበረን የመረጃ መሰብሰቢያ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ዘመኑን የዋጀ መረጃ መስጠት የሚችል ቆጠራ ለማከናወን ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ ዝግጅቱ ቆጠራውን ለማከናወን በፋይናንስ፣ በሎጂስቲክስ፣ የሰው ኃይል እና ምን አይነት የቆጠራ ዘዴ መደረግ አለበት የሚለውን የሚያጠቃልል መሆኑን ጠቅሰዋል።

ቆጠራው በሀገሪቱ የሚገኙ ሁሉንም ወረዳና ቀበሌዎች የሚያካትት መሆኑን ጠቁመው፤ በሶስቱም የምርት ወቅቶች ማለትም በመኸር፣ በበጋ መስኖ እና በበልግ የሚደረግ ነው። በዚህም አነስተኛ ይዞታ ባለው አርሶ አደር፣ በኢንቨስትመንት የሚለሙ ሰፋፊ እርሻዎችና በማህበር የሚለሙ መሬቶችም ይካተታሉ ብለዋል።

ቆጠራው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ምዕራፍ ሁለት አካል በመሆኑን በስፋትና በትልቅ ትኩረት የሚከናወን መሆኑን ጠቅሰው፤ አጠቃላይ በጀቱ ከ16 ቢሊዮን ብር በላይ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከዚህ ውስጥ ሦስት ቢሊዮን ብር በመንግሥት የሚሸፈን ሲሆን ቀሪውን በጀት ደግሞ ከአጋር አካላት ለማግኘት እየተሠራ ነው ብለዋል።

የግብርና ሚኒስትርና የአብይ ኮሚቴው ተባባሪ ሰብሳቢ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ግብርና ከሀገሪቱ አጠቃላይ ሀገራዊ ጥቅል ምርት አንድ ሦስተኛውን ይሸፍናል። ስለሆነም ቆጠራው ከግብርናው ባለፈ ለሀገሪቱ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ግብርና ላይ የሚመጡ ለውጦችና ከግብዓት ጀምሮ እስከ ምርት ድረስ ያሉ ጉዳዮች ላይ ከመረጃና ዳታ ተአማኒነት ጋር የሚነሱ ጉዳዮች እንዳሉ ጠቅሰው፤ ይህን በአግባቡ የመቁጠርና መረዳት ጉዳይ ግብርናው በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን አስተዋጽኦ ለመረዳት ትልቅ ትርጉም ይኖረዋል ብለዋል።

ከ20 ዓመት በፊት ግብርና ቆጠራ ሲደረግ የመስኖ ስንዴ እንዳልነበረ ጠቅሰው፤ ባለፉት አምስት ዓመታት የመስኖ ስንዴ በክረምት ከሚመረተው ምርት ጋር እኩል የሆነበት ጊዜ ላይ ተደርሷል ሲሉ ገልጸዋል።

ከዚህ በፊት በከተማ ከሚሠራው ግብርና በአሁኑ ሰዓት ያለው የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ ትልቅ ለውጥ እንደተመዘገበበት አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት ብቻ ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም ማልማት ችላለች ያሉት ዶክተር ግርማ፤ በተያዘው ዓመት ደግሞ ይህን ቁጥር ወደ 12 ሚሊዮን ሄክታር ለማሳደግ እየተሠራ ነው። ከ20 ዓመት በፊት ቆጠራ ሲካሄድ ምንም አይነት የሚቆጠር ኩታ ገጠም እርሻ አልነበረም ሲሉ አስረድተዋል።

ስለሆነም የግብርና ቆጠራው በዘርፉ የመጡ ለውጦችና ትግበራዎችን ለማካተት፣ በመረጃ ላይ የተመሠረተ እቅድ ለማቀድ እና የግብርና ዘርፉ ኢኮኖሚው ላይ ያለውን ድርሻ ለመገንዘብ እንዲሁም አጠቃላይ ያለውን ሀብት ለማወቅ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር በከር ሻሌ (ዶ/ር)፤ ቆጠራውን ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች በመጠናቀቅ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በሥራው ላይ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 62 ሺህ ዜጎች እንደሚሳተፉ ጠቅሰው፤ በአሁኑ ሰዓት የአሠልጣኞች ሥልጠና እየተሰጠ መሆኑን አመላክተዋል።

ቆጠራው ከመስከረም 2017 ጀምሮ ለአንድ ዓመት የሚካሄድ ሲሆን፤ ሥራውን ግብርና ሚኒስቴርና ፕላንና ልማት ሚኒስቴር በጋራ እንደሚያስተባብሩት ተጠቁሟል።

# የክልል መዋቅራዊ ጥያቄዎች...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ርዕሰ መስተዳድሩ ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት ከተሠሩት አንዱና ትልቁ የለውጡ ትሩፋትና ስኬት መካከል ሕዝቡን ባለቤትና አሳታፊ ያደረገ እውነተኛ ዴሞክራሲ የተረጋገጠበት የክልል አደረጃጀት ሥራ ተሠርቷል።

ያለፉት የለውጥ ዓመታት መንግሥት የተሳካ የፖለቲካ ጉዞ የተጓዘበት ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ በለውጡ እውነተኛ ዴሞክራሲ፣ ህዝብ የወደደውን የፈቀደውን የተገነዘበውን እንዲወስን ተደርጓል ብለዋል።

የዜጎች የክልልነት ጥያቄ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መካሄዱ እንደሀገር ለውጡ የተሳካበት ተግባር መሆኑን ጠቅሰው ለውጡ በርካታ የውጭና የውስጥ ሃይሎች በመቋቋም ሕዝበ ውሳኔ በማድረግ ስኬታማ ጉዞ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

አዲሱ ክልል ይስተዋሉ የነበሩ የማዕከል አገልግሎት ተደራሽ፣ ፍትሀዊ፣ የፖለቲካ ተሳትፎ ያለበት፣ የተጠቃሚነትና አሳታፊነት ችግሮችን ሊቀርፍ በሚችል መልኩ መመሥረቱን የገለጹት አቶ ጥላሁን፣ አዲሱ ክልል ጥያቄዎችን መመለስ በሚያስችል መልኩ ዞኖችን በማደራጀት ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል ብለዋል።

የሕዝብ እንደራሴዎች ተመካክረው ያመጡት በክልልነት እንደራጅ ሃሳብ መላው ሕዝብ ይሁንታን ማግኘቱን በመግለጽ፣ እውነተኛ ዴሞክራሲ በተጨባጭ የታየበት የክልል አደረጃጀት ሥራ መሠራቱንም ተናግረዋል።

አዲሱ ክልል የሰላም፣ ብልጽግና፣ የመቻቻል ተምሳሌት እንዲሆን ራዕይ ተይዞና መሠራቱንና የሕዝብ ይሁንታ ማግኘቱን ገልጸው፣ ለውጡ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሕዝብ በራሱ በነቂስ ወጥቶ የራሱን ክልል፣ ሕገ መንግሥት፣ አርማ፣ሰንደቅ ዓላማ መርጦ በውሳኔ ተግባራዊ እንዲሆን መደረጉን አስረድተዋል።

ከክልል ምስረታ በኋላ ሕዝቡ ሀብቱን በመስጠት ድጋፉን በተጨባጭ ማሳየቱን በመግለጽ፣ ሕዝቡ የመረጠውና የወሰነው ክልል ወደ ሥራ ሲገባ ከፍተኛ ድጋፍ ማድረጉን ገልጸዋል።

የክልሉ መንግሥት ዜጎች የሰጡትን የቤት ሥራ በመገንዘብ ባለፉት ጊዜያት ያልተሠሩ ሥራዎች በሚያካክስ መልኩ እየሠራ እንደሚገኝ የገለጹት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ መንግሥት የሕዝብን ጥያቄዎች መመለስ በሚያስችል አግባብ ወደ ተግባር ገብቷል ብለዋል።

በተጨማሪም የሽግግር ጊዜ እቅድ በማውጣት የክልል ማዕከላትን የማደራጀት፣ የሰው ሃይል ማሠማራት፣ የአሠራር ሥርዓቶችን ለማሳለጥ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰው፣ በተለይም 54 አዋጆችን፣ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣት መቻሉን ተናግረዋል።

የእቅድ ክለሳዎችን በግብርና፣ በቱሪዝም፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በማዕድን፣ በሥራ እድል ፈጠራ ቁልፍ ተግባራትን በመለየት ወደ ተግባር መግባቱን በመግለጽ በቀጣይ የተሻለ በመሥራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ብልጽግና እንዲረጋገጥ ማድረግ የሚያችል ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

# ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ውይይቱ በሁለቱ ሀገራት መካከል ግንኙነት ለማጠናከር አይነተኛ ሚና እንዳለው ጠቅሰው የጋራ ደህንነትን ለማጠናከር የጎሳ ግጭቶችና የከብት ዘረፋ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል አቅጣጫ መቀመጡን ገልጸዋል፡፡

በስብሰባው በሁለቱ ሀገራት የድንበር አካባቢዎች ያሉ የልማት እድሎችንና ተግዳሮቶች መገምገማቸውን ጠቅሰው በተለይም በጸጥታ፣ በማህበረሰብ ልማትና በስደተኞች ዝውውር የጋራ ደህንነትን ከማጠናከር አኳያ ይስተዋሉ የነበሩ የጎሳ ግጭቶች ዘረፋዎች ዙሪያ የነበሩ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት የሚያስችል አቅጣጫ እንደተቀመጠም አስረድተዋል።

በደቡብ ሱዳን አዋሳኝ የሆኑ የቤኒሻንጉል ምዕራብ ኢትዮጵያና የጋምቤላ ክልሎች በጋራ የሚሠሩበትና የጋራ ደህንነታቸውን የሚያስጠብቁበት ሁኔታ መፈጠሩን በመግለጽ የጋራ ልማት፣ ንግድንና የኢንቨስትመንት መሠረተ ልማት ትስስር እንዲጠናከር ለማድረግ የጋራ ስምምነት መደረጉን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን የጋራ ባህል፣ ታሪክና ንግድ ያላቸው ሀገራት ናቸው ያሉት አምባሳደሩ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን በማጎልበት ችግሮችን መቅረፍ ይገባል ብለዋል።

የሚቀጥለው ስብሰባ በደቡብ ሱዳን የሚካሄድ መሆኑን ጠቅሰው የጋራ የሆኑ ጉዳዮች ላይ አቅጣጫዎች እየተቀመጡ ያለውን ትብብር ለማጠናከር እንደሚሠራም ገልጸዋል።

የሁለቱን ወንድማማች ሀገራት ሊያገናኝ የሚችል የመንገድ ልማት በደቡብ ሱዳን በኩል መጀመሩን ገልጸው በተለይም ንግድን የጋራ ልማትን በማጠናከር በአካባቢው የሚስተዋሉና ወደ ግጭት ሊያመሩ የሚችሉ ጉዳዮችን የሚቀርፍ መሆኑን አስረድተዋል።

የጋራ ልማት ተጠቃሚነትና ሰላምና አብሮነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም የወደፊት ራዕይ ያመጣል ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ ሁለቱ ሀገራት በልማት ትስስር አብረው እንዲነግዱና እንዲተሳሠሩ በጋራ ለመሥራት ያስችላል ብለዋል።

በደቡብ ሱዳን ምክትል የውጭ ጉዳይና ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር መንዴይ ሰማያ ኩምባ በበኩላቸው፣ ለሁለት ቀናት የተካሄደው ስብሰባ በሁለቱ ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነትና ግንኙነትን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ይረዳል ብለዋል።

ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር ታሪካዊ ባህላዊ የሕዝብ ለሕዝብ ወዳጅነት እንዳላት ጠቅሰው በተለይም በኢኮኖሚ፣ በጸጥታ፣ በመሠረተ ልማት ማስፋፋትና ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎችን በመግታት ዙሪያ በጋራ ለመሥራት እንደሚያስችልም ተናግረዋል።

መግባባት የተፈጠረባቸው ጉዳዮች የሁለቱን ሀገራት የጋራ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠን እንደሚረዱም ገልጸዋል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

## የውስጥ ገጾች



የነብስ አድን ክትባት ዘመቻ

ገጽ 9

የጤና መኮንኑ አርሶ አደር

ገጽ 10



# ‹‹አደጋን እየተከላከልን ማልማት፤ እያለማን አደጋን መከላከል የግድ ነው››


-በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተመራማሪ እና አስተማሪ ተባባሪ ፕሮፌሰር መሣይ ሙሉጌታ ( ዶ/ር)

ገጽ 7



የራይድ ዘራፊው መጨረሻ

ገጽ 11



ውሳኔ ብቻውን ውሳኔ ነው?

ገጽ 14

“እኔ እማውቀው አለማወቄን ነው”

ገጽ 15

ሰነድ ማጥፋት ወይስ ቆሻሻ ማስወገድ?

ገጽ 12

# ነፃ ሃሳብ

## ምክክር- አማራጭ የሌለው መፍትሄ

ታሪኩ ዘለቀ

አለመግባባትና ግጭቶችን በሰለጠነ መንገድ ለመፍታት ምክክር /ውይይት/ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው። ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችና ጥናቶችም ይህንኑ ነው የሚጠቁሙት:: ይሁን እንጂ በሳይንሳዊ መንገድ የሚተገበረው የምክክር መድረክ የየአገራቱ ባህል እና የማህበረሰብ ስነ ልቦና ውቅር ያገናዘበ ሊሆን አይችልም። በዚህ ምክንያት ተግባር ላይ ሲውል ነባራዊው የማህበረሰብ ስሪትን ካላገናዘበ በስተቀር ውጤታማ የማይሆንበት እድል ሰፊ ነው። ለዚህ ነው አንድ ወጥ የሆነ ሳይንሳዊ ቀመር ያለው የምክክር አጀንዳ ማዘጋጀት እንደማይቻል የዘርፉ ምሁራን የሚናገሩት::

በጉዳዩ ላይ ተከታታይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚገልፁት «ሀገራዊ ምክክር» እንደ አንድ የማህበረሰብ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀውሶች መፍቻ ዘዴ በማህበረሰብ ሳይንስ ጠቢባን የተጠና አንድ ወጥ ትርጉም የተሰጠው ባለመሆኑ ለሁሉም የሚስማማ ሞዴል አይደለም:: ጥናቶች እንደሚያሳዩት ግልፅ የትግበራ፣ እቅድና የአሰራር ደንቦችን ከተከተለ እንዲሁም ሀገራዊ ጉዳዮች በጥልቀት ከተመረመሩና በዛው መሰረት ላይ ከቆሙ የስኬት እድሉ ከፍ ያለ እንደሚሆን ይገመታል::

ምክክር ዋልታ ረገጥ የሆኑ የልዩነትና የግጭት ምክንያቶችን ለማርገብና ለማቀራረብ አቅም ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል:: እንዲህ አይነት ምክክሮችን በርካታ ሀገራት ሞክረውታል:: ተሳክቶላቸው ሀገራቸውን ወደ ሌላ ምዕራፍ ያሻገሩ እንዳሉ ሁሉ ለስኬት ያልበቁ ምክክሮችን ያካሄዱ ሀገራትም አሉ::

ሀገራት የውስጥ ችግሮች ሲገጥሟቸው ሕዝብን መሰረት ያደረጉ መድረኮችንና ሌሎች የውይይት መርሀ ግብሮችን ሲዘረጉ እንመለከታለን:: ከቦስኒያ የእርስ በርስ ፍጅት በኋላ የተዘረጉ ሀገራዊ ምክክሮች አብዛኞቹ ለውጥ ማምጣታቸውን ተመልክተናል:: ኢሲያዊቷ ካምቦዲያ ሀገራዊ ምክክርን ተግብራ ውጤት ካመጡ ሀገራት መካከል ተጠቃሽ ነች::

በአፍሪካም በሀገራዊ ምክክር ያለፉ ችግሮቻቸውን በእርቅና በምክክር አሉ:: በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱት አንዷ ቱኒዚያ ናት:: የአረብ አመፅ የሚባለው አብዮት ተስፋፍቶ በአገሪቱ አመፅ ተነስቶ ቀውስ ተፈጠረ:: የነበረውን ቀውስ ለመፍታት ቱኒዚያ የምክክር ኮሚሽን አቋቁማ ምክክር በማድረግ ስኬታማ ውጤት አግኝታበታለች::

የቱኒዚያ ምክክር ለስኬት የበቃበት ምክንያት የመፍትሄ ጠንሳሾች በሆኑት ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አማካኝነት መሆኑ ይነገራል:: የዚህ ውይይት አመቻቾች ከታችኛው ማህበረሰብ ሀሳብ አምጥተው በብዙ ከመከሩ በኋላ አደጋ ውስጥ የነበረችን ሀገር ከነበረችበት ቀውስ እንድትወጣና እንድትረጋጋ አድርገዋል:: የምክክሩ አመቻቾች ከየትኛውም ፖለቲካ ፓርቲ ነፃ የሆኑ፣ ከማንኛውም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት፣ አትራፊነት ጉዳይ የሌላቸው፣ሀገሪቱ የገጠማትን ችግር ብቻ መፍታት ዓላማ ይዘው የተነሱ ሰዎች ስለነበሩ ተሳክቶላቸዋል::

ደቡብ አፍሪካም ከአፓርታይድ ስርዓት መጠናቀቅ በኋላ «ያለፈውን እንርሳና የወደፊቱን ብቻ እናስብ» በሚለው መርሀቸው መሰረት ደም አፋሳሽ የነበረውን የታሪክ ክፍላቸውን በዕርቅ ቆልፈውበታል። የእርቅና እውነት አፈላላጊ ኮሚሽን «Truth and Reconciliation Commission» አቋቁመው ችግሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ ፈትተዋል::

እኤአ በ1994 የተከሰተው የሩዋንዳው የዘር ጭፍጨፋ የተረጋጋውና ሰላም የሰፈነበት ሀገር መገንባት የተቻለው ተመሳሳይ ምክክር ከተደረገ በኋላ ነው:: ከሁሉም የከፋ የዘር ፍጅትን ያስተናገደችው ሩዋንዳ ሀገራዊ ምክክርን የብሄራዊ እርቅ ማሳለጫዋ አድርጋ በመጠቀሟ ከታላቁ ቁስል በፍጥነት በማገገም ለሌሎች አርአያ መሆን ችላለች::

ከላይ በምሳሌነት የጠቀስናቸው ሀገራት አሻጋሪ የሆነና ከነበሩበት ችግር ሊያወጣቸው የሚችል ምክክር ማድረግ ችለዋል:: ቱኒዚያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሩዋንዳ ባካሄዱት ሀገራዊ ምክክር ላይ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ አካላት በሙሉ መካተታቸውንና ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል መወከሉን አስቀድመው አረጋግጠዋል:: ይህ ነው ለሌሎችም ምሳሌ እንዲሆኑ ያስቻላቸው:: ሀገራቱ ምክክሩን የጀመሩት ሁሉም እንደሚሳተፍ አረጋግጠው ነበር:: በዚህ ምክንያት የተሳካ ምክክር አድርገዋል::

ዛሬ ደግሞ ተራው የኢትዮጵያ መሆኑን እየተመለከትን ነው። ስኬታማ አፈፃፀም ያላቸው አገራትን ተሞክሮ በመቀመርና ከራሷ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በመቃኘት ለምክክሩ ቅድመ ዝግጅቶችን እያጠናቀቀች ትገኛለች:: ለዚህ ነው መጪው መድረክ የሀሳብ ልዕልና የሚንፀባረቅበት እንደሚሆን የተገመተው:: በውጤቱም አዲስ የችግር አፈታት ባህል የሚዳብርበት እንደሚሆን ተስፋ ተጥሎበታል:: የሀሳብ ልዩነቶችን በማስተናገድ ችግሮችን ለመፍታት ምክክር ወሳኙ መሆኑን እንደሚያመላክትም ይጠበቃል::

እንደሚታወቀው ሀገራዊ ምክክር ለግጭትና አለመግባባቶች ምክንያት የሆኑ ሀሰተኛ ትርክቶችን በማስቀረት አንድነትን የሚያመጡ የጋራ ትርክቶችን በመገንባት በኩል ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል:: እስከ ዛሬ ድረስ በሀገራችን ሰፍኖ የኖረው የባላንጣነት ፖለቲካ በተሳሳተ ትርክቶች ላይ የተመሰረተ መሆኑ ይታወቃል:: ይህንን ለማረቅ መፍትሄው በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ በስክነት መወያየት ነው። ትርክቶቹ በአጀንዳነት ለውይይት ቀረቡ ማለት ንፋስ መታቸው ወይም ተጋለጡ ማለት ነው:: ስለዚህ በመሰል ትርክቶች ላይ ቁጭ ብለን ጥቅምና ጉዳታቸውን ስንወያይ በምትካቸው ሊተካ የሚችለውን ሌላ እውነተኛ የጋራ ትርክት መፍጠር ያስችላል::

የመልካም ነገሮች ሁሉ መጀመሪያ ምክክር በመሆኑ ለሀገርም ሆነ ለሕዝብ ይዞት የሚመጣው አወንታዊ ጎን ቀላል ነገር አይደለም:: ማንኛውም ነገር ፀንቶ እንዲቆይ ከተፈለገ ምክክር ያስፈልጋል:: ኢትዮጵያን ለማሳደግና አሁን ካለችበት የበለጠ ከፍ ለማድረግ፣ አሁን ካሉብን ችግሮች ነፃ ለመውጣት ምክክር አስፈላጊና ወሳኝ ነው::

ምክክሩ አዲስ ተስፋን ይዞ እንደሚመጣ የብዙ ኢትዮጵያዊያን ምኞትና ፍላጎትም ጭምር ነው:: በእርግጥም በኢትዮጵያ ምክክር አዲስ ልደት ነው ማለት ይቻላል:: አዲስ ልደት ደግሞ አዲስ ተስፋ ሰንቆ የሚመጣ ነው:: እናም የኢትዮጵያችንን ችግሮች ነቅሰን የምናወጣበት፣ መፍትሄውንም የምንጠቁምበት፣ ለልጆቻችን የተደላደለ ኑሮ የሚኖሩበትን ሀገር ለመፍጠር የምናመቻችበት መድረክ ነው::

ኢትዮጵያ በሀገረ መንግስት ግንባታ ከዓለም ሀገራት ቀደምቷ እንደሆነች ሁሉ በሀገራዊ ምክክር በሀሳብ ልዕልና የተመሰረተ ምክክር ማሳያም መሆን ይጠበቅባታል:: ይህ እንዲሆን የአጀንዳ ልየታው ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት እንዲሁም ተሳታፊ አካላት ሁሉ መካተታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ውይይታችን በሀሳብ ልዕልና ላይ የተመሰረተ፣ የማንም ሀሳብ የማይናቅበት፣ የማንም ጥያቄ የማይረገጥበት፣ሁሉም ሰው የሚሰማውን ስህተት እንኳ ቢሆን አቅርቦ በውይይቱ ሂደት እየታረመ እንዲሄድ ምቹ ሁኔታ የሚፈጠርበት ሊሆን ይገባል:: አጀንዳዎች በትክክል ተለይተው ከወጡ የምክክሩን ሂደት 50 በመቶ እንዳለቀ ሊቆጠር ይገባል:: በመሆኑም አጀንዳ በማፍለቅ የሚሳተፉ አካላት በከፍተኛ ጥንቃቄና ኃላፊነት በተሞላው መንገድ ሊሰሩት ይገባል::

በእርግጥ ተሳታፊዎች የመለየት ስራውን አሳታፊ እና አካታች በሆነ መልኩ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ሲከናወን ተመልክተናል:: የተለዩት ተወካዮች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ከሚያደርጉባቸው የምክክር ምዕራፎች መካከል በምክክር አጀንዳዎችን የመለየት አንዱ ነው። በተጨማሪ ምክክር የሚደረግባቸውን እጅግ መሰረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮችን አሳታፊና አካታች በሆነ ሂደት የመለየቱ ስራ በራሱ ምክክር የሚፈልግ ነው። ከሁሉ በላይ ጉዳዩ ቅንነትና መግባባትን የሚጠይቅ በመሆኑ ሂደቱ በቀጣይ ለሚከናወነው ሀገራዊ የምክክር ጉባኤ ስኬታማነት ቁልፍ ሚና ይኖረዋል:: በመሆኑም መምህራን፣ ምሁራን፣ በተለያየ ደረጃ የተውጣጡ የማህበረሰብ ክፍሎች በአጀንደ ልየታው በመሳተፍ ለችግሮቻችን መፍትሄ ሀሳብን ማምጣት ይጠበቅባቸዋል::

በተለያየ ግዜ ከሚወጡ መረጃዎች መረዳት እንደምንችለው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ስራውን ወደፊት ማምጣት ችሏል:: በአዲስ አበባ ከተማ የአጀንዳ ልይታ አከናውኗል:: በአጀንዳ ልየታው የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፈዋል:: ህብረተሰቡን ያማከለ ውክልናም ተንፀባርቆበታል:: የተካሄደው አጀንዳ የማሰባሰብ ስራ ግልፅና አሳታፊ መሆኑን ተሳታፊዎች ተናግረዋል:: አጀንዳ በማሰባሰብ ሂደቱ መሰረታዊ የሚባሉ ችግሮችን የመለየት ስራ ተከናውኗል:: ህብረተሰቡ የሚያነሳው ማንኛውም ጥያቄዎች ቀርበዋል:: በኢትዮጵያ መንግስት አወቃቀር ውስጥ ህብረተሰቡ የማይፈልጋቸው ጉዳዮችንና መንግስት ያላሟላቸው ነገሮችን በዝርዝር ቀርበውበታል:: ከመንግስት የሚፈልጋቸው፣ ከሀገሪቱ መንግስት መዋቅር መከናወን የሚገባቸው ነገሮች በውይይቱ ቀርበው ተለይተዋል::

ይሁን እንጂ አንድ ጉዳይ ግን አሁንም በትኩረት ሊታይ ይገባል። እርሱም ኢትዮጵያ የተሟላ ምክክር እንድታደርግ ሁሉም አካል ተሳታፊ መሆን እንደሚጠበቅበት ማወቅ ነው:: የምክክሩ አንዱና ትልቁ ተግዳሮት የትጥቅ ትግል ለማድረግ ጫካ የገቡ እንዲሁም የሰላማዊ ፖለቲካ አቀንቃኝ ነን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችም «በኮሚሽኑ ላይ እምነት የለንም፣ ምክክሩ ላይ አንሳተፍም» የሚል አይነት ይዘት ያላቸው መግለጫዎችን በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲያወጡ መመልከታችን ነው:: እነዚህ አካላት ኮሚሽኑ እንዲመሰረት የተለያዩ ሀሳቦችን እንዳዋጡ ሁሉ ምክክሩ እንዲደረግም በራቸውን ክፍት ማድረግ አለባቸው::

ምክክር ሁሉን አቀፍ ጥቅም ስላለው መሳሪያ ይዘው ጫካ የገቡ አካላት የሕዝብ ጥያቄን አንግበው ከሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊከታተለው በሚችለው የምክክር መድርክ የሕዝብ ጥያቄዎቻቸውን የሚያቀርቡበት መንገድ መቀበልና መሳተፍ አትራፊ ያደርጋቸዋል:: ይህን እንዲሳካ በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጠበቅባቸው ኃላፊነት አለ:: ኢትዮጵያ ከፓርቲም በላይ በመሆኗ ለራስ ብቻ ከማሰብ ወጣ ብለው ውጤታማ ምክክር እንዲደረግና ሀገር ተጠቃሚ እንድትሆን ተሳትፏቸው በርትቶ የበኩላቸውን አስተዋፆ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል:: ትጥቅን እንደ መፍትሄ አማራጭ የወሰዱ ኃይሎች ወደ ጠረጴዛው እንዲመጡ ግፊት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በእርግጥ የእያንዳንዱ የኢትዮጵያዊ ችግር ሙሉ በሙሉ አሁኑኑ በሀገራዊ ምክክሩ ሊፈታ አይችልም:: ነገር ግን በጥንቃቄ የተመራ ምክክር ቢያንስ የተቀራረበ ሀሳብ ይዞ ለመውጣትና የችግሮቻችንን መነሻ ለማወቅ ያስችለናል:: ጫፍና ጫፍ የወጣን ሀሳብ ወደ መሀል ማቀራረብ አንዱና ትልቁ ተግዳሮት ቢሆንም በጋራ ሆነን የምንፈታው ሊሆን ይገባል::

የማንግባባቸው ጉዳዮች ብዙ ናቸው:: በምልክቶቻችን እና በጀግኖቻችን ጭምር አንግባባም:: የእኛ ሀገር ከሌሎች ሀገራት አውድ በመጠንም ቢሆን ልዩነት እንዳለው ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል:: ዋናው ነገር ሁሉም የፖለቲካ ተሳታፊዎች ምክክሩን ለሚያመቻቸው አካል እምነት በመስጠት አይሆንም ከሚለው ሀሳብ ወጥተው ወደ ጠረጴዛ ውይይት መምጣት አለባቸው::

የማንግባባቸው ጉዳዮች ብዙ ናቸው:: በምልክቶቻችን እና በጀግኖቻችን ጭምር አንግባባም:: የእኛ ሀገር ከሌሎች ሀገራት አውድ በመጠንም ቢሆን ልዩነት እንዳለው ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል

የፖለቲካ ፓርቲዎች ጠንካራ ሀገረ መንግስት ለመገንባትም ሆነ የፖለቲካ ባህላችንን ለማዳበር ብዙ መትጋትና መልፋት ይጠበቅባቸዋል:: ልዩነቶችን በውይይት መፍታት መለማመድ መጀመር አለባቸው:: ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆኑ በምክክር ሂደቱ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በንቃት መሳተፍ የውዴታ ግዴታው መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል::

የተጀመረው ምክክር ስኬታማ እንዲሆን መገናኛ ብዙሀን ዜጎች ስለ ጉዳዩ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሊሰሩ ይገባል:: ይህ ምክክር ሀገርን የማዳን፣ ኢትዮጵያውያንን የማቀራረብ፣ ሰላምን የመፍጠር ተልዕኮ እንዳለው በመተረክ አስቻይ ሁኔታን መፍጠር አለባቸው:: አለፍም ብለው «ኢትዮጵያውያን እንመክራለን መክረን ከችግሮቻችን መውጣት እንችላለን፣ ችግሮቻችንን በአንቀልባ አዝለን ቁጭ ማለት የለብንም፣ ዛሬ ላይ ቁጭ ብለን እውነትን በጋራ እንፈልግ» የሚሉ መሰል መልእክቶችን በማስተላለፍ ማህበረሰቡን ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል::

ምሁራን አሻጋሪ የመፍትሄ ሀሳቦችን ማፍለቅ ተቀዳሚና ቋሚ ስራቸው ሊሆን ይገባል:: መገናኛ ብዙሀን ያሉንን ጥንካሬ እሴቶች ለትውልድ ማስተማር ይጠበቅባቸዋል:: የትምህርትና የሀይማኖት ተቋማት ግብረገብ ያለውና ሀገር ወዳድ ትውልድ የመፍጥር ሚናቸውን መወጣት አለባቸው::

በድንቁርና ተባብሮ ከመጥፋት ይልቅ ተጋግዞ ክፉ ዘመንን ማሸነፍ ይገባልና ሁላችንም ሰላም፣ ዴሞክራሲና ፍትህ የሰፈነባት የጋራ ሀገር እንድትኖረን ተግተን እንስራ! ሰላም ከሰፈነባቸውና በእድገት ጎዳና ሽቅብ ከደረሱ ሀገራት እንደተማርነው በስክነት፣ በመረጋጋትና በከበሬታ መመካከር ሀገራዊ መፍትሄ መሆኑን ሁላችንም ልንገነዘብ ይገባል። ሰላም !!

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹አደጋን እየተከላከልን ማልማት፤ እያለማን አደጋን መከላከል የግድ ነው››

**- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ እና አስተማሪ ተባባሪ ፕሮፌሰር መሣይ ሙሉጌታ ( ዶ/ር)**



**ምሕረት ሞገስ**

የትናንቱ የገጠር ተማሪ የዛሬው ተባባሪ ፕሮፌሰር እና ተመራማሪ ዶ/ር መሣይ ሙሉጌታ የተወለዱት፤ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ኩዩ ወረዳ ከገርበ ጉራቻ ከተማ በ5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሃሌሉ ጫሪ በምትባል የገጠር ቀበሌ ነው:: በገርበ ጉራቻ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን የተከታተሉት መሣይ ሙሉጌታ (ዶ/ር)፤ እናት እና አባታቸው ከእርሳቸው በታች አሥራ አንድ ልጆችን ወልደዉ፣ አሳድገዋል፣ አስተምረዋልም::

አቶ ሙሉጌታ ለልጃቸው ባላቸው አቅም የትምህርት ቁሳቁስ ለማሟላት ጥረት አድርገዋል:: መሣይ (ዶ/ር) ወላጆቻቸው ድጋፍ የሚያደርጉላቸው ባላቸው ልክ በመሆኑ ቅያሪ ልብስም ሆነ ጫማ የማይኖርበት አንዳንዴም የተቀደደ ልብስ መልበስ እና የተገነጠለ ጫማ ማድረግ ግዴታ ሆኖባቸው በማይመች ሁኔታም ቢሆንም ትምህርታቸውን ተከታትለዋል:: የዶ/ር መሣይ አባት አቶ ሙሉጌታ ደግሞ ራሳቸው ሳይማሩ ልጃቸውን ትምህርት ቤት ሔደው ከማስመዝገብ ባሻገር፤ በተለይ የገበያ ቀን ሐሙስ ሐሙስ ልጃቸው ትምህርት እየተማረ መሆኑን ቦታው ድረስ ሄደው ይከታተሉ ነበር:: ክትትላቸው እስከ ስድስተኛ ክፍል የቀጠለ ሲሆን፤ ዶ/ር መሣይ መስመር መያዛቸውን ሲያረጋግጡ አባት ክትትል ማቆማቸውን ዶ/ር መሣይ ይናገራሉ::

በእርሳቸው እምነት ገጠር መወለድ ትምህርት ለመማር ያለውን ፈተና ከፍ ቢያደርገውም፤ ጥሩ የሚሆንበት አጋጣሚም አለ:: ገጠር ተወልዶ በቀላሉ ተስፋ መቁረጥ የሚታሰብ አይደለም:: ችግሮችን መጋፈጥ የተለመደ ነው:: በሌላ በኩል መጥፎ ሁኔታው ከልብስ እና ከመማሪያ ቁሳቁስ ጀምሮ ለትምህርት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮችን ማግኘት ቀላል አይደለም:: ቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን፤ ትምህርትን የመከታተያ ጊዜ እጥረትም ያጋጥማል:: ሙሉ ቀን መማር እና በፈለጉት ጊዜ ማጥናት አይቻልም:: ቀን የግብርና ሥራ ማለትም ማረስ፣ አረም ማረምና እና ሰብል መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን፣ ከብት መጠበቅም ግዴታ ነበር:: ስለዚህ ትምህርት በፈረቃ ነው:: ትምህርት ከመሄድ በፊት ወይም ከትምህርት ቤት ከመጡ በኋላ የግብርና ሥራውን ማጠናቀቅ ግዴታ ነው::

አሁን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአገር ልማት ኮሌጅ በምግብ ዋስትና እና የአደጋ ስጋትን በተመለከተ እያስተማሩ እና እየተመራመሩ የሚገኙት የዛሬው የዘመን እንግዳችን መሣይ ሙሉጌታ (ዶ/ር)፤ ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው:: በትምህርት ዘርፍ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ለመድረስ የቀራቸው አንድ ደረጃ ወይም ሙሉ ፕሮፌሰርነት ብቻ ነው:: ከእርሳቸው ጋር ከግል ሕይወታቸው ጀምረን አሁን እያስተማሩ እና እየተመራመሩበት ስላሉበት ዘርፍ በተመለከተ ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል:: መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- የገጠር ሕይወት ለትምህርት ምን ያህል ምቹ ነው?**

**ዶ/ር መሳይ፡**- ገጠር መወለድ ለትምህርት ሕይወት ጥሩ ጎንም አለው:: ጥሩ የሚያስብለው የገጠር ልጅ በብዙ ፈተና ውስጥ ስለሚያልፍ በትምህርት ሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙትን የተለያዩ ፈተናዎች ለማለፍ አይቸገርም:: መጥፎ ነገሩ ግን በእኛ ጊዜ የገጠር ሕይወት በእጥረት የተሞላ ነው:: የትምህርት ቁሳቁስ እና ጊዜ ማግኘት ፈተና ነው:: ነገር ግን ለግማሽ ቀን እየሠራሁ፤ ግማሽ ቀን እየተማርኩ ባሳልፍም አሁን ያለሁበት ደረጃ ላይ መድረስ ችያለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- የገጠር ሰው በተለይ በዛ ጊዜ አንዳንድ የተሻለ ግንዛቤ ያለው ሰው ካልሆነ ልጁን ለማስተማር ዝግጁ አይደለም:: እርሶ እንዴት ወላጆችዎ ፈቅደው አስተማርዎት?**

**ዶ/ር መሳይ፡-** ይሔ እኔንም በጣም የሚገርመኝ ጉዳይ ነው:: በቅርብ የተማረ ዘመድ አልነበረኝም:: አባቴ እንዴት ደርሶ መልስ ሃያ ኪሎ ሜትር እየሄድኩ ወንዙን፣ ተራራውን፣ ሜዳውን፣ መንደሩን እያቆራረጥኩ እንድማር እንደፈቀደልኝ አላውቅም:: ትምህርት ቤት መላክ ብቻ ሳይሆን፤ ባለው አቅም ሙሉ ድጋፍ አድርጎልኛል:: አልፎ ተርፎ ትምህርት እየተማርኩ መሆኑን ይከታተለኝ ነበር:: በአካባቢው የነበረው አንድ የገርበ ጉራቻ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ ነበር:: በዚያን ጊዜ በአካባቢውም የተማርነው ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበርን:: ስለሆነም የአባቴ ቆራጥነት ይገርመኛል::

**አዲስ ዘመን፡- በግማሽ ቀን ትምህርት ለዛውም 20ኪሎ ሜትር ደርሶ መልስ በእግር ሔደው፤ የግድ ማጥናት ያስፈልጋል:: ለዛ ደግሞ ጊዜ የለም:: እንዴት ዩኒቨርሲቲ መግባት ቻሉ?**

**ዶ/ር መሳይ፡-** ብዙም የትምህርት ጥቅም ገብቶኝ ሳይሆን፤ እንዲሁ ገና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ስማር ከብቶችን ስጠብቅ ወይም አረም ሳርም ትንሽ አረፍ ስል አነብ ነበር:: በተለይ እስከ ስድስተኛ ክፍል የትምህርትን ጥቅም ተረድቻለሁ ለማለት አልደፍርም:: ነገር ግን አስተማሪዎች ከገበሬው ሻል ያለ ልብስ ለብሰው ስናይ፤ እኛም አድገን አዲስ ልብስ እና ጫማ እንገዛለን ከማለት ውጪ ብዙም በትምህርት እዚህ ላይ እንደርሳለን አንልም ነበር::

ነገር ግን አንድ ቀን የትጋቴ መነሻ የሆነ ይመስለኛል:: ሁለተኛ ክፍል እየተማርኩ የጠዋት ፈረቃ ተማሪ ነበርኩ:: ወደ ሁለት ሔክታር የስንዴ ማሳ አዝመራችንን ወፎች እምሽክ አድርገው በሉት:: ከላዩ ላይ አንድ ኪሎ እንኳ ማንሳት አልተቻለም:: እናቴ ይዛኝ እርሳው ሔዳ ‹‹ይህንን አዝመራ ወፍ በልቶብናል:: አንተ ትምህርት ቤት ባትሔድ ትጠብቀው ነበር:: አሁን ግን ተበልቶ አልቋል፤ ስለዚህ ከሁለቱም ያጣን እንዳንሆን በትምህርትህ መጠንከር አለብህ::›› ማለቷ ለእኔ ትልቅ የመነሻ ምክንያት ሆኖኛል የሚል ግምት አለኝ::

በተጨማሪ እድሜ እየጨመረ 8ኛ ክፍል አካባቢ ስደርስ ዩኒቨርሲቲ እየገቡ ለእረፍት የሚመጡ ወጣቶችን ማየት ስጀምር፤ የትምህርት ጥቅም ገባኝ:: ከፍ ማለት እንደሚቻል ሳውቅ በደንብ ማጥናት ጀመርኩ:: 8ኛ ክፍል 100 ፐርሰንት በማምጣቴ አስተማሪዎቼ እጅግ ተደሰቱ:: ያ የበለጠ አነቃቃኝ፤ የ12ኛ ክፍልን ብሔራዊ የማጠቃለያ ፈተና ስወስድ የጊዜውን ጥሩ ውጤት 3 ነጥብ 4 አምጥቻለሁ:: የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪ ነበርኩ:: ዩኒቨርሲቲ ልገባ ስል ቀደም ሲል መንግስት ሥራ ይመድብበት የነበረበት መንገድ ቀርቶ ከአሁን በኋላ ከመምህርነት ውጪ ተመራቂው ራሱ ሥራ ፈልጎ መግባት አለበት የሚል ወሬ መወራት ጀመረ:: ስለዚህ ኮተቤ መምህራን ኮሌጅን አንደኛ ምርጫዬ አድርጌ ሞልቼ እዛ ገባሁ::

በባህሪዬ ምንም ነገር አያታልለኝም:: በአብዛኛው ጊዜዬን የማጠፋው በማንበብ ነበር:: ስለዚህ ኮተቤ በጣም ጥሩ ውጤት በማምጣቴ በ1989 ዓ.ም ዲግሬዬን የወርቅ ተሸላሚ ሆኜ አጠናቀቅኩ:: ትምህርቴ በጂኦግራፊ እና አካባቢ ጥናት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፤ ወዲያው ጅማ መምህራን ኮሌጅ ማስታወቂያ ሲያወጣ ተወዳድሬ ከብዙ አመልካቾች መካከል አልፌ በረዳት ሌክቸረርነት ተቀጠርኩ::

በ1992 ዓ.ም እና በ1993 ዓ.ም ሁለተኛ ዲግሪ ለመማር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጂኦግራፊ እና በአካባቢ ጥናት ት/ት ክፍል አጠናቀቅኩ:: በመመረቂያ ፅሁፍ ካገኘሁት የA+ ውጤት በተጨማሪ አጠቃላይ ውጤቴ እጅግ በጣም ምርጥ የሚባል ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- መጀመሪያ ጂኦግራፊ በድጋሚ ጂኦግራፊ በአጠቃላይ የመልከአ ምድር ጉዳይ ላይ ያተኮሩበት ጉዳይ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር መሳይ፡-** በአጋጣሚ ነው:: ምክንያቱም ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ስገባ የነበሩት የትምህርት ክፍሎች አማርኛ፣ ሒሳብ፣ እንግሊዘኛ፣ ስፖርት ሳይንስ፣ ታሪክ እና ጂኦግራፊ ብቻ ነበሩ:: ለእኔ የተሻለ ይሆናል ብዬ የገመትኩት ጂኦግራፊ ነው:: ሌሎች እንደ ኢኮኖሚክስ ያሉ የት/ት ክፍሎች ቢኖሩ ኖሮ ምናልባት ወደ ሌሎች እሳብ ነበር:: በእርግጥ ገጠር በማደጌ የመሬት አቀማመጥ ያስደስተኛል:: ምናልባት ያ ትንሽ ስቦኛል ብዬ እገምታለሁ:: ዋናው ጉዳይ ግን አማርኛ እንዳልማር አፌን የፈታሁት በአፋን ኦሮሞ በመሆኑ ትንሽ ያስቸግረኝ ነበር:: እንግሊዘኛም ያው ገጠር አድጌ ከከተማ ልጆች ጋር መወዳደር ይከብደኛል ብዬ አሰብኩና ተውኩት:: በምንም መልኩ የተሻለ የሚሆነው ጂኦግራፊ ነበር ብዬ አሰብኩና ገባሁ:: በዚህም አልከፋኝም:: ምክንያቱም በጥሩ መምህራን በጥሩ ሁኔታ መማር ብቻ ሳይሆን መድረስ የምፈልገው ቦታ ሁሉ ደርሻለሁ::

የሁለተኛ ድግሪዬን ከጨረስኩ በኋላ ወደ ጅማ አልተመለስኩም:: የግል ተቋማት ጋር አዲስ አበባ ውስጥ መስራት ጀመርኩ:: ነገር ግን ብዙም ሳልቆይ መልሼ ወደ ዩኒቨርሲቲ መምህርነት መመለስ ፈለግኩ:: ስለዚህ አዳማ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ተወዳድሬ ተቀጠርኩ:: በዛ ጊዜ ዩኒቨርሲቲው እንደ አሁኑ ኢንጂነሪንግ እና ቴክኖሎጂ ብቻ አልነበረም:: የማህበረሰብ (ሶሻል) ሳይንስ ትምህርቶች ነበሩት:: ለአንድ ዓመት ካስተማርኩ በኋላ የ3ኛ ዲግሪ የ(ፒ ኤች ዲ) ዕድል መጣ:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጆኢግራፊ እና ጥናት ትምህርት ክፍል ሶሽዮ-ኢኮኖሚ ዴቨሎፕመንት ፕላንግ (specialization in Socioeconomic Development Planning) ተማርኩ::

የማስትሬትና የዶክትሬት ዲግሪ የመመረቂያ ፅሁፌን የሰራሁት የምግብ ዋስትና ላይ አተኩሬ ነው:: በተጨማሪ የአካባቢ ሳይንስ ላይ በማተኮር አ/አ/ዩ ሳይንስ ፋኩሊቲ ተጨማሪ ሁለተኛ ዲግሪ ኮርሶችን ወስጃለሁ:: እንዲሁ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች እየሠራሁ ከ10 ዓመት በፊት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአገር ልማት ኮሌጅ በእኔ ሙያ የሰው ኃይል ይፈልጉ ስለነበር፤ በተባባሪ ፕሮፌሰርነት ተቀጠርኩኝ::

አሁን በተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ አስተምራለሁ፣ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን አማክራለሁ፣ የምርምር ሥራን እሠራለሁ:: እነዚህም በሀገር ልማት ኮሌጅ ሁለት ፕሮግራሞች (ማለትም የምግብ ዋስትና ጥናት እና የአደጋ ስጋት ፕሮግራሞች) እና በሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ውስጥ ኮርስ አስተምራለሁ፣ ተማሪዎችን አማክራለሁ:: የአደጋ ስጋት ፕሮግራም ላይ ፕሮግራሙን ከመቅረፅ ጀምሮ፣ ከማስተማር እንዲሁም ከመመራመር ጀምሮ ተማሪዎችን በማማከር ላይ እሠራለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- ከኢትዮጵያ ውጭ የት ሀገር ተማሩ ወይንም ሠሩ?**

**ዶ/ር መሣይ፡-** አዎ! ውጪ ሀገር ከትምህርት፣ ሥልጠና እና ምርምር ጋር በተያያዘ የተለያዩ አገራት ሄጃለሁ:: በውጪው ዓለም እንደተማሪ፣ እንደ አስተማሪም ሆነ እንደ ተመራማሪ ሠርቻለሁ:: ለምሳሌ ደቡብ አፍሪካ ጁሁዋንስበርግ ዩኒቨርሲቲ በተደጋጋሚ ተመላልሼ ሰርቻለሁ:: ኬኒያ ሞህ ዩኒቨርሲቲም እንደ ተመላላሽ ምሁር (Visiting Scholar) አገልግያለሁ:: ደቡብ ኮሪያ፣ ቻይና፣ ኡጋንዳ፣ ሱዳን እና ሌሎች ሀገሮች ከማስተማርና ከምርምር ጋር በተያያዘ የተጋበዝኩባቸው ቦታዎች ናቸው:: የእኛ አገር ብቻ ሳይሆን የሌሎች አገሮችንም የትምህርት እንቅስቃሴ እና የማህበረሰቡን እንቅስቃሴ ማየት አስፈላጊ በመሆኑ፤ የተለያዩ አካባቢዎች ከማስተማር በተጨማሪ የምርምር ፅሁፎችን ማቅረብ አስፈላጊ ነው:: በዑጋንዳ እና በኬኒያ ጉዳዮች ላይ አርቲክሎችን አሳትሜያለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- የአደጋ ስጋት ፕሮግራምን በት/ት ክፍላችው እንዴት ተቀረፀ?**

**ዶ/ር መሳይ፡-** የአደጋ ስጋት ፕሮግራም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊትም በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ነበር:: ለምሳሌ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲን እና ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲን እንዲሁም ሰመራ ዩኒቨርሲቲን መጥቀስ ይቻላል:: አዳማም እያለሁ ከዚህ ጋር ተቀራራቢ የሆነ ትምህርት አስተምር ነበር:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስመጣ እኔ ያለሁበት ኮሌጅ በፍላጎቱ የአደጋ ስጋት ፕሮግራም እንዲቀረፅ ሃሳብ አቀረበ:: በአጋጣሚ እኔ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ከዚሁ ጉዳይ ጋር የተያያዘ የማስተማር ሥራ እሰራ ስለነበር የፕሮግራሙ ቀረፃ ሲከናወን የኮሚቴው አባል ሆንኩኝ:: አንዱ ፕሮግራም ላይ ሰብሳቢም ነበርኩ:: ከተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ ተደርጎልን ፕሮግራሙን ቀረፅን:: አሁን በእዚሁ ዘርፍ የሶስተኛ ዲግሪያቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች ሁለተኛ ዓመት ላይ ደርሰዋል::

የሁለተኛ ዲግሪ ላይ ደግሞ ፕሮግራሙ ተቀርፆ አልቆ ለሚመለከተው አካል ካስገባን በኋላ፤ እየተጠባበቅን ነው:: እንደሚታወቀው አሁን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ ሆኗል:: ትንሽ ከእርሱ ጋር በተያያዘ አንዳንድ የምናስተካክላቸው ነገሮች ይኖራሉ እንጂ ፕሮግራሞቹ ይኖራሉ::

**አዲስ ዘመን፡-የአደጋ ስጋት ዙሪያ ከማስተማር ባሻገር ምን ሠራችሁ?**

**ዶ/ር መሳይ፡-** በተለይ የራሴን ሥራ ስገልፅ፤ ከላይ እንደገለፅኩት መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የምርምር ሥራዎችን አከናውኛለሁ:: በአደጋ ስጋት ላይ ብቻ ሳይሆን፤ በምግብ ዋስትና እና በአገር ልማት ዙሪያ ሰፊ ጥናት እድርጌያለሁ:: ተማሪዎቻችንም ትኩረታቸው በእነዚሁ ጉዳይ ላይ ሲሆን፤ በተለይ እኔ የማማክራቸው ተማሪዎች በአገር ልማት፣ በአደጋ ስጋት በምግብ ዋስትና እና በማህበራዊ ሳይንስ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሠሩ ናቸው::

**አዲስ ዘመን፡-የትምህርት ክፍሉ መከፈቱ ምን ጥቅም አስገኘ ?**

**ዶ/ር መሳይ፡-** ብዙ ጥቅም ያስገኛል:: እኛ ኢትዮጵያውያን ምስራቅ አፍሪካ ውስጥ በመኖራችን

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹አደጋን እየተከላከልን ማልማት፤. . .

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

ከአቀማመጣችን አንፃር በርከት ያሉ የአደጋ ስጋቶች የሚያንዣብቡብን ነን:: ስለዚህ በአደጋ ስጋት ዙሪያ በ2ኛ እና በ3ኛ ዲግሪ ደረጃ ማስተማሩ ሀገርን ከአደጋ ሥጋት ለመታደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው:: እንደውም ሊያጋጥም ከሚችለው እና ካለው ችግር አንፃር ከዚህ በፊትም በሰፊው መሠራት ነበረበት የሚል እምነት አለኝ::

ምስራቅ አፍሪካ የተለያዩ ችግሮች ያሉበት ቀጠና ነው:: ከተፈጥሮ ብንጀምር ከመካከለኛው ምስራቅ ተነስቶ እስከ ሞዛምቢክ የተዘረጋው ትልቁ ስምጥ ሸለቆ አንዱ አሳሳቢ ቦታ ነው:: እንደ አዳማ እና አርባምንጭ ያሉ አንዳንድ ትልልቅ ከተሞቻችንም እዚህ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ ይገኛሉ :: ይህ ስምጥ ሸለቆ የመሬት መንቀጥቀጥ ችግር የሚያሰጋበት አካባቢ ነው:: ሁለተኛው ይህ አካባቢ ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ በተደጋጋሚ በድርቅ የሚጎዳ ነው:: ከዚህም አንፃር ድርቅ ሲከሰት መጠነ ሰፊ ጉዳት ያመጣል:: በሕዝብ ላይ፣ በእንስሳት እና በአጠቃላይ በአካባቢ እንዲሁም በተፈጥሮ ሃብት ላይ ችግር ስለሚያስከትል በአደጋ ስጋት ጉዳይ ላይ የሚመራመሩ ምሁራንን በጥራት ማፍራትአስፈላጊው ነው::

ሌላው እንደሚታወቀው አካባቢው በግጭት የሚታወቅ ነው:: ሶማሊያ፣ ሱዳን እና ሌሎቹም አገሮች የእርስ በእርስ ግጭት ያለባቸው እና አካባቢውም ባለመረጋጋት የሚታወቅ ነው:: በተጨማሪ በድርቁ እና በግጭቱ እንዲሁም በተለያዩ ውጫዊ ምክንያቶች የአካባቢው ኢኮኖሚም ብዙም የተረጋጋ አይደለም:: የሶማሊያም፣ የጅቡቲም፣ የኤርትራም የሌሎቹም ኢኮኖሚ የተረጋጋ አይደለም:: ስለዚህ ይህንን መረዳት፣ ተፅዕኖ መፍጠር፣ መገምገም እና መከታተል የሚችል ባለሞያ ያስፈልጋል:: እነዚህ ጉዳዮች ፕሮግራሙን በጣም አስፈላጊ ያደርጉታል::

**አዲስ ዘመን፡- አደጋዎችን ቀድሞ መከላከል ይቻላል?**

**ዶ/ር መሳይ፡-** ቀድሞ መከላከል የሚቻልበትም የማይቻልበትም ሁኔታ አለ:: ለምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥን ቀድሞ በትክክል መተንበይ አስቸጋሪ ነው:: በተቃራኒ ግን የግጭት አደጋንን መተንበይና መከላከል ይቻላል:: ድርቅንም ለመከላከል አሁን እየተደረገ እንዳለው አይነት የአረንጓዴ አሻራ ኢንሼቲቭን በማስፋት መከላከል ይቻላል:: ተፅዕኖውንም መቀነስ ይቻላል:: ለእንደዚህ ዓይነት ቀድሞ መከላከል ለሚቻሉ አደጋዎች ደግሞ የሰለጠነ የሰው ኃይል በጣም አስፈላጊ ነው::

**አዲስ ዘመን፡-የአደጋ ስጋት ዙሪያ ከሚደርጉት ጥናት አኳያ ዓለም አደጋን እየተከላከለ ያለው በምን ያህል መጠን ነው? ኢትዮጵያስ በምን ደረጃ ላይ ናት?**

**ዶ/ር መሳይ፡-** መጀመሪያ በዓለም ደረጃ ያለውን እንመልከት:: ዓለምን የአደጋ ስጋትን ከመቀነስ አንፃር በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል:: አንደኛው የሳይንስ ግኝቶችን በመጠቀም የተፈጥሮ አደጋዎችን ከሞላ ጎደል መተንበይ እና መቆጣጠር እየቻለ ነው:: ለምሳሌ የጎርፍ አደጋ ወይም የድርቅ አደጋን መተንበይና ጉዳቱን መቀነስ ይቻላል:: በሰው ልጅ ሕይወት ላይ የከፋ አደጋ እንዳያስከትሉ ማድረግ ይቻላል:: በአደጋው ልክ ጉዳት እንዳይደርስ ማድረግ ይቻላል:: አንዳንድ የተፈጥሮ አደጋዎች ግን አውዳሚነታቸው ቀጥለዋል:: ለምሳሌ በቅርብ ጊዜ በቱርክ እና አካባቢው የተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ በጣም አውዳሚ ነበር:: ሰሜን አፍሪካ የተከሰተውን የተራራ መንቀጥቀጥና መደርመስ አደጋንም ማንሳት ይቻላል:: እነዚህ አልፎ አልፎ የሚከሰቱት አውዳሚ አደጋዎችን አስቀድሞ መተንበይ ከባድ ነዉ::

አሁን ዓለም መከላከል ያቃተው ሰው ሰራሽ አደጋውን ነው:: ማለትም ሰው ሰራሽ አደጋ ከሌላው ጊዜ በላይ እየከፋ መጥቷል:: ስጋቱም ቀላል አይደለም:: ለምሳሌ በራሺያ እና ዩክሬን መካከል እየተካሔደ ያለው ጦርነት ሰው ሰራሽ አደጋ ነው:: አስቀድሞ መከላከል ይቻል ነበር:: ነገር ግን አስቀድመው አልተከላከሉም:: ይኸው እስከዛሬ ድረስ የሰው ሕይወት እየቀሰፈ እና የዓለም ኢኮኖሚን እያናጋ የእነርሱንም ኢኮኖሚ እየበላ ነው:: በእስራኤል እና በፍልስጤም መካከል እየተደረገ ያለው ግጭትም በተመሳሳይ መልኩ በርካታ ወራትን አስቆጥሯል:: ወደ 35ሺህ ሰው አልቋል:: ይህንንም አስቀድሞ መከላከል ይቻል ነበር:: ነገር ግን መከላከል አልተቻለም:: ሌሎች በርካታ ቦታዎች ላይ አሁንም የቀጠሉ ጦርነቶች/ግጥቶች አሉ::



**ለገበሬው ችግሮቹን በተገቢዉ ሁኔታ አላቃለልንለትም:: ገበሬው ዛሬም ድረስ ከሺህ ዓመታት በፊት በተፈጠረ በሞፈር እና ቀንበር እያረሰ ነው**

ጎረቤታችን ሱዳን ውስጥ የእርስ በእርስ ግጭት የከፋ ደረጃ ላይ ይገኛል፡:: ሶማሊያ ሀገር ውስጥም ችግር አለ:: ታይዋን አካባቢ ያለው ሁኔታ አስጊ ነው:: በዚህ አካባቢ ምናልባት የአሜሪካ እና የቻይና ጉዳይ በጣም ያሳስባል:: ሰሜን እና ደቡብ ኮሪያ መካከል ያለውም ሁኔታ ተጨማሪ ሥጋት ነው፣ መርገብ አልቻለም:: ኒኩሌር የታጠቁ እነ ራሺያ እና ሰሜን ኮሪያ ከተፈጥሮ አደጋ በላይ ስጋት ሆነዋል:: ዓለም ወይም ፖለቲከኞቻችን እነዚህን ሰው ሰራሽ አደጋዎችን በተገቢው ሁኔታ እየተከላከሉ ወይንም በድርድር እየፈቱ አይደለም::

ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ድርቅ ካደረሰው ጉዳት በላይ አስቀድመን ልንከላከላቸው የምንችላቸው ሰው ሰራሽ ችግሮቻችን የከፋ ችግር ውስጥ ጥለውን አልፈዋል:: ለምሳሌ ቀርበን መነጋገር ባለመቻላችን የአንድ ሀገር ልጆች ተከፋፍለን እየተገዳደልን ኖረናል:: መከላከል አይቻልም ወይ? ከተባለ መከላከል ይቻል ነበር:: አንዱ ወገን ለዘብ ብሎ ቀርቦ ቢነጋገር መፍታት እና መከላከል ይቻል ነበር:: በሰው ሰራሽ ግጭቶች ምክንያት ኢኮኖሚያችን ምን ያህል እየተጎዳ እንደኖረ ይታወቃል:: እንዲህ ዓይነቶቹ በአጠቃላይ በዓለም ያለው በደንብ ሲታዩ ከተፈጥሮ ይልቅ ሰው ሰራሽ አደጋዎች እየጎዱን ነው::

ልማትን በዘላቂነት ለማምጣት አደጋን መከላከል የግድ ነው:: አደጋን ሳንከላከል እና ሳንቆጣጠር ወደ ልማት ብቻ ካተኮርን ልማቱ ይወድማል፤ የሰው ልጅ አውዳሚ እንስሳ ነው:: በብዙ ዓመት የለማ ሃብት፤ በሰው ልጅ በጥቂት ቀናት ይጠፋል:: ስለዚህ አደጋ መከላከል ከልማት ጋር የተገናኘ ነው:: አደጋን መከላከል ብቻውን አይበቃም:: ልማትም ብቻውን አይበቃም:: አደጋን እየተከላከልን ማልማት፤ እያለማን አደጋን መከላከል የግድ ነው:: አደጋ መከላከል ሲባል ደግሞ ሰው ሰራሹን ወይም የተፈጥሮውን ብቻ ሳይሆን ሁለቱም ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል::

**አዲስ ዘመን፡- በተፈጥሮ ሃብት እና አጠቃቀም ዙሪያ ጥናቶችን አጥንተዋል:: ጥናቶት ላይ በመመርኮዝ ስለኢትዮጵያ ተፈጥሮ ሃብት እና አጠቃቀም ዙሪያ ምን ይላሉ?**

**ዶ/ር መሳይ፡-** ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ ከሃምሳ እና ከስድሳ በመቶ በላይ በደን የተሸፈነች መሆኗን ጥናቶች ያመለክታሉ:: ነገር ግን በተለይ ከ1950ዎቹ እና ከ1960ዎቹ ጀምሮ ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት አልተሰጠም:: ትኩረታችን ሌላ ነበር:: በደርግ ጊዜ ጦርነት ነበር:: ከዛ በኋላም ቢሆን ትኩረት ስላልተሰጠው ደኑ ተመናምኖ ራቁታቸውን ከሆኑ አገራት ተርታ ለመሰለፍ ጥቂት ቀርቶን ነበር::

ኢትዮጵያ በውሃ ሃብት የተሻለች ነበረች:: ሃይቆች አሉን፤ አንዳንዶቹ መጠናቸው በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል:: ለምሳሌ አቢጃታ ሃይቅ በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል:: ሐረማያ ሃይቅ ጠፍቶ ነበር፤ አሁን ትንሽ እያገገመ ነው:: ሌሎች ደግሞ ብዙም የማይታወቁ ትንንሽ ሃይቆች፣ ወንዞች፣ ምንጮች ደርቀዋል:: ከገጠር ወጥቼ ተመርቄ አንድ ወቅት ወደ ተወለድኩበት አካባቢ ከአምስት ዓመት በኋላ ስሔድ ለመፋቂያ እንኳ የሚሆን እንጨት አልነበረም:: አሁን በቅርቡ ከአረንጓዴ ልማት ጋር ተያይዞ የሚሠራው ኢንሼቲቭ ጥሩ ውጤት እያስገኘ ነው:: አሁን ደኑ እየተመለሰ፣ የውሃ ሃብቶችም እያገገሙ ነው::

የጂኦግራፊክ ኢንፎርሜሽን ሲስተም (GIS/RS) ቴክኖሎጂን በመጠቀም በምናደርጋቸው ጥናቶች የመሬት አጠቃቀም እና የመሬት ሽፋን በምን ያህል መጠን እየጨመረ እንደሚገኝ ማወቅ ይቻላል:: የአረንጓዴ አሻራ ኢንሸቲቭ በእውነት ለመናገር ያመጣው ለውጥ በቀላሉ የሚገለፅ አይደለም:: ሰዎች ዛፍ እንዲተክሉ እና እንዲንከባከቡ እያነሳሳ ይገኛል:: ዛፍ ለቤት መስሪያ ብቻ ሳይሆን አየር ሙቀትን እንደሚቆጣጠር፣ የውሃ አካላትን እንደሚያጎለብት ሁሉም እየተረዳ መጥቷል:: ስለዚህ የችግኝ የተከላ እንቅስቃሴው ሰፍቷል:: ይህ እንቅስቃሴ እስከ ግለሰብ ድረስ ወርዶ ከተሰራበት ከ100 ዓመት በፊት ወደ ነበርንበት ቦታ መመለስ ይቻላል:: በደን ሽፋን እና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብት ፣ በአፈር እና ውሃ ሃብት ወደ ነበርንበት መመለስ እንችላለን::

**አዲስ ዘመን፡- እርሶ የገበሬ ልጅ ነዎት:: መነሻዎ ገጠር ነው:: ጂኦግራፊ ተምረዋል:: እርሶ ብቻ ሳይሆኑ ብዙዎች ተምረዋል:: ነገር ግን በሌላ በኩል ምሁራን ለገጠሩ ሕዝብ በተለይ ለአርሶ አደሩ ምን አደረጉ ይላሉ? ምን ማድረግስ ነበረባቸው?**

**ዶ/ር መሣይ፡-** እኔን ጨምሮ ሌሎች የተማሩ ሰዎች ታች ወርደን ከገበሬው ከገበሬዉ በመሥራት ላይ ችግር ያለ ይመስለኛል:: ለገበሬው ችግሮቹን በተገቢዉ ሁኔታ አላቃለልንለትም:: ገበሬው ዛሬም ድረስ ከሺህ ዓመታት በፊት በተፈጠረ በሞፈር እና ቀንበር እያረሰ ነው:: ምርታማነቱ ዛሬም ዝቅተኛ ነው:: አሁንም በተለያዩ እጥረቶች እና ፈተናዎች ውስጥ ይገኛል:: የግብዓት አቅርቦት እጥረቱ ቀላል አይደለም:: ከዓመት ዓመት ከጎተራው የሚበላ የገበሬ ቤተሰብ ጥቂት ነው:: በአካባቢ ጥበቃ፣ በግብርና እና ሌሎችም ከገበሬው ጋር ቀጥታ በሚገናኙ ዘርፎች ላይ ሶስተኛ ዲግሪ ይዘን ዶክተር የተሰኘን ብዙ ነን:: ነገር ግን እንደ ብዛታችን ገበሬውን አልጠቀምነውም:: ለወደፊቱ ብዙ መሥራት ያለብን ይመስለኛል::

ሆኖም ምንም አላደረግንም ማለት አይደለም:: ቢያንስ ገጠር ያለው ሰው የተሻለ ንፁህ ውሃ ማግኘት እንዲችል በተወሰነ ደረጃ ረድተነዋል:: በአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ ላይም ጥሩ ግንዛቤ ተፈጥሯል:: ማዳበሪያ ኬሚካል ቢሆንም ይቀርባል፤ ፀረ-ዓረም ፀረ-ተባይ ይቀርብለታል:: ምን ያህል ጠቀመ የሚለው እንዳለ ሆኖ ማለት ነው:: የምሁራን እና የመንግስት ድጋፍ ባይኖር ኖሮ፤ ገበሬው ከዚህም በከፋ ችግር ውስጥ ሊኖር እንደሚችል አያጠራጥርም:: ማድረግ የምንችለውን ያህል አድርገናል ወይ የሚለው ግን ያጠያይቃል::

**አዲስ ዘመን፡- ለእዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር መሣይ፡-** ሌሎች ምክንያቶች እንዳሉ ሆኖ የት/ት ሥርአት ላይ የተሻለ ሥራ መሠራት ያለበት ይመስለኛል:: የትምህርት ሥርአታችን የአገራችንን ችግር ለይቶ የሚሳይ እና ችግር እንድንፈታ የሚያስችለን መሆን አለበት:: ተመልሰን ሕዝባችንን እንድናገለግል፣ እንድናከብር እና እንድናግዝ መሆን አለበት:: ካሪኩለሙን ከእኛ አገር ችግር ፈቺነት አንፃር ማስተካከል ያስፈልጋል:: የኛን ባህል፣ ታሪክ እና ችግርን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት:: ይህ ማለት ጭራሽ የትኛውንም ሀገር ተሞክሮ አንውሰድ ማለት አይደለም::

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ዓለም አይተዋል:: ምን ማድረግ አለብን ይላሉ?**

**ዶ/ር መሣይ፡-** በጣም የምቀናው እና ወደ እኛ አገር መምጣት አለበት የምለው የተሻለ የሥራ ባህል ነው:: ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብት የታደለች ናት:: ነገር ግን የሥራ ባህል ላይ ትልቅ ክፍተት ያለ ይመስለኛል:: ያንን ማስተካከል ያስፈልጋል:: በጣም ታታሪ መሆን አለብን:: ሕጋዊ እና ሥነ-ምግባራዊ ባልሆነ አ ቋ ራ ጭ መንገድ ሃብት ለማጋበስ መሞከርን መተው መቻል አለብንም:: በሥራ የሚያምን (meritorious) ሕዝብ ለመፍጠር መጣር ያስፈልጋል:: የሥራ ባህላችን እና የትምህርት ሥርዓታችን ላይ በጥሩ ሁኔታ ከሠራን ሌላው ከባድ አይደለም::

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ሥም እጅግ አመሰግናለሁ::**

**ዶ/ር መሣይ፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

# ማህደረ ጤና

## የነብስ አድን ክትባት ዘመቻ

**አስናቀ ፀጋዬ**

አንዳንድ ጊዜ በሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የጤና አገልግሎቶች ሊቋረጡ ይችላሉ:: ይህንኑ ተከትሎ በተለይ ሴቶችና ህፃናት ተጎጂ ይሆናሉ:: በኢትዮጵያ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ምክንያት በርካታ የጤና ተቋማት ወድመዋል:: በዚህም በርካቶች ከጤና አገልግሎት ውጪ ሆነዋል:: በተመሳሳይ በሀገሪቱ በኦሮሚያና አማራ ክልል በሚገኙ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ድርቅ በመከሰቱ ብዙዎች ከቀያቸው ተፈናቅለው ከጤና አገልግሎቶች ለመራቅ ተገደዋል:: በጦርነቱና በድርቅ ምክንያት ህፃናት ቀደም ሲል የጀመሩትን ክትባት አቋርጠዋል:: ሌሎቹ ደግሞ በጭራሽ ክትባት አልጀመሩም:: በዚህ መነሻነት ነው እንግዲህ ክትባት ጀምረው ያቋረጡና ያልጀመሩ ህፃናትን እንዲከተቡ ጤና ሚኒስቴር በዚህ ሳምንት መጨረሻ የክትባት ዘመቻ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያስጀመረው::

የጤና ሚንስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ እንደሚናገሩት፤ በጤና ፖሊሲ ውስጥ ከፖሊሲ የሚመነጩ የተለያዩ ስትራቴጂዎች አሉ:: ከነዚህ ውስጥ የአምስትና የሶስት አመት እቅድ ውስጥ የቅድሚያ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው የጤና አገልግሎቶች ውስጥ የእናቶችና የህፃናት ጤና አንዱ መሆኑ ይታወቃል:: ባለፉት አመታት መንግሥት፣ አጋር ድርጅቶችና ማህበረሰቡ በጋራ በሰሩት ስራ የእናቶችና የህፃናትን ሞት ለመቀነስ ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል:: ኢትዮጵያም በተለይ የእናቶችና ህፃናትን ሞትና ህመም በመቀነስ ጥሩ ስም ያላት ሀገር ለመሆን በቅታለች::

የክትባት አገልግሎት ደግሞ የህፃናትን ሞት ለመቀነስ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው:: በኢትዮጵያ ባለፉት አራት አስርት አመታት የክትባት መርሃ ግብር በርካታ ህፃናትን ተጠቃሚ አድርጓል:: በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህፃናትን ከሞት ታድጓል:: ዘርፉን የሚያጠኑ ተመራማሪዎች እንደሚሉት በክትባት ላይ የሚደረገው የአንድ ዶላር ኢንቨስትመንት ምላሹ ከሀምሳ ዶላር በላይ ነው:: ይህም ክትባት ምን ያህል ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ያመለክታል:: ክትባት የጤና ጥቅም ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በተለያዩ የልማት ዘርፎች ላይ አስተዋፅኦ የጎላ መሆኑ ይነገራል::

ኢትዮጵያ ከአርባ አመት በፊት ከስደስት በማይበልጡ የክትባት አይነቶች የጀመረችው ክትባት በአሁኑ ውቅት ከአስራ አራት በላይ የሚሆኑ የክትባት አይነቶች ለህፃናት፣ ለልጃገረዶችና ለአዋቂዎች እየጠሰጡ ይገኛሉ:: እነዚህ ክትባቶች በሽታን የመከላከል ስትራቴጂን መሰረት አድርገው የሚሰራባቸው ናቸው:: ከዚህ በፊት ክትባቶች ከውጪ የሚመጡ ቢሆንም አሁን ላይ በሀገር ውስጥ ክትባት የማምረት ጅምር አለ:: ይህን በማጠናከር ኢትዮጵያ ራሷን ችላ በሀገር ውስጥ ክትባቶችን አምርታ ህፃናት በሚያስፈልገው የጥራት ልክ በክትባት ተደራሽ የሚሆኑበት ግዜም ሩቅ አይደለም::

ሚኒስትር ዲኤታው እንደሚገልፁት፤ በኢትዮጵያ በተፈጠረው ሰው ሰራሽና የጠፈጥሮ አደጋ ምንም አይነት ክትባት ያላገኙና ክትባት ጀምረው ያቋረጡ በርካታ ህፃናት አሉ:: ህፃናቱ ሀሉንም ክትባቶች ወስደው ሲያጠናቅቁ ነው ተከትበዋል ሊባሉ የሚችሉት:: እነዚህ ህፃናት በአብዛኛው የሚገኙት በግጭትና ድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች፣ ራቅ ያሉ ቦታዎችና የአርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ ሲሆን በከተሞች አካባቢዎችም ያልተከተቡ በርካታ ህፃናት እንዳሉ ጥናቶች ያሳያሉ::

ህፃናቱ ክትባት ሳያገኙ ወይም ክትባቱን ጀምረው ለማቋጣቸው በርካታ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ:: በዋናነት ግን በሀገሪቱ የነበሩ የተለያዩ ግጭቶችና የድርቅ አደጋዎች ህፃናቱ ክትባት እንዳያገኙና የጀመሩትን ክትባት እንዳያጠናቁ ምክንያት ሆነዋል:: በእያንዳዱ ክልል በሚገኙ ወረዳዎች ምን ያህል ህፃናት ክትባት እንዳላገኙና አግኝተው ያቋጡት ምን ያህል እንደሆኑ ጥናት ተሰርቷል:: እነዚህን ህፃናት በክትባት ተጠቃሚ ለማድረግ የማካካሻ ክትባት መርሃ ግብር/big catch policy/ ከሶስት ወራት በፊት ተዘጋጅቷል:: እስካሁን ድረስ በመደበኛው ክትባት ክትባት ጀምረው ያቋረጡና ያልጀመሩ ህፃናትን ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል:: በዚህም በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ህፃናት ሙሉ በሙሉ ክትባት እንዲያገኙ ተደርጓል:: በዚህ ብቻ ግን የሚያበቃ መሆኑን በማየት ለአስር ቀን የሚቆይ የክትባት ዘመቻ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማድረግ ተወስኗል:: የክትባት ዘመቻውም ካለፈው ማክሰኞ ጀምሮ በይፋ ተጀምሯል::



የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጄ ዱጉማ፣

**‹‹በተከታታይ አስር ቀናት የሚከናወነው የነብስ አድን ክትባት ዘመቻ ከፍተኛ ውጤት የሚያመጣ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናትን ተጠቃሚ የሚያደርግና የሕፃናትን ሞት በእጅጉ እንዲቀንስ የራሱን አስተዋፅኦ የሚያበረክት ነው፡››**

የክትባት ዘመቻው በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚከናወን ሲሆን ትኩረት የሚደረግባቸው የተወሱ አካባቢዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በዚህ ዘመቻ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ህፃናት ይከተባሉ:: የሚከተቡት ህፃናት እድሜያቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑና ከዚህ በፊት በተለያዩ ምክንያቶች ክትባት ያልወሰዱ ወይም ደግሞ ክትባት ጀምረው ያቋረጡ ናቸው:: በዚህ የክትባት ዘመቻ ትኩረት የሚሹና ቅድሚያ የሚሰጣቸው በተለይም በግጭትና በድርቅ ምክንያት ከቀያቸው የተፈናቀሉና ወደቀያቸው እየጠመለሱ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ::

በሌላ በኩል የተለያዩ ወረርሽኞች ያሉባቸው አካባቢዎች በክትባት ዘመቻው ቅድሚያ ይሰጣቸዋል:: ተለይ ኮሌራ፣ ኩፍኝ ወይም የወባ ወረርሽኝ ያለባቸው አካባቢዎች በክትባት ዘመቻው ቅድሚያ ይሰጣቸዋል:: በፀጥታ ችግር ምክንያት አገልግሎት ያቋረጡ ጤና ኬላዎች፣ ጤና ጣቢያዎች የነበሩበት ቦታ ላይ ቅድሚያ ይሰጣል:: ምክንያቱም የበለጠ ብዙ ህፃናት ክትባት ያለወሰዱበት ቦታ እንርሱ ስለሆኑ ለእነርሱም ተጨማሪ ቅድሚያ ይሰጣል:: ራቅ ያሉ ወረዳዎች፣ በጤና ሴክተር ዝቅተኛ አፈፃፀም ባላቸው አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተደርጓል::

ስለዚህ ከ1 ሺ በላይ የሚሆኑ ወረዳዎችን በመለየት ለየትኞቹ ቅድሚያ እንደሚሰጥ ታውቋል:: ለእያንዳንዱ ወረዳ ምን ያህል የህክምና ግብአት እንደሚደርስ ተረጋግጧል:: ለክትባት አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች ተሟልተዋል:: የጤና ባለሞያዎች ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል:: የክትባት መስጫ ተቋማትም ዝግጁ ሆነዋል::

በዘመቻው ሁሉም የጤና ባለሞያዎች ተሳታፊ ይሆናሉ:: በተለይ ከ38 ሺ በላይ የሚጠጉት የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሙሉ በሙሉ በክትባት ዘመቻው ይሳተፋሉ:: በጤና ጣቢያ ያሉትም እንዲሁ ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን ወርደው በመርዳት ሰፊ ስራ ይሰራሉ ተብሎ ይጠበቃል:: ከመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎችም ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የጤና ባለሞያዎች ወርደው ድጋፍ ያደርጋሉ:: ክትባቱንም በጤና ተቋማት ውስጥ ይሰጣሉ:: ከዛም ውጪ ያሉ ተንቀሳቃሽ ቡድኖችም ራቅ ባሉና ጤና ተቋማት በቀላሉ በማይገኙ ቦታዎች ላይ አስፈላጊውን ክትባቱን ይዘው ይቀርባሉ::

ዘመቻው ሀገር አቀፍ እንደመሆኑ በተለይ ለመግባት ቀላል ባልሆኑ አንዳንድ አካባቢዎች የሁሉም ጤና ባለሞያዎች ድጋፍ ያስፈልጋል:: በዚህ ክትባት ሙሉ በሙሉ ክትባት ያልጀመሩና ክትባት ጀምረው ያቋረጡ ህፃናት ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ ለማድረግ ይሰራል:: ከዛ በኋላ የክትባት ስረአቱን በማጠናከር ክትባት ያልወሰዱ ወይም ያልጀመሩ ህፃናት በማይኖሩበት መንገድ መስራት ያስፈልጋል::

በግጭት በተጎዱ አብዛኛዎቹ አካባቢዎች ላይ መድረስ እንደሚቻል ከክልሎች ጋር ንግግር ተደርጓል:: የተወሰኑ ቦታዎች ግን ተጨማሪ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል:: ከዚህ አንፃር ከፀጥታ አካላት፣ ከልማትና አጋር ድርጅቶች፣ በአካባቢው ካሉ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመሆንና ማህበረሰቡን በማስተባበር በእነዚህ ቦታዎች ላይ ተደራሽ ለመሆን ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ:: በተለይ ግብአት ለማድረስ ሊከብድ ስለሚችል የአለም ጤና ድርጅትን የመሰሉ አጋር ድርጅቶችን በመጠቀም በቦታዎቹ ላይ ለመግባት ጥረት ይደረጋል::

በክትባት ዘመቻው እድሚያቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑ ህፃናት ሁሉንም የክትባት አይነቶች ያገኛሉ:: ትልቅ ትኩረት የሚደረግባቸው አምስት የክትባት አይነቶች ግን አሉ:: በተለይ ፀረ አምስት/ፔንታ/፣ የሳምባ ምች፣ የኩፍኝ፣ የአንጀት ህመምና የፖሊዮ ክትባቶች በዚህ ክትባት ዘመቻ ህፃናት የሚከተቧው የክትባት አይነቶች ናቸው:: ነገር ግን ደግሞ የህፃናቱ እድሜ ታይቶ ማንኛውም የክትባት አይነት የሚሰጥበት ሁኔታ ይኖራል::

ሚንስትር ዲኤታው እንደሚሉት ይህን ክትባት ማካካሻ መርሃ ግብር ተፈፃሚ ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል:: በተለይ የጤና ባለሞያዎችና አመራሮች ለክትባት ዘመቻው እውን መሆን ኃላፊነታቸውን በከፍተኛ ደረጃ መወጣት ይጠበቅባቸዋል:: ግን ደግሞ የክትባት ዘመቻው የጤናው ዘርፍ ስራ ብቻ ባለመሆኑ በተለያዩ ዘርፎች ያሉ የመንግሥት አመራሮችም ለክትባት ዘመቻው መሳካት የራሳቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል:: ሌሎች አጋር ድርጅቶችና ማህበረሰቡም በክትባት ዘመቻው ንቁ ተሳታፊና አጋዥ መሆን አለባቸው::

በተለይ እድሜያቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑና ምንም አይነት ክትባት ያላገኙ ወይም ደግሞ ጀምረው ያቋረጡ ህፃናት ጤና ባለሞያዎች በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ለይተዋቸው ዝግጁ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: ጤና ተቋማትም ለዚህ ዝግጁ መሆን አለባቸው:: ለቀጣዮቹ ሁለት ሳምንታት የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ስራ የክትባት ዘመቻው መሆን አለበት:: ከክልሎች ጋርም በተግባቦት እየተሰራ ይገኛል:: በቀጠሮ ያሉትን ህፃናትንም ደግሞ ፈልጎ ማግኘት፤ ተፈናቃይ ከሆኑ የት እንደሄዱ፣ ወደ ቀያቸው ከተመለሱም በአግባቡ ፈልጎ ማግኘትን ጭምር የሚሰራ ሥራ ነው::

ከዚሁ የክትባት ዘመቻ ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩ ሌሎች ስራዎችም ይኖራሉ:: በተለይ የወባ ወረርሽኝ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ስለሚገኝ በክትባት ዘመቻው ቤት ለቤት ሲኬድ አብሮ የሚታይ ይሆናል:: ይህ ብቻ ሳሆን ከሥርአተ ምግብ ጋር በተያያዘ በተለይ የምግብ እጥረት ያጋጣማቸውን ህፃናት የመለየት፣ ህክምና የመስጠትና ወደ ህክምና ተቋማት መላክና ሌሎችም ተጓዳኝ ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል::

ይህ የክትባት ዘመቻ ውጤታማ እንዲሆንና ልጆች የዚህ ክትባት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ወላጆችና አሳዳጊዎችም ልጆቻቸውን ወደ ህክምና ተቋም በመውሰድ ማስከተብ ይጠበቅባቸዋል:: ነገር ግን ክትባቱ በጤና ተቋማት ብቻ የሚሰጥ ባለመሆኑ በግዚያዊነት በውሎ ገብ በተንቀሳቃሽ ቡድን በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚሰጥ በመሆኑ ወላጆች እነዚህን ሁሉ አማራጮች በመጠቀም ልጆቻቸውን ማስከተብ ይኖርባቸዋል:: በተመሳሳይ የመገናኛ ብዙሃንም ይህን የነብስ አድን ክትባት ዘመቻ አስፈላጊነት በማጉላትና ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል::

በተከታታይ አስር ቀናት የሚከናወነው የነብስ አድን ክትባት ዘመቻ ከፍተኛ ውጤት የሚያመጣ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህፃናትን ተጠቃሚ የሚያደርግና የህፃናትን ሞት በእጅጉ እንዲቀንስ የራሱን አስተዋፅኦ የሚያበረክት ነው::

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የጤና መኮንኑ አርሶ አደር

**ማህሌት አብዱል**

ወጣት አዳነ ሹሜ ትውልዱም ሆነ እድገቱ በጉራጌ ዞን እንድብር ከተማ ልዩ ስሙ የሰሚ በተባለ ቦታ ነው። ከልጅነቱ ጀምሮ የጤና ባለሙያ የመሆን ህልም ነበረው፤ ይህን የተረዱት ወላጆቹም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ወደ አዲስ አበባ ልከውት በግል የጤና ኮሌጅ በጤና መኮንንነት አስተማሩት።

ትምህርቱን እንዳጠናቀቀም አዲስ አበባ ከተማ በሚገኝ የግል ክሊኒክ ተቀጥሮ ለሁለት ዓመታት አገለገለ። ይሁንና የሚከፈለው ደመወዝ እዚህ ግባ የማይባልና ለከተማ ኑሮ የማይበቃ በመሆኑ ሥራውን ለቆ ወደ ትውልድ ቀዬው መመለሱን ወጣት አዳነ ያስረዳል። ‹‹በወቅቱ ይከፈለኝ የነበረው ደመወዝ አይደለም ለቤት ኪራይ ለቀለቤም አይበቃም ነበር›› ሲል ይገልፃል።

እንድብር ከተማ ላይ ከአክስቱ ጋር በመተባበር የራሳቸውን ጤና ጣቢያ በጋራ ይከፍታሉ፤ እሱም በሙያው መስራቱን ይቀጥላል። ይሁንና ይህም ስራ እንዳሰበው አዋጭ ሆኖ አላገኘውም።

አሁንም ሥራውን ለቆ አዋጭ ይሆናል ባለው ንግድ ላይ ተሰማራ። ንግዱም ቢሆን አልሳካልህ አለው። ‹‹ከመንግሥት 30 ሺህ ብር ተበድሬ ልብስ ንግድ ብጀምርም ከማገኘው በላይ ወጪዬ በዛ፤ ስለሆነም ከአራት ዓመታት በኋላ ከስሬ ሱቁን ዘጋሁት›› ሲል ይገልፃል።

ወጣቱ የጤና መኮንን ድህነትን ለማሸነፍና በሁለት እግሩ ለመቆም በጣረ ቁጥር ፈተናዎች ቢበዙበትም እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም፤ አዕምሮውም ሌላ አማራጭ ከማሰብ አልቦዘነም። ይህንን የባለቤቱን ኪሳራ ያየችው የህይወት አጋሩ ግን የመንግሥት ስራ ተቀጥሮ እንዲሰራ ወተወተችው፤ እሱ ግን አሻፈረኝ አለ፤ ላጋጠሙት ችግሮችም እጅ ሳይሰጥ ሌሎች የስራ ዘርፎችን መቃኘት ያዘ።

ብዙ አውጥቶ ካወረደ በኋላ ያለጥቅም የኖረውን የወላጆቹን መሬት አሰበ፤ መሬቱን በማልማት ጥቅም ላይ ሊያውል የሚችልበትን ሁኔታ አውጠነጠነ፤ የተሻለ ገቢ እንደሚያስገኝለትም አለመ። አልሞ ብቻም አልቀረም፤ ውጥኑን መሬት ላይ አወረደ።

ሰርቶ የመለወጥ ተስፋው ዳግሞ እንዲያንሰራራ ያደረገው ደግሞ በሌማት ቱሩፋት ህይወታቸው ተቀይሮ የተመለከታቸው ሰዎች እንደሆኑ ይናገራል። ‹‹በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትራችን በደቡብ ክልል የሌማት ቱሩፋት አማካኝነት የተሰራውን ስራ በቴሌቪዥን ሲገልፁ ካያሁኝ በኋላ በግብርና ስራ ላይ ለመሰማራት ልቤ ተነሳሳ›› ሲል ይገልፃል።


‹‹ከሁለት ሄክታር በላይ በሚሆነውና ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር በቆየው በቤተሰቦቼ መሬት ላይ ባህር ዛፍ ብቻ ይለማ ነበር፤ ከዚህም በየስምንት ዓመቱ ተጠብቆ እስከ መቶ ሺ ብር ብቻ ይገኝ ነበር፤ ግን የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርገን ምርት ማምረት አለብኝ ብዬ ወሰንኩኝ›› ሲል ያስረዳል።

በዚህ መሰረት እድሜ ጠገቡንና ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር የቆየውን የባህር ዛፍ ጫካ ሙሉ ለሙሉ መነጠረና በምትኩ ሙዝ፣ አቦካዶ፣ አፐልና ዝንጅብል ለመትከል ተዘጋጀ። ይሁንና ዛፉ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ እንደመሆኑ ጉቶውን ነቅሎ ማውጣት ብዙ ገንዘብ፤ ጊዜና ጉልበት እንደጠየቀው ይናገራል።

ጉቶውን ማስወገድ ብዙ ቢያደክመውም ጥቅምም እንደሚያገኝበትም አሰበ። ከጉቶው ከሰል አውጥቶ በመሸጥ ወጪውን ለመተካት ጥረት አደረገ። በሌላ በኩል መሬቱ አሲዳማ እና ገደላማ በመሆኑ ምክንያት መሬቱን ለልማት ምቹ የማድረጉ ሂደትም ብዙ ዋጋ ያስከፈለው መሆኑን ይገልጻል። ‹‹ በመሬቱ ላይ ኖራና አዛባ በማድረግ በማከም ለም ለማድረግ ብዙ ዋጋ አስከፍሎኛል፤ ከአንድ ዓመት በላይ ጊዜም ወስዶብኛል›› ይላል።

መሬቱን ካለማም በኋላ መጀመሪያ የተከለው አቦካዶ ነበር፤ ሆኖም አተካከሉን ባለማወቁ እና መሬቱም በባህር ዛፉ ተጎድቶ ስለነበር ከተከላቸው 100 የአቦካዶ ችግኞች ሶስቱ ብቻ ሲቀሩ 97ቱ በሙሉ ወደሙበት። ወጣት አዳነ በዚህም ተስፋ አልቆረጠም፤ አንድ ከከንባታ አካባቢ የመጣ ጓደኛውን በጉዳዩ ላይ አማከረ ፤ እሱ ያለበት አካባቢ የአየር ንብረት ከከንባታ አካባቢ ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ ዝንጅብል ቢተክል እንደሚያዋጣው ጓደኛው መከረው፤ ምክሩንም ተቀብሎ ተገበረ።

‹‹ግን ደግሞ ዝንጅብል በእኛ አካባቢ ያልተለመደ በመሆኑ ልከስር እንደምችል እያሰብኩኝ በ500 ካሬ ላይ 100 ኩንታል ተከልኩኝ፤ በዚህም 24 ኩንታል አገኘሁና ፤ ምርቱንም በ156 ሺ ብር ሸጥኩት›› ሲል ይገልጻል። ‹‹ውጤቱን አበረታች መሆን ስመለከት የበለጠ ለመስራት አነሳሳኝ፤ ዛሬም ድረስ በግብርና ስራ ላይ እንድቀጥል አደረገኝ፤ ለካ መሬታችን ከሰራንበት ወርቅ ነው ብዬ እንዳስብ አደረገኝ›› በማለት ተስፋውን ያለመለመለትን አጋጣሚ ያስታውሳል።


ወጣት አዳነ ሹሜ

**‹‹ከዚህ ቀደም የመንግሥት ጠባቂ ነበርኩ፤ አሁን ግን ከራሴ አልፌ ለሌሎች የአካባቢዬ ወጣቶች ተስፋ ሆኛለሁ››**

ከዝንጅብሉ ያገኘውን ገንዘብ በሙሉ ኪሱ ሳይከት ጉቶ በመንቀልና የሚያለማበትን መሬት በማስፋፋት ከአርባ ምንጭ አንድ ሺ የሙዝ ችግኝ በማምጣት ተከለ። በዚህም አልተወሰነም፤ አንድ አንድ ሺ 500 የቡና ችግኝ በሙዝ መሃል በመትከል የአካባቢውን ገፅታ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ መቀየር ቻለ።

ወጣቱ በአሁኑ ወቅትም ቡናው ማፍራት መጀመሩን ይናገራል። ጥረቱን ያየው የከተማ አስተዳደሩ ደግሞ በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ 300 ሺ ብር የብድር ድጋፍ አደረገለትና የእርሻ ስፍራውንም ሆነ የምርት መጠኑን በእጥፍ ከፍ ማድረጉን ይገልፃል።

ከተተከለ አንድ ዓመት የሆነው ሙዝም ቢሆን ማፍራት መጀመሩን ከስሩ የሚያበልቀውን ውላጅ ችግኝ (ሰከር) ለሌሎች የአካባቢው አርሶ አደሮች እየሸጠ ተጠቃሚ መሆን መቻሉን ወጣት እንዳለ ያስረዳል። ‹‹ከአንድ ሙዝ ሰከር ብቻ 60 ብር አገኛለሁ፤ ሙዙ ሙሉ ለሙሉ ሲበስል ደግሞ እያንዳንዱ ግንድ 40 ኪሎ የሚይዝ በመሆኑ የማገኘው ገቢ በከፍተኛ መጠን እንደሚጨምር አልጠራጠርም›› ሲል በቁርጠኝነት ይናገራል። ሙዙ ደርሶ ለገበያ ሲያቀርብም አንዱን ኪሎ እስከ 30 ብር ለመሸጥ ማቀዱን ተናግሮ፤ ይህም አሁን ያለውን የካፒታል አቅም በከፍተኛ ደረጃ ያሳድግልኛል ብሎ ተስፋ ጥሎበታል።

‹‹ከዚህ ቀደም የመንግሥት ጠባቂ ነበርኩ፤ አሁን ግን ከራሴ አልፌ ለሌሎች የአካባቢዬ ወጣቶች ተስፋ ሆኛለሁ›› ሲል ለበርካታ ወጣቶች ስራ መፍጠሩ ተጨማሪ ኩራት እንደሆነለት ይናገራል። የእሱን ተሞክሮ ያዩ ጓደኞቹም የባህር ዛፍ መሬታቸውን እየመነጠሩ የምግብ ዋስትና ሊያረጋጡ፣ ጥሩ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ ወደሚችሉ የግብርና ስራዎች እንዲገቡ ምክር እንደሚሰጣቸው ይናገራል። ይህን ምክር ለመስጠትና ተሞክሮውን ለማጋራት ደግሞ የአካባቢያቸው የወጣት ሊግ መሪ መሆኑ ጠቅሞታል። ከዚህ ባሻገርም በመንደሩ ላሉ 40 አባወራዎች አንድ ኩንታል ዝንጅብል በመከፋፋል በነፃ ወስደው እንዲያለሙ ማድረጉን ነው ያመለከተው።

ወጣት እንዳለ በአሁኑ ወቅት ለ15 ወጣቶች ቋሚ፤ አምስት ለሚሆኑት ደግሞ በጊዜያዊነት የስራ እድል መፍጠር ችሏል። ስራውን በማስፋት እስከ 100 ሺ ለሚደርሱ የአካባቢው ወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር አቅዷል።

ወጣት አዳነ፤ ከአንድ ዓመት በፊት ስራውን ሲጀምር ምንም ካፒታል እንዳልነበረው አስታውሶ፤ ላጋጠሙት ተግዳሮቶች እጅ ሳይሰጥ ቀን ከሌሊት በመልፋቱ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር የሚደርስ ሃብት ማፍራት መቻሉን ይጠቁማል። በእንድብር ከፍተኛ የችግኝ እጥረት መኖሩን የሚጠቅሰው ወጣት እንዳለ፤ ያዘጋጃቸውን የቡና፣ የሙዝ እና የተለያዩ ፍራፍሬዎች ችግኞች በዘንድሮው ክረምት ለህብረተሰቡ ለማቅረብ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ያመለክታል።

የመነጠረውን የባህር ዛፍ እንጨት በመጠቀም 90 ቆርቆሮ የወሰደ ትልቅ ቤት መስራቱን ጠቁሞ፤ ከእርሻው ጎን ለጎንም የእንስሳት እርባታ ለመጀመር የሚያስፈልጉትን ዝግጅቶች ማጠናቀቁንም ያመለክታል። ‹‹አንድ ሃበሻ ከብት ገዝቼ ከፈረንጁ ጋር አዳቀልኩትና ከሰሞኑ ደግሞ ጊደር አግኝቻለሁ፤ ወደፊት ግን የእንስሳት እርባታውን ለማስፋፋት እቅድ አለኝ፤ ለዚህም ነው አስቀድሜ የማረባበትን ስፍራ ያዘጋጀሁት›› በማለት ወደ ከፍተኛ ባለሃብትነት ለመሸጋገር ያደረገውን ጥረት ያስረዳል።

በጥምር ግብርና ዘርፍ ወደ ኢንቨስተርነት የማደግ ተስፋ መሰነቁን የሚገልፀው አርሶአደሩ የጤና ባለሙያ፤ በአሁኑ ወቅት በንብ ማነብና ዓሳ ልማት ሥራም ለመሰማራት ዝግጅት እያደረገ መሆኑን አስታውቋል። ‹‹በአሁኑ ወቅት ሁለት ዘመናዊ ቀፎ ገዝቻለሁ፤ የዓሳ ኩሬ ለመስራትም ዝግጅት እያደረኩ ነው›› በማለት ይጠቁማል።

ይሁን እንጂ አሁን ያለው ቦታ ላሰበው ሥራ በቂ እንደማይሆን ይነገራል። ላሰበው ልማት የከተማው አስተዳደር ቦታ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ማሰቡንም አጫውቶናል። ይህ ከተሳካለት ደግሞ አቦካዶ፣ ዝንጅብል፣ ቡና እና ሌሎች የግብርና ውጤቶችን በስፋትና በጥራት በማምረት ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገራት ለመላክና ለሀገሩ የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት ማቀዱን ተናግሯል።

ወጣት እንዳለ፤ ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶች በተለይም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው በሙያቸው ስራ ባለማግኘታቸው ምክንያት ተመልሰው ቤተሰብ ላይ የተቀመጡ ወጣቶች ከእሱ ህይወት እንዲማሩ ይመክራል። ‹‹ስራ ካልናቁና ከሰሩ መለወጥ እንደሚቻል በራሴ ህይወት አይቻለሁ፤ ሌሎች ወጣቾም የማንንም ድጋፍ ሳይጠብቁ እንደእኔ አዕምሯቸውንና ጉልበታቸውን በመጠቀም ስራ ፈጣሪ ሊሆኑ ይገባል›› ይላል።

‹‹እኔ በብር ብቻ አላምንም፤ ተነሳሽነቱ ከሌለ ገንዘቡ ቢኖርም ውጤታማ መሆን አይቻልም›› ያለው ወጣቱ፣ ስለዚህ ወጣቶች ብድር ማግኘት አልቻልኩም፤ የሚደግፈኝ አላገኘሁም ብለው እጃቸውን አጣጥፈው ሊቀመጡ እንደማይገባም አስገንዝቧል። አጠገባቸው ያለውንና ተፈጥሮ የሰጣቸውን አቅም ተጠቅመው ራሳቸውን ሊለውጡ እንደሚገባም አስታውቋል። ‹‹ትምህርት መማር ጥሩ ነው፤ ግን ደግሞ በተማርንበት ዘርፍ ስራ ካላገኘን ብሎ ማማረር ግን ተገቢ አይደለም፤ ይልቁንም ያላየነውና በእጃችንን ያለውን ሃብት ተረድተን ልንጠቀምበት ይገባል›› የሚለው ደግሞ የጤና መኮንኑ አርሶአደር ሌላው ምክሩ ነው።

# ተናጋሪው ዶሴ

# የራይድ ዘራፊው መጨረሻ

አስመረት ብስራት



አንድ ሰው አንድ ነገር ካለው ያንን ነገር ማን ሊጠቀምበት እንደሚገባ የመወሰን መብት አለው። ለምሳሌ ያህል፣ ከሌሎች ልጆች ጋር ለመጫወት ቤታቸው ልትሄዱ ትችሉ ይሆናል። ወደ ቤታችሁ ስትመለሱ ግን ከእነሱ ቤት አንድ ነገር ወስዳችሁ ብትመጡ ተገቢ አይደለም። የልጆቹ አባት ወይም እናት ካልፈቀዱ በቀር ምንም ነገር መውሰድ የለባችሁም። እነሱን ሳትጠይቁ ምንም ነገር ወስዳችሁ ብትገኙ ግን ይህ ተግባር ሌብነት ነው። አንድን ነገር ለመስረቅ የምትፈተኑት ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? የእናንተ ያልሆነውን ነገር ስትመኙ ነው። ስትሰርቁ ሌላ ሰው ቢያይችሁ እንኳ አምላክ ያያል ብሎ መቆጠብ የግድ ነው። አምላክ ደግሞ ስርቆትን እንደሚጠላ ማስታወስ ይኖርባቸዋል። ለአምላክና ለሰው ፍቅር ካላችሁ ፈጽሞ ሌባ እንዳትሆን ይረዳችኋል። በማለት በልጅነታችን ወላጆቻችን የሀይማኖት አባቶች የመከሩንን ምክር እንዳነሳ ያደረገኝ በቀላል ሌብነት ተነስተው ዘራፊ ስለሆኑ ወጣቶች ታሪክ ላካፍላቹ ስለወደድኩ ነው።

በቅድሚያ ይህን ታሪክ ለማስተማሪያ ይሁን ብለው ጋዜጣችን ላይ እንድጠቀም የፈቀዱልንን የአዲስ አበባ ፖሊስ መዘገብ ቤት አባላት ከልብ እያመሰገነኩ ታሪኩን ላካፍላችሁ።

## ልማደኞቹ ዘራፊዎች

ጓደኝነታቸው የሚያስቀና ሲወጡም ሲገቡም የማይለያዩ ልጆች ነበሩ። መሽቶ ተለያይቶ ነግቶ እስኪገናኙ የሚነፋፈቁት ጓደኛሞች እድሜያቸው ተቀራራቢ ከመሆኑም በላይ አንድ ሰፈር ተወልደው እዛው አድገው አብረው ነበር የአስኳላን ደጅ የረገጡት።

በልጅነታቸው ጨዋታ የሚያበዙ ዘዋሪ ልጆች ቢሆንም የሰው ምክር የሚቀበሉ ታዛዥ ልጆች ነበሩ። ከፍ ከፍ እያሉ ሲሄዱ ግን ሳንቲም አየሰረቁ ጣፋጮችን መብላት የተለያዩ ነገሮችን መግዛት ተለማመዱ። ወላጆቻቸውም ልብ ሳይሉ ቀርተው ይሆን ቸል ብለው ሳይቀጧቸው ይቀራሉ።

እድሜያቸው ከፍ እያለ ሲሄድ ግን በከረሜላና በብስኩት የጀመሩትን ግዢ ወደ አደንዛዥ ሱስ አሳድገው ያገኙትን በሙሉ የሚመነትፉ ዋልጌ ልጆች ሆኑ። በልጅነታቸው አብረው ትምህርት ቤት እንደገቡት ሁሉ አንድ ላይ ትምህርታቸውን አቋረጡ።

ከዛም በየሰፈሩ ማውደልደል፤ ታክሲ ተራ እየቆሙ የተሳፋሪን ኪስ ማውለቅ ዋና ተግባራቸው ሆነ። ቀድመው ቸል ያሏቸው ወላጆቾቻቸውም ዘግይተውም ቢሆን የልጆቻቸውን መበላሸት እንደተረዱ ቢመክሩም ቢያስመክሩመ ሰሚ ጆሮ አላገኙም።

በቀላል መነሻ ብዙ የለመዱት ልጆች እድሜያቸው ከፍ እያለ ሲሄድ ከበድ ከበድ ያሉ እቃዎችን በመስረቅ ከልጅነት ጀምሮ በሚያወቁት የዘረፋ ተግባር አጠናክረው ቀጠሉበት። ወጣቶቹም ለዚህ እኩይ ተግባራቸው ይመቻቸው ዘንድ ለብቻቸው ተከራይተው ዘርፎ አዳሪ ሆኑ።

## ባለራይዱ

ለፍቶ አዳሪ ወጣት ነው ባለራይዱ። ከትንሽ ነገር ተነስቶ ትልቅ የመሆን ሕልም የሰነቀ ወጣት። ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ያገኘውን ስራ በመስራት ትምህርቱን ይከታተል ነበር። ባለው ትርፍ ሰዓት በሙሉ ከመላላክ አንስቶ እስከ ወያላነት፤ ከወያላነት በተጨማሪ ሊስትሮውንም ጆብሎውንም እየሞከረ ያገኘውን ገንዘብ እቁብ ይጥልበት ነበር። በጣላት እቁብ አጠራቅሞ ትንሽዬ ሻይ ቤት ከፍቶ እየሰራ በትምህርቱ የገፋ ነበር። በትምህርቱም ውጤታማ ስለነበር ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በሆቴል ማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪውን ይዟል።

ትምህርቱን አጠናቆ በአንድ ሆቴል አስተዳዳሪ የመሆን እድል ሲያገኝ ከዚህ ቀደም ያጠራቀመውን ገንዘብና፤ የምግብ ቤቱን እቃ በመሸጥ የጎደለውን በመበደር ቪትዝ መኪና ገዛ። በሆቴሉ ውስጥ በፈረቃ ከመስራቱ የተነሳ ከእንቅልፍ የተረፈውን ጊዜ በሙሉ ራይድ በመስራት የተሻለ ሕይወት ለመኖር ይታትር ነበር።

ዘመኑን በሙሉ በስራና በትምህርት በማሳለፉ የተነሳ የፍቅር ጓደኛ እንኳን የኖረው ዘግይቶ ነበር። የወላጆቹ ለምን አታጋባም ጥያቄንና ውትወታን ለማስቀረት ብሎ ጓደኛ ቢይዝም ከልጅቷ ጋር በጣም በመግባባታቸው የተነሳ ደስ የሚል የፍቅር ጊዜ እያሳለፉ ነበር።

ከእሁድ በስተቀር ሁሉንም ቀንና ሌሊት በስራ የሚያሳልፈው ወጣት እዳውን ከፍሎ መኖሪያ ቤት እንደገዛ የወደዳትን ልጅ አግብቶ ተረጋግቶ ለመኖር አቅዶ በተለመደው ትጋት ስራውን ይሰራ ነበር። በአዲሱ ፍቅር ልቡ ቢጠፋም ሕልሙ ከፍ ያለ ነበርና ጊዜውን አቻችሎ በመያዝ እሁድ እሁድ ከፍቅሩ ጋር እያሳለፈ በተቀረው ቀን በሙሉ ይሰራ ነበር።

## ያልታሰበችው ምሽት

እለቱ ሰኔ 8 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት ከሌሊቱ 7 ሰዓት 20 ደቂቃ ከሶስቱ ዘራፊዎች መካከል ሲሳይ በኃይሉ የተባለው ተከሳሽ ካልተያዙ ሁለት ግብረ-አበሮቹ ጋር በመሆን የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ በዝናባማው የሰኔ ለሊት ነበር የተለመደ ስራቸውን ለመስራት ከቤት የወጡት።

ቦታው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ጀሞ ኪሩ ሆቴል ተብሎ ከሚጠራው አከባቢ በእለቱ ባለራይዱ የተለመደ አገልግሎቱን ለመስጠት ቆሞ ተሳፋሪ ይጠባበቅ ነበር። ወጣቱ የራይድ አገልግሎት የሚሰጥበትን 1 ሚሊዮን 400 ሺ ብር የሚገመተውን ቪትዝ መኪና ይዞ ቆሞ እያለ ሌቦቹ ጓደኛሞች ወደ እርሱ በመምጣት ፒያሳ እንዲያደርሳቸው በመጠየቅ 600 ብር ይስማማሉ፡፡

በዚሁ መሰረትም ተከሳሽ ከመኪናው የኋላ ወንበር በሾፌሩ በኩል፣ አንደኛው ሌባ፣ ሁለተኛው ሌባ ደግሞ በተሳፋሪ በኩል ከኋላ ወንበር በመቀመጥ መጓዝ ጀመሩ። በመጓዝ ላይ እንዳሉ ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ዓለም ሰላም ድልድይ አካባቢ ሲደርሱ ጋቢና የተቀመጠው ሌባ ታማሚ በመምሰል ሊያስታውከኝ ነው መኪናውን አቁምልኝ ሲል ባለራይዱን ይጠይቀዋል። ባለራይዱም ዳገቱን ጨርሼ ላቁምልህ በማለት በፍጥነት ሲያሽከረክር አንደኛው ሌባ ባለራይዱን በእጁ አንገቱን አንቆ በመያዝ እና በሁለት በኩል ስለት ያለውን ጩቤ አንገቱ ላይ አድርጎበት በማስፈራራትና ሁለቱንም እጆቹን በስለት በመውጋት ጉዳት እንዲደርስበት ያደርጋል፡፡

ሌላኛው ሌባ ደግሞ ራሱን እንዳይከላከል ከኋላ ተበዳይን በመጎተት የመኪናውን የእጅ ፍሬን ስቦ ተሽከርካሪው እንዲቆም በማድረግ የግል ተበዳይን በጋራ በመተባበር ከተሽከርካሪው ውስጥ አውጥተው ጥለው መኪናውን ወሰዱ። መረጃው የደረሰው ፖሊስም ክትትል በማድረግ ሲሳይ በኃይሉ የተባለውን ሌባ ከነሰረቀው ተሽከርካሪው ይያዛል፡፡

## የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ጥቆማ እንደደረሰው ክትትል በመጀመሩ የተነሳ የተሰረቀው ተሽከርካሪ ከዘራፊዎቹ እጅ ሳይወጣ ከአንደኛው ሌባ ጋር በቁጥጥር ስር ሊያውለው ቻሉ፤ ግብረ አበሮቹን እንዲጠቁም የተጠየቀው ተጠርጣሪ አሉ የተባለ ቦታን በሙሉ ቢያመላክትም ለጊዜው ሊደረስባቸው ሳይችል ቀረ። በዚህም የተነሳ የተበዳይን ንብረት ይዞ እጅ ከፍንጅ የተያዘውን ሌባ ከሶ ሊያስፈርድበት ወሰነ።

በዚህም የተገኘውን መረጃ በሙሉ አጠናቅሮ በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ አቀረበ።

በመሆኑም በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 671/1/ለ/ መሰረት ተከሳሽ በፈፀመው የከባድ ውንብድና ወንጀል ክስ ቀርቦበት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል፡፡

## የዐቃቤ ሕግ ክስ ዝርዝር

ዐቃቤ ሕግም ሲሳይ በኃይሉ የተባለው ተከሳሽ ካልተያዙ ሁለት ግብረ-አበሮቹ ጋር በመሆን የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ሰኔ 8 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት ከሌሊቱ 7 ሰዓት ከ 20 ደቂቃ ሲሆን በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ጀሞ ኪሩ ሆቴል ተብሎ ከሚጠራው ቦታ የግል ተበዳይ የራይድ አገልግሎት የሚሰጥበትን 1 ሚሊዮን 400 ሺ ብር የሚገመት ዋጋ ያላትን ቪትዝ መኪና ይዞ ቆሞ እያለ ተከሳሽ ወደ እርሱ በመምጣት ፒያሳ እንዲያደርሳቸው በመጠየቅ 600 ብር ይስማማሉ፡፡

በዚሁ መሰረትም ተከሳሽ ከመኪናው የኋላ ወንበር በሾፌሩ በኩል፣ አንደኛው ያልተያዘው ግብረ-አበር ጋቢና፣ 2ኛና ያልተያዘው ግብረ-አበር ደግሞ በተሳፋሪ በኩል ከኋላ ወንበር በመቀመጥ በመጓዝ ላይ እንዳሉ ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 08 ዓለም ሰላም ድልድይ አካባቢ ሲደርሱ ጋቢና የተቀመጠው ታማሚ በመምሰል ሊያስመልሰኝ ነው መኪናውን አቁምልኝ ሲል የግል ተበዳይን ሲጠይቅ ዳገቱን ጨርሼ ላቁምልህ በማለት በፍጥነት ሲያሽከረክር ተከሳሽ የግል ተበዳይን በእጁ አንገቱን አንቆ በመያዝ እና በሁለት በኩል ስለት ያለውን ጩቤ አንገቱ ላይ አድርጎበት በማስፈራራትና ሁለቱንም እጆቹን በስለት በመውጋት ጉዳት እንዲደርስበት ያደረጋል፡፡

2ኛው ያልተያዘው ግብረ-አበር ደግሞ የግል ተበዳይን እንዳይከላከል ከኋላ ተበዳይን በመጎተት የመኪናውን የእጅ ፍሬን ስቦ ተሽከርካሪው እንዲቆም በማድረግ የግል ተበዳይን በጋራ በመተባበር ከተሽከርካሪው ውስጥ አውጥተው ጥለው መኪናውን የወሰዱ ሲሆን ተከሳሽ በፖሊስ ክትትል ከነተሽከርካሪው ይያዛል፡፡

በመሆኑም በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 671/1/ለ/ መሰረት ተከሳሽ በፈፀመው የከባድ ውንብድና ወንጀል ክስ ቀርቦበት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል፡፡

## ውሳኔ

**በክርክሩ ሂደትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰሙ በኋላ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ተከሳሽ የመከላከያ ምስክር የለኝም በማለት የቀረበበትን ክስ መከላከል አልቻለም ነበር። ተከሳሽ የቀረበበትን ወንጀል ማስተባበል ባለመቻሉ ምክንያት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት በተከሳሽ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠትና የቅጣት ውሳኔ በማሳረፍ በ13 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ሰነድ ማጥፋት ወይስ ቆሻሻ ማስወገድ?

**ዋስልኝ አየለ**

የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ «ኅብር ሕይወቴ» መጽሐፍ ላይ ያነበብኩት አንድ ገጠመኛቸው ትዝ አለኝ። ደርግ ንጉሣዊ ሥርዓቱን አስወግዶ ይሁን ኢህአዴግ ደርግን አስወግዶ በየትኛው እንደሆነ ዘነጋሁት፤ ብቻ ግን ፕሮፌሰር ባህሩና ባልደረቦቻቸው ባለፈው ሥርዓት ዘመን የነበሩ ሰነዶችን እየሰበሰቡ ነው። የመንግሥት ተቋማት የወረቀት ሰነዶችን በማስወገድ ስም አውጥተው እየጣሉ ነው። ከሚጣሉ ወረቀቶች ውስጥ ግለሰቦች ይጠቅመናል ያሉትን እየመረጡ ይወስዳሉ።

ይህን ያወቀ አንድ የእነ ፕሮፌሰር ባህሩ ባልደረባ አንድ ሃሳብ መጣለት። ይሄውም ያልተገኙ ወረቀቶችን በየግለሰቦች ቤት እየዞሩ መፈለግና መግዛት። የተጣሉ ወረቀቶችን እያነሱ መልቀም የጀመሩት እነ ፕሮፌሰር ባህሩ፤ ከግለሰቦች ቤትም «እባካችሁ ከመንገድ ላይ የለቀማችሁትን ወረቀት ሸጡልን» ማለት ጀመሩ። ይህን ሲያደርጉ ማንም የገንዘብ ድጋፍ አያደርግላቸውም፤ ከኪሳቸው እያወጡ ነበር የሚገዙት። ለምን? የወረቀቶችን ዋጋ (ጥቅም) ያውቃሉ!

ይህን ያስታወሰኝ የበጀት መዝጊያ የሆነው የሰኔ ወር በመጣ ቁጥር፣ ተቋማት ቦታ በቀየሩ ቁጥር፣ ተቋማት እድሳት ባደረጉ ቁጥር፣ እያወጡ የሚጥሉትን የወረቀት ክምር ሳስተውል ነው። በተለይም በዚህ ዓመት በኮሪደር ልማቱ ምክንያት በብዙ አካባቢዎች ከተቋማት አቅራቢያ የሚጣሉ ወረቀቶችና ሌሎች ዕቃዎች ብዙ ነበሩ። ችግሩ ግን በግንባታ እና በእድሳት ምክንያት የመጣ አይደለም፤ በየጊዜው በተቋማት ጊቢ ውስጥ የወረቀት ክምር ማየት የተለመደ ነው።

ይህን የሚያደርጉ አካላት «ለምን አደረጋችሁ?» ቢባሉ የሚኖሯቸው መልሶች ግልጽ ናቸው። የመጀመሪያው «ቆሻሻ እያስወገድን ነው» የሚል ነው። ቆሻሻ የሚሉበት ምክንያት ደግሞ ወረቀቶቹ ያገለገሉ ስለሆኑ፣ ለወደፊት ለምንም ነገር ስለማያስፈልጉ፣ በአጭሩ አገልግሎታቸው ያለፈ ስለሆነ አይጠቅሙም ብለን ነው ይላሉ።

ለእነዚህ ሰዎች የወረቀቶች አገልግሎት ለዕለቱና ለወቅቱ ብቻ ነው። ለምሳሌ፤ የ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት የተመለከቱ ሥራዎችን የያዙ ሰነዶች ከሰኔ 30 በኋላ የ2017 ዓ.ም በጀት ዓመት ስለሆነ ከዚህ በኋላ አያስፈልጉም ብለው ያምናሉ ማለት ነው። ወይም ከአሥር ዓመት በላይ የቆዩ ወረቀቶች «ከዚህ በኋላ ምን ይሠራሉ?» ብለው ያስባሉ ማለት ነው። ለሚያስወግዱት አካላት ወይም እንዲወገድ ትዕዛዝ ለሠጡት አመራሮች የወረቀቶች አገልግሎት ማለት ከእነርሱ ኃላፊነት ጋር የተያያዘ ብቻ ይመስላቸዋል፤ ምናልባትም ኃላፊነቱን ሲለቁት አይመለከተኝምና ይወገድ ይሉ ይሆናል። ወረቀቶቹ የያዙት መረጃ የተጠያቂነት ጊዜ ገደቡ ካለፈ ከዚህ በኋላ ስለማልጠየቅበት ቢወገድም ችግር የለውም ብለው ያስቡ ይሆናል።

ነገሩ ግን ወዲህ ነው። እያንዳንዱ የተጻፈ የተቋማት ሰነድ የሀገሪቱ ታሪክ ነው። ቀላል ምሳሌ እንውሰድ። ከ50 ዓመታት በፊት የተጻፉ ሰነዶች ስናገኝ በመገረም ስሜት ውስጥ ነው የምናነባቸው። እነዚህ ሰነዶች ያን ያህል ከባድ እና የሀገር ዳር ድንበር ጉዳይ ሆነው አይደለም፤ ምናልባትም በመማሪያ ደብተር ሽፋን ላይ የሚሞላ ቅጽ ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን የዚያን ዘመን ቅርጽ ያሳያሉ። የዚያን ዘመን ሁኔታዎች ይገልጻሉ። እንኳን የትልልቅ ተቋምት ሰነድ ይቅርና የአንድ አነስተኛ ምግብ ቤት የምግብ ዝርዝር (ሜኑ) ከዛሬ 30 እና 50 ዓመታት በኋላ ዋጋ አለው። ጠረጴዛ ላይ የተነጠፈ የምግብ ዋጋ ዝርዝር ለዛሬው ያሉትን ምግቦች ከማየት ያለፈ ምንም ስሜት አይሰጠንም። ለወደፊቱ ትውልድ ግን የሚነግረው ነገር አለው። በተቋማት ውስጥ የፋይናንስ ክፍል ትንንሽ ደረሰኞች ዋጋ አላቸው፤ የስብሰባ ቃለ ጉባዔዎች ዋጋ አላቸው። 25ኛ ዓመት፣ 50ኛ ዓመት... ምናምን እየተባለ በሚከበረው የተቋማት ማስተዋወቂያ ከበራሪ ወረቀቶች እስከ መጽሔት ይታተማል፤ እነዚህ ወረቀቶች ዋጋ አላቸው። ያለምንም ምክንያት የሚታተም ወረቀት አይኖርም። ስለዚህ እነዚህን ሰነዶች የሚያጠፏቸው ለምን ይሆን?

«ለምን ታጠፏቸዋላችሁ?» ብለን ብንጠይቅ ሁለተኛው መልስ የሚሆነው ወደ ዲጂታል ቀይረነዋል የሚል ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ ሁለት ነገር መጠራጠር አለብን። አንደኛው፤ የምር እነዚያ ሁሉ ወደ ውጭ የተጣሉ ወረቀቶች ወደ ዲጂታል ተቀይረዋል ወይ? የሚለው ነው። አስፈላጊ አይደሉም ብለው የጣሏቸውን ወረቀቶች ወደ ዲጂታል ይቀይሯቸዋል ብሎ ማመን አስቸጋሪ ነው። መጽሔቶችንና ሌሎች በራሪ ወረቀቶችን፣ ሰነዶችን የሚጥሏቸው አገልግሎታቸው አልፏል፣ ምንም የሚያስፈልጉበት ጉዳይ አይኖርም በሚል እንጂ ቦታ አጠበቡ በሚል ብቻ አይደለም። የተጣሉትን ሁሉ ወደ ዲጂታል ቀይረውት ከሆነ ግን እሰየው ነበር!

ወደ ዲጂታል ቀይረውታል የሚለውን በየዋህነት አምነን ተቀብለን እንበልና ሁለተኛውን ችግር እንመልከት። በሠለጠኑት ሀገራት መረጃዎች ወደ ዲጂታል ሲቀየሩ ወረቀት ላይ የነበሩትን በማጥፋት አይደለም፤ የወረቀቶቹ ራሳቸውን ችለው ሌላ ታሪክ ናቸው። ለብቻቸው ይቀመጣሉ። «ከወረቀት ነፃ አገልግሎት» ሲባል ቢያንስ ከዚህ በኋላ የሚሠሩ ሥራዎችን በዲጂታል ማድረግ እንጂ የነበሩትን ማጥፋት ማለት አይደለም። የቴክኖሎጂው ፈጣሪ በሆኑት ሀገራት እንኳን የወረቀት አገልግሎት አልቀረም። በዋናነት ደግሞ ከዚህ በፊት የነበሩ የወረቀት ሰነዶችን በማጥፋት አይደለም።

የመጀመሪያው ችግር ሁሉም ወደ ዲጂታል የተቀየሩ ላይሆኑ ይችላሉ የሚለው ከሆነ፤ ሁለተኛው ችግር ደግሞ ዲጂታል ራሱ አስተማማኝ አይደለም። የዲጂታሉ ዓለም ምን ምን ደካማ ጎኖች አሉት? የሚሉ መረጃዎችን ስንበረብር የምናገኘው የመጀመሪያው ችግር የሳይበር ጥቃት ነው። ምንም እንኳን ጥቃቱ የሚደረገው ሀገራዊ ምሥጢር ለሆኑት መረጃዎች ቢሆንም እግረ መንገዱን ግን ብዙ መረጃዎችም ይጠፋሉ። በሌላ በኩል የዲጂታሉ ዓለም ስንት ዘመን እንደሚኖር አይታወቅም። ለአሠራር ቀልጣፋና ምቹ የሆነውን ያህል የሚያጋጥሙት ችግሮች ደግሞ በታዳጊ ሀገራት አቅም የማይጠገን ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፤ ኢሜይል ለብዙ ዓመታት የቆዩ መረጃዎችን አጠፋለሁ ብሎ ነበር። ልክ እንደዚህ ሁሉ ሌሎች የዲጂታል አማራጮችም ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል ማለት ነው።

ምንም እንኳን በዚህ ዘመን የወረቀት አገልግሎት እንጠቀም ማለት ቢያስቸግርም ቢያንስ ግን የተገለገልንባቸውን ማጥፋት አይገባም።

«ለምን ያጠፏቸዋል?» ብለን ብንጠይቅ አንድ አደገኛ ብልሹ አሠራር ሊኖር ይችላል። ለምሳሌ፤ ብልሹ አሠራሮች እንዳይታዩባቸው የሚፈልጉ፣ ከሕዝብ በጀት ላይ አለግባብ ሥራ የሠሩ ሰነዱ እንዳይገኝ ሊያጠፉት ይችላሉ። በተለይም አንዳንድ ሰነዶች የተጠያቂነት ጊዜ ገደብ ያላቸው ናቸው። ያ ጊዜ ገደብ ካለፈ ቢያንስ ለጊዜው ተጠያቂ አልሆንም በሚል የታሪክ ተጠያቂ ላለመሆን ያጠፉት ይሆናል። በግደለሽነት ከሚጣሉት ሰነዶች ይልቅ ተጠያቂነትን ለመሸሽ ታስቦበት የሚጠፉ ሰነዶች የበለጠ ጎጂ ናቸው።

ያም ሆነ ይህ ተቋማት በዚህ ጉዳይ ላይ ተጠያቂነት ያለበት አሠራር ሊኖራቸው ይገባል። በግደለሽነት ሰነዶችን የሚያጠፉ ሠራተኞችና አመራሮችም የዛሬ ሥራ የነገ ታሪክ ነውና አውጥቶ ከመጣል ይልቅ በአግባቡ ማስቀመጥ ይለመድ! የሀገር ታሪክ ሲባል የግድ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወይም የምርጫ ክርክር ሂደት ብቻ አይደለም። የሥራ ሰነዶችም ለታሪክ የሚቀመጡ እንጂ በቆሻሻ ስም የሚወገዱ አይደሉም!

# ዓለም አቀፍ

## ሄዝቦላህ የተገደሉ መሪውን ሞት ለመበቀል 200 ሮኬቶች እና ድሮኖችን ወደ እስራኤል ተኮሰ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሌባኖሱ ታጣቂ ቡድን ሄዝቦላህ ከ200 በላይ ሮኬቶች እና ድሮኖችን ወደ ሰሜናዊ እስራኤል መተኮሱ ተሰምቷል። ቡድኑ ይህን ጥቃት ያደረሰው እስራኤል ከሄዝቦላህ ነባር አመራሮች መካከል አንዱን ከገደለች በኋላ ነው።

እስራኤል በጥቃቱ ምክንያት አንድ የጦር መኮንን መገደሉን ስታሳውቅ በተለያዩ ቦታዎች እሣት መነሳቱን ገልጣለች። የእስራኤል ወታደራዊ ኃይል እንደለገጸው ለጥቃቱ ምላሽ ለመስጠት በደቡባዊ ሌባኖስ የሚገኙ የሄዝቦላህ "ወታደራዊ መሠረተ-ልማቶች" ላይ እርምጃ ወስዷል።

የሌባኖስ መገናኛ ብዙኃን እንደዘገቡት በእስራኤል የድሮን ጥቃት ምክንያት በሁላ ከተማ አንድ ሰው ተገድሏል።

ረቡዕ ከሰዓት የመጀመሪያውን ጥቃት የሰነዘረው ሄዝቦላህ አስቀድሞ 100 ሮኬቶችን ወደ እስራኤል ተኩሷል። ይህ ጥቃት ባለፉት 9 ወራት ከታዩት እጅግ ከፍተኛው ሲሆን፣ በእስራኤል እና በታጣቂው ቡድን መካከል የለየለት ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ተሰግቷል።

በደቡባዊ ሌባኖስ ታየር ከተማ የተገደሉት የሒዝቦላ አዛዥ ሞሐመድ ኒማህ ናስር የቡድኑ ነባር አመራር የነበሩ ሲሆን፣ በእስራኤል መገደላቸው ሄዝቦላህን አስቆጥቷል።

የእስራኤል ጦር ሠራዊት እንደሚለው ናስር የሄዝቦላህን አዚዝ የተባለ ክንፍ ይመሩ የነበሩና ከደቡብ ምዕራብ ሌባኖስ ለሚደረጉ የሮኬት ጥቃቶች ተጠያቂ ናቸው። እስራኤል ነባሩ የጦር አዛዥ "በርካታ የሽብር ጥቃቶችን ፈፅመዋል" ስትል ትከሳለች።

እስራኤል፤ ናስር የሄዝቦላህ ሌላኛው ክንፍ መሪ የሆኑት ታሌብ ሳሚ አብዱላህ አጋር ናቸው የምትል ሲሆን፣ ታሌብ ባለፈው ወር መገደላቸውን ተከትሎ ሄዝቦላህ ከ200 በላይ ሮኬቶች እና ሚሳዔሎችን ወደ ሰሜናዊ እስራኤል ማስወንጨፉ ይታወሳል።

መስከረም 26 የተፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ በእስራኤል እና ሐማስ መካከል ጋዛ ውስጥ ጦርነት ከተቀሰቀሰ ጀምሮ በእስራኤል እና በሊባኖስ ድንበር አቅራቢያ በየቀኑ በሚባል ደረጃ የተኩስ ልውውጥ ይካሄዳል።

ሄዝቦላህ ጥቃቱን የሚፈጽመው የፍልስጤሙን ቡድን ሐማስን ለመደገፍ እንደሆነ የሚገልጥ ሲሆን፣ ይህ ቡድን በኢራን እንሚደገፍ ይታወቃል። ሄዝቦላህ እና ሐማስ በእስራኤል፣ በዩናይትድ ኪንግደም እና በሌሎች ሀገራት ሽብርተኛ ቡድኖች ተብለው ተፈርጀዋል።

እስካሁን ድረስ 400 ሰዎች ሊባኖስ ውስጥ መገደላቸው የተሰማ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ የሄዝቦላህ ተዋጊዎች ናቸው። እስራኤል ውስጥ ደግሞ 25 ሰዎች ሲገደሉ አብዛኛዎቹ ወታደሮች እንደሆኑ ተነግሯል።

የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤኒያሚን ኔታኒያሁ በሰሜናዊ እስራኤል በኩል መረጋጋትን ለማስፈን እንደሚሠሩ ተናግረዋል።

"የትኛውም እኛን ሊጎዳ የመጣ መጨረሻው ሞት ነው። ይህንን በተግባር እያሳየን ነው" ሲሉ ሐሙስ ዕለት ተናግረዋል።

በእስራኤል እና ሄዝቦላህ መካከል ባለው ግጭት ምክንያት በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ በሰሜናዊ እስራኤል እና ደቡባዊ ሊባኖስ የሚኖሩ ሰላማዊ ዜጎች ቀያቸው ጥለው ለመሸሽ ተገደዋል።

"የመሪያችን የተወዳጁ ሐጅ አቡ ኒማህ [ናስር] ግድያን ለመበቀል የምናደርገው እርምጃ ዛሬ በቅፅበታዊ መንገድ ተጀምሯል" ሲሉ የሄዝቦላህ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሐሺም ሳፊዲን ሐሙስ በተካሄደው የናስር ቀብር ላይ ተናግረዋል።

"ይህ ጥቃት ጠላታችን አስቧቸው በማያውቃቸው ሥፍራዎች ላይ ጭምር የሚካሄድ ነው" ብለዋል።

በተባበሩት መንግሥታት የሌባኖስ ሰላም ማስከበር ኃይል ቃል አቀባይ እንደሚሉት ከሁለቱም ወገኖች የተሰነዘሩ ጥቃቶች እየከፉ ነው ብለው እስራኤል እና ሄዝቦላህ ከዚህ እንዲቆጠቡ አሳስበዋል።

"በጣም አሳስቦናል. . . ምክንያቱም አለመግባባት ካለ ግጭቱ ከፍ ወዳለ ደረጃ ሊሸጋገር ይችላል" ሲሉ ቃል-አቀባዩ ካንዲስ አድሪየል ለቢቢሲ ተናግረዋል።



የተባበሩት መንግሥታት እና ዩናይትድ ስቴትስ ግጭቱ ከተስፋፋ ኢራን እና ሌሎች የቀጣናው ቡድኖች ሊቀላቀሉ ይችላሉ የሚል ስጋታቸውን ገልጸዋል።

የእስራኤል ባለሥልጣናት ዲፕሎማሲያዊ ድርድሮች ከከሸፉ ለጦርነት ዝግጁ መሆናቸውን በተደጋጋሚ አሳውቀዋል። የመከላከያ ሚኒስትሩ ዮዋቭ ጋላንት ወታደራዊ ኃይሉ "ሊባኖስ ውስጥ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ተዘጋጅቷል፤ አሊያም ድርድር ልናደርግ እንችላለን" ብለዋል።

ከሐማስ እጅግ የላቀ ኃይል እንዳለው የሚነገርለት ሄዝቦላህ ከእስራኤል ጋር የለየለት ጦርነት ውስጥ መግባት እንደማይፈልግ አሳውቆ፤ በእስራኤል እና በሐማስ መካከል የሚደረገውን ድርድር እንደሚታዘብ ገልጿል። ነገር ግን ጦርነት የሚነሳ ከሆነ "ያለምንም ሕግ" እንደሚዋጋ አስጠንቅቋል።

## የፈረንሳይ አየር መንገድ በፓሪስ ኦሎምፒክ ምክንያት እስከ 180 ሚሊዮን ዩሮ ኪሳራ ሊደርስበት እንደሚችል ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የፈረንሳይ አየር መንገድ በፓሪስ ኦሎምፒክ ምክንያት እስከ 180 ሚሊዮን ዩሮ ኪሳራ ሊደርስበት እንደሚችል ገለጸ።

በየአራት ዓመቱ የሚካሄደው ተወዳጁ የኦሎምፒክ ስፖርት በፈረንሳይ መዲና ፓሪስ አስተናጋጅነት ከቀናት በኋላ ይካሄዳል።

ኤር ፍራንስ የተሰኘው የፈረንሳይ አየር መንገድ ይህን የፓሪስ ኦሎምፒክ ታሳቢ በማድረግ እስከ 180 ሚሊዮን ዩሮ ገቢ ሊያገኝ እንደሚችል እቅድ አውጥቶ ነበር።

ይሁንና አየር መንገዱ የፓሪስ ኦሎምፒክ ውድድሮችን ለመሳተፍ የሚጓዙ መንገደኞች ሌላ ምርጫ እየተከተሉብኝ ነው ሲል አስታውቋል።

ዩሮ ኒውስ ኤር ፍራንስን ዋቢ አድርጎ እንደዘገበው ከሆነ ውድድሩን ለመካፈል ወደ ፓሪስ ከሚመጡ አጠቃላይ አትሌቶች እና ተመልካቾች ውስጥ 20 በመቶውን ለማጓጓዝ እቅድ ነበረው።

በቀን 125 ሺህ መንገደኞችን በማጓጓዝ እስከ 180 ሺህ ዩሮ ገቢ ለማግኘት እቅድ ቢኖረንም መንገደኞች እስካሁን የቅድመ በረራ እቅዳቸው ላይ አልተመዘገቡም ብሏል።

ከዚህ ባለፈም አትሌቶች እና ተመልካቾች ከኤር ፍራንስ ይልቅ ሌሎች አየር መንገዶችን እና የመጓጓዣ አማራጮን ለመጠቀም እያሰቡ ነውም ሲል ቅሬታውን ገልጿል።

በፈረንሳይ ያለው የፖለቲካ ትኩሳት እና የአደባባይ ተቃውሞዎች ወደ ፓሪስ ለመምጣት ፍላጎት የነበራቸውን ጎብኚዎች ሃሳባቸውን እንዲቀይሩ ትልቁ ምክንያት እንደሆነም በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።




ፓሪስ ከተማ የዘንድሮውን ኦሎምፒክ ውድድር ከሀምሌ 19 እስከ ነሀሴ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የምታስተናግድ ሲሆን ከተማዋ የኦሎምፒክ ውድድርን ስታስተናግ ከ100 ዓመት በኋላ ነው።

# ውሳኔ ብቻውን ውሳኔ ነው?

አስናቀ ፀጋዬ

የሰዎች የእለት ተእለት ክዋኔ በውሳኔ የተሞላ ነው። በእያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴያቸው ውስጥም ሰዎች የተለያዩ ውሳኔዎችን ያሳልፋሉ። ከዚህ አንፃር ውሳኔ የሰው ልጅ አንዱ የሕይወት አካል እንደሆነ ይቆጠራል። የሰውን ልጅ ከፍና ዝቅ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥም የመወሰን አቅሙ እንደሆነ ይነገራል። ለዛም ነው ውሳኔን በራስ፣ በኑሮና በሕይወት ላይ ማስተላለፍ እጅግ ቁልፍ ጉዳይ ነው የሚባለው።

ውሳኔ አንድን ነገር የማድረግና ያለማድረግ ምርጫ ነው። አንድን ነገር ለማድረግና ላለማድረግ በመምረጥ ሂደት ግን ማመንታት፣ ለመወሰን መቸገር፣ ቸኩሎ አልያም ደግሞ ዘግይቶ መወሰን፣ ለመወሰን ከራስ ጋር ሙግት መግጠምና ሌሎችም መሰል እንቅፋቶች ያጋጥማሉ። ዋናው ቁም ነገር ግን የተሰላ ውሳኔ መወሰን ውጤቱ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ መረዳት ያሻል። በተለይ ደግሞ ከውሳኔ በፊት የውሳኔውን ውጤት በጥልቀት መረዳት የተሳሳተ ውሳኔ ከማሳለፍ ይታደጋል።

ለምሳሌ አንድ ሰው በቀን አንድ ገፅ መፅሃፍ ለማንበብ ወስኖ ያለውን ካደረገ አእምሮውን ለማሳደግ ቆርጦ ተነስቷል። በየቀኑ ለተወሰኑ ደቂቃዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለማድረግ ከወሰነ የአካል ብቃቱን እያሳደገ ነው። ይህ ሲባል እግረ መንገዱን የሰውነቱን ጤና ከመጠበቅ በዘለለ ትንፋሹን፣ ፅናቱንና ነገሮችን የመቋቋም አቅሙን እያጎለበተ ነው። ይህ ሁሉ የሚመጣው ታዲያ በውሳኔ ነው።

በጣም ለሚወደው ነገር ትልቅ ትኩረት ለመስጠት የወሰነ ሰው የገንዘብ ስኬት ወደሚሰጠው ነገር ራሱን እየወሰደ ነው። የማኅበረሰብ ወይም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ የተወሰነ ግዜ ለመስጠት የወሰነና ያለውን የሚፈፀም ሰው የሕሊና እርካታ ወደሚሰጠው ነገር እየተጓዘ ነው። ለሚወዳቸው ሰዎች፣ ለቤተሰቦቹ፣ ለጓደኞቹ፣ ለፍቅረኛው ግዜ ለመስጠት የወሰነ ሰው ስሜታዊ እርካታ ለሚሰጠው ነገር እየጣረ ነው። ታዲያ አንተስ መቼ ነው በአካል፣ በፋይናስ፣ በስነ-ልቦና፣ ለስሜትና ደስተኛ ለሚያደርጉ ነገሮች ግዜ ለመስጠት የምትወስነው መቼ ነው?

አንዳንድ ሰዎች «ደስተኛ ወይም ስኬታማ ያልሆንኩት የምፈልገው ነገር ስላልተሟላልኝ ነው፤ በቤተሰቦቼ ምክንያት ነው፤ በዙሪያዬ ባሉ ጓደኞቼ ምክንያት ነው ወይ ደግሞ በምኖርበት ሀገር ድህነት ምክንያት ነው» ሊሉ ይችላሉ። እነርሱ እነዚህን እንደምክንያት ቢዘረዝሩም ታዲያ ምክንያታቸው ውሃ የሚቋጥር አይደለም። ምክንያቱም መወሰን ስላልቻሉ ነው። እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር በእጃቸው ለማስገባት ቢወስኑ ኖሮ ለዛ ነገር የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍለው ማሳካት አያቅታቸውም ነበር።

አንድ ጀልባ ቀዛፊ የልጅነትና አብሮት የተማረ ጓደኛው ከሀገሪቱ ንጉስ ቀጥሎ ትልቅ ስልጣን የሚባለውን ጠቅላይ ሚኒስትርነት እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ ሁሌም እንቆቅልሽ ይሆንበታል። እሱ ከኔ ምን የተለየ ነገር ቢኖረው ነው እኔ እዚህ ውሃ ለውሃ ጀልባ ለመቅዘፍ እየተንከራተትኩ እሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሆነው ብሎ ሁሌም አምርሮ ይቀናና ይናደድ ነበር።

በአንድ አጋጣሚ የሀገሪቱ ንጉስ ከባድ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ የሚያደርጉትን ስብሰባ ለማካሄድ ካቢኔያቸውን ሰብስበው ያንን ወንዝ መሻገር ነበረባቸውና የዚህን ሰው ጀልባ ይሳፈራሉ። ጀልባውን ተሳፍረው ወንዙን ከተሻገሩ በኋላ ንጉሱና ካቢኔያቸው ማታ ከወንዝ ማዶ ጊዚያዊ ድንኳን አዘጋጅተው ባረፉበት ወቅት ሌሊት ላይ ለቅሶ ያዘለ ከባድ ጩኸት ይሰማሉ። ከዛም ባለጀልባውን አስጠርተው ጩኸቱ ምን እንደሆነ ይጠይቁታል።

ባለጀልባውም ቆይ አረጋግጬ ልምጣ ብሏቸው ትንሽ ቆይቶ ተመልሶ ይመጣና ድመት እንደጮኸች ይነግራቸዋል። «የጫካ ናት ወይስ የቤት ድመት?» ብለው ሲጠይቁት «ቆይ እሱንም አረጋግጬ ልምጣ» ብሎ ተመልሶ ሄዶ አራጋግጦ ይመጣና «የቤት ድመት ነች ለማዳ ናት» ብሎ ይመልሳል። «አሃ! ምን ሆና ነው ግን የጮኸችው» ብለው ይጠይቁታል። አሁንም «ንጉስ ሆይ አሁንም ሄጄ አረጋግጬ ልምጣ» ብሎ ተመልሶ ሄዶ ይመጣና ሙጭሊቶቹ በምትወልድበት ግዜ እንደጮኸች ይነግራቸዋል። ንጉሱም «ስንት ልጆች ወለደች?» ብለው ይጠይቁታል። «ቆይ ንጉስ ሆይ እሱንም አረጋግጬ ልምጣ» ይላቸውና አሁንም ደርሶ ይመለስና አራት ሙጭሊቶች እንደወለደች ይነግራቸዋል።

ንጉሱ አሁንም መልሰው የሙጭሊቶቹ ቀለማቸው ምን አይነት እንደሆነ ይጠይቁታል። እርሱም አሁንም አረጋግጬ ልመለስ ይላቸውና ደርሶ ይመለሳል። ሁለት ጥቁር ሁለት ነጭ ሙጭሊቶች እንደወለደች ይነግራቸዋል። «እንዴ እናትዬዋስ ቀለሟ ምን ይመስላል» ብለው ንጉሱ ሲጠይቁት ንጉስ ሆይ እሱንም አረጋግጬ ልምጣ ይላቸውና ተመልሶ መጥቶ የእናትዬዋ ቀለም ነጭ በጥቁር እንደሆነ ይነግራቸዋል።

በዚህ ግዜ ንጉሱ ታዲያ ለድመቷ ምን አደረክላት ብለው ጀልባ ቀዛፊውን ይጠይቁታል። እርሱም ንጉስ ሆይ ቆይ አንድ ነገር አድርጌላት ልምጣ ብሎ ሊሄድ ሲል ቆይ ቆይ አንተ እዚሁ ጋር ቆየኝ ብለው እዛው በቆመበት የሀገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ካረፈበት ድንኳን አስጠርተው «የሆነ ጩኸት ሰምቼ ነበር እስኪ ምን እንደሆነ አጣራ» ብለው ይልኩታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም እሺ ብሎ ከአፍታ ቆይታ በኋላ ይመለሳል።

ጩኸቱ የተሰማው አንድ ጥቁር በነጭ ቀለም ያላት የቤት ድመት አራት ሙጭሊቶች በወለደች ቅፅበት እንደሆነና የወለደቻቸው ሙጭሊቶችም ሁለት ነጭ ሁለት ጥቁር ሲሆኑ ለእናትዬዋ ምግብና ወተት እንደተሰጣት እርሷና ሙጭሊቶቿ ለማዳ የቤት ድመት በመሆናቸው የዱር አውሬ እንዳያጠቃቸው አስተማማኝ በሆነ አጥር እንደከለሏቸው ይናገራል።

ንጉሱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላቀረበላቸው ሪፖርት አመስግነው ካሰናበቱት በኋላ ወደጀልባ ቀዛፊው ዞረው እንዲህ አሉት። «ጀልባህን ተሳፍረን ስንመጣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን እያየህ ሲሰማህ የነበረውን የቅናት ስሜት አስተውዬው ነበር። የኔና የእርሱ ልዩነት ምንድን ነው ብለህ ለራስህ ስጠይቅ እንደነበረም እገምታለሁ። አንተ ብዙ ግዜ ተመላልሰህ ሁኔታውን ተመልክተህ ያልወሰንከውን ውሳኔ እርሱ በአንድ ምልታ ወጥቶ ወስኖ ነገሮችን አስተካክሎ መጣ።»

እንግዲህ በሕይወታችን ውስጥ ወደተለያየ አቅጣጫ የእኛን በሳል ውሳኔዎች ሊጠይቁ የሚችሉ ወቅቶች ይመጣሉ። እነዛን ወቅቶች ግን የምናልፋቸው ወይም የምንወስናቸው በየትኛው ጥበባችን ነው? በሕይወታቸው ላይ አስገራሚ ለውጥ ያመጡ ሰዎች ከባድ ውሳኔዎችን ወስነው እዛ እንደደረሱ አስብ። አንተ ራሱ አሁን የደረስክበትን ደረጃ የወሰነልህ ከዛሬ አምስትና አስር ዓመት በፊት ታደርጋቸው የነበሩ ነገሮች ናቸው። ታነባቸው የነበሩ መፅሃፍት፣ ታያቸው የነበሩ የቴሌቪዥን ሾዎችና ፊልሞች፣ ትሰማቸው የነበሩ ዘፈኖች፣ በዙሪያህ ይሰበሰቡ የነበሩ ጓደኞችህ፣ አብረሃቸው የምትውላቸው ሰዎች ናቸው ዛሬ የቆምክበትን የወሰኑልህ።

ታዲያ አንድ ነገር አስተውል። የዛሬ አምስት ዓመት የሚኖርህንም ሁኔታ የሚወስኑት አሁን የምታደርጋቸው ነገሮች ናቸው። ስለዚህ በቶሎ ወስን። ሚዛን ወደምትፈልገው አቅጣጫ እንድታጋድል ከፈለክ ያን አቅጣጫ ጫን አድርገህ መያዝ ብቻ ነው የሚጠበቅብህ። ስለዚህ አንተም የዛሬ አምስትና አስር ዓመት መሄድ ወደምትፈልግበት አቅጣጫ ሚዛን እንድታጋድል አሁኑኑ ወስንና ውሳኔህን ተግባራዊ ለማድረግ ወስን። ውሳኔ ከዚህ በላይ ምንም አይጠይቅም። ሕይወት ቀያሪ ነገር ነው ተጠቀምበት። ነገር ግን ደግሞ ትክለኛ ውሳኔ በትክክለኛው ቦታና ሰዓት ለመወሰን ከፈለክ የሚከተሉትን ስድስት ነጥቦች ተከተል።

### 1ኛ. ችግሩን ጠንቅቆ ማወቅ

ምንም ሰው አንድ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት መሰብሰብ ያለበትን መረጃዎች ሁሉ መሰብሰብ ይኖርበታል። ማወቅ ያለበትን ነገር ሁሉ ማወቅ አለበት። ይሁንና ስለሚወስነው ነገር በቂ መረጃ ከሌለው ግራ ይጋባል። ይሁንና መረጃ መሰብሰብ ሲጀምር በቂ እውቀት ኖሮት እርገጠኝነትና ልበ ሙሉነት ይሰማዋል። እንዲያም ሆኖ ከመጠን በላይ መረጃ ከተሰበሰበ ደግሞ መልሶ ግራ መጋባት ይመጣል። ስለዚህ በቂ መረጃ ሲኖር መወሰን የግድ ይላል።

እዚህ ጋር በቂ መረጃ እንዳለ እንዴት ሊታወቅ ይችላል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ለዚህ መልስ ባይኖርም በቂ መረጃ ሲኖር እርገጥኝነት ይሰማል። ለእርግጠኝነት የቀረበ ስሜት ሲሰማ ደግሞ መወሰን ያስፈልጋል። ምክንያቱም ያኔ በቂ መረጃ ተይዟል ማለት ነው።

### 2ኛ. የሚወሰነው ውሳኔ ከሕይወት ዓላማ ጋር አብሮ መሄድ አለበት

ለዛሬ ወይም ለግዚያዊ ጥቅም ብለን ቀላል ውሳኔ መወሰን የለብንም። ዘላቂውን ጥቅም ማስቀደም አለብን። ነገ ምን ሊፈጠር ይችላል፤ ምን ላገኝ እችላለሁ፤ ምን ልጎዳ እችላለሁ ብለን ማሰብ አለብን። ምንም ነገር ከመወሰናችን በፊት ነገን ማሰብ ይኖርብናል። ውሳኔያችን ከሕይወት አላማችን፣ ከነገው ፍላጎታችን፣ ከመዳረሻችን፣ ከማንነታችን ጋር አብሮ እንደሚሄድ እርግጠኛ መሆን አለብን።

### 3ኛ. ሌላ ሰው እንደምንመክር አስበን መወሰን

እንደምታውቁት ለሌሎች ሰዎች መምከር እንችልበታለን። ሰዎች ምን ቢያደርጉ ምን እንደሚሳካላቸው እናውቅበታለን። ለራሳችን ነው የማናውቀው። ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም ይባላል። እኛም ብንሆን ብዙ ግዜ ለሰው እንጂ ለራሳችን አናውቅም። ስለዚህ ራሳችን የገጠመን ችግር ሌላ ሰው እንደገጠመው አስበን ራሳችንን መምከር ያስፈልጋል። እንደሁለተኛና ሶስተኛ ወገን አይተን ራሳችንን «እንዲህ ብታደርግ እንዲህ ይፈጠራል፤ እንዲህ ብታደርግ ይሄ ነው መፍትሄው» እያልን ራሳችንን መምከር ይገባል። ያኔ ከጫና እንውጣለን። ምክንያቱም እኔ አይደለውም ችግር ውስጥ የገባሁት እንላለን። ያኔ ብዙ መፍትሄ ይመጣል። ከመፍትሄዎቹ መካከል ጥሩውን መርጠን መወሰን ነው።

### 4ኛ. ውጤቱን ማነፃፀር

አንድ ነገር ከመወሰናችን በፊት «ያ የምንወስነው ውሳኔ ምን ሊያስከትል ይችላል፤ እንዲህ ብማር ነገ ደስተኛ ላልሆን እችላለሁ፤ እንዲህ ብሰራ ስራው ላያድግ ይችላል፤ ይህን ቢዝነስ ብጀምር እኮ መጨረሻ ላይ ሄዶ ሄዶ እዚህ ጋር ሊያቆም ይችላል» ብለን ብዙ ነገር አስበን ውጤቱን አሰላስለንና አወዳድረን መወሰን ያስፈልጋል። እንደዛ ካላደረግን መጨረሻ ላይ የሚመጠው ውጤት ከባድ ይሆናል። ምክንያቱም አሁን ያለንበት ጋር ቆመን ብቻ ማየት የለንበትም። ስለዚህ አንድ ነገር ከመወሰናችን በፊት ውጤቱን ማሰብና አስቀድሞ መተንበይ አለብን። ከዛ በኋላ የሚጎዳ ከሆነ መተው፤ የሚጠቅም ከሆነ ደግሞ መቀጠል ነው።

### 5ኛ. በየቀኑ የምንወስናቸው ትናንሽ ውሳኔዎች ላይ መስማመድ

በቀን ውስጥ በጣም ብዙ ውሳኔዎችን እንወስናለን። ጠዋት ስንት ሰዓት ልነሳ፣ ስራ ልግባ አልግባ፤ ምን ልብላ፤ ከማጋር ልዋል፤ ምን ሳደርግ ልዋል፤ ምን ላድርግ፤ በምን ልዝናና፤ ምን ስሰራ ላምሽ፤ ምን ልጠጣ፤ ምን ልብላ .... ወዘተ ብዙ ውሳኔ አለ። እነዚህ ውሳኔዎች ግን ሕይወታችንን እስከመጨረሻ ድረስ ሊቀይሩት ይችላሉ። ምክንያቱም የዛሬ አምስት ዓመት በፊት ታደርጋቸው የነበሩ ነገሮች፣ አብርሃቸው ትውላቸው የነበሩ ሰዎች፣ ታያቸው የነበሩ የቴሌቪዥን ፊልሞች፣ ድራማዎች፣ ታነባቸው የነበሩ መፅሃፍቶች፣ አብራሀቸው ትሰበስባቸው የነበሩ ሰዎች በሙሉ ዛሬ የደረስክበትን ደረጃ ወስነዋል። ዛሬ የምታደርጋቸውም ነገሮች የዛሬ አምስትና አስር ዓመት የምትደርስበትን ይወስናሉ። የዛሬ አምስት ዓመት ያደረከው ከዛሬው ጋር ተመሳሳይ ከሆነ የዛሬም አምስት ዓመት አሁን ያለህበት ቦታ ነው የምትኖረው።

ስለዚህ በየቀኑ የምታደርጋቸው ትናንሽ ውሳኔዎች ሕይወትህን እስከመጨረሻው ይቀይሩታል። አስተውል ትልቁን መርከብ የሚያሰምጠው ማእበል ብቻ አይደለም። ከታች በትንሽዬ ቀዳዳ ውሃ መግባት ከጀመረ የግዜ ጉዳይ ነው እንጂ መርከቡ መስጠሙ አይቀርም። ስለዚህ አንተም የምትወስናቸው ውሳኔዎች በሙሉ ሕይወትህን ሊቀይሩት ይችላሉ። እነዚህ ትናንሽ ውሳኔዎች ላይ ብልጥ ከሆንክ፣ ጥበበኛ ከሆንክ ትላልቆቹ ውሳኔዎች ሲመጡ መወሰን አይከብድህም። ምክንያቱም በትናንሾቹ ጥሩ በራስ መተማመን ይሰማህልና።

### 6ኛ. ከውሳኔ በኋላ ማመንታት የለብንም

ይህ ወሳኝ ነጥብ ነው። ከውሳኔ በኋላ ማመንታት የለብንም። አንዳንድ ግዜ ጥሩ ውሳኔ እንወስንና ቆይ እስኪ ይህን ነገር ባደርገው ብለን ማመንታት ከጀመርን ሌላ የማይረባ ውሳኔ ይከተልና እሱን ወስነን የማይረባ ነገር ይፈጠራል። ስለዚህ በደምብ አስበን ከወሰንን በኋላ ወደ ድርጊት መግባት አለብን። እርግጥ ወሰንን ማለት ወደ ድርጊት ገባን ማለት አይደለም።

ስለዚህ ከላይ የተቀመጡት አምስት ትክክለኛ ውሳኔ ለማሳለፍ የሚረዱ ነጥቦችን ከተጠቀማችሁ መወሰን አለባችሁ። መወሰን ግን ብቻውን በቂ አይደለም ወደገደለው ወደ ድርጊት መግባት ይኖርባችኋል። ያ ማለት ስድስተኛውን ነጥብ ልብ ማለት ይገባል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## ልማቱ የሚፈልገውን የግብር ገቢ ለመሰብሰብ!

የአንድ ሀገር መንግሥት የልማት ፋይናንስ ምንጮች ከሆኑት መካከል ግብር/ ታክስ/ እና ባንኮች ከዜጎች ቁጠባ የሚሰበስቡት ሀብት ይጠቀሳሉ፡፡ የውጭ ብድርና ርዳታም በእዚህ በኩል አስተዋጽኦ እንዳለው ቢታመንም፣ ይህ ሀብት ግን ለተለያዩ ተጽዕኖዎች የተጋለጠ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ አስተማማኝ ምንጭ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትም የሚያካሂዳቸውን የልማት እቅዶች ለማሳካት የሚያስፈልገውን የሀብት ምንጭ በወሳኝነት ከግብር/ታክስ/ በሚገኝ ገቢና ከዜጎች በሚሰበሰብ ቁጠባ ላይ አድርጎ ይሰራል፡፡ ለዚህም ከግብር የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ በትኩረት እየሰራ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎም ባለፉት ዓመታት በየዓመቱ በግብር ገቢ ላይ ለውጦችን ማሳየትም ተችሏል፡፡

ገቢው በየዓመቱ እያደገ ስለመሆኑም ሁሌም ይገለጻል፤ በዚያው ልክም የሚሰበሰበው ገቢ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት አኳያ ሲታይ ዝቅተኛ ሲባል ነው የኖረው፤ ከፍተኛ ገቢ መሰብሰቡ በተጠቆመበት በአሁኑ ወቅትም ይሄው ጉዳይ ተነስቷል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ከትናንት በስቲያ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት እንዳስገነዘቡት፤ በዚህ በጀት ዓመት መንግሥት 529 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ ባለፉት አስራ አንድ ወራት /የዚህ ወር አልተጠቃለለም/ 466 ቢሊዮን ብር ወይም 96 በመቶ ገቢ ሰብስቧል፡፡ ይሄም ከአምናው ጋር ሲወዳደር ከፍተኛ መሻሻል ያለው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአንዳንድ አፍሪካ ሀገሮችን የገቢ ግብር አሰባሰብ በመጥቀስ ኢትዮጵያ ያለችበትን የግብር ገቢ አሰባሰብን አቅምንም አሳይተዋል፡፡ ሞሮኮ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርቷ /ጂዲፒዋ/ 32 በመቶ፣ ደቡብ አፍሪካ 24 በመቶ ፣ ኬንያም 15 ነጥብ 9 በመቶ በየዓመቱ እንደሚሰበስቡ ጠቁመዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከኬንያ በግማሽ ያነሰ፤ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርቷ /ጂዲፒዋ/ ሰባት በመቶ ገደማ ብቻ ግብር እንደምትሰበስብ ጠቅሰው፣ ሰባት በመቶውን ወደ 10 በመቶ ማድረስ ብትችል የልማት ጥያቄዎቿን በስፋት ለመመለስ እንደሚያግዛት አመልክተዋል።

በግብር ገቢው የሚሰበሰበው ሀብት ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ያህል እንዳይሆን አድርገዋል ከሚባሉት ምክንያቶች መካከል የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ፣ ገቢ መሰወር፣ ህገወጥ ንግድ የሚሉት ሁሌም ይጠቀሳሉ፤ ዘንድሮም ተጠቅሰዋል፡፡ መንግሥት እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የገቢ ሰብሳቢ ተቋሙን በማዘመንና በመሳሰሉት ላይ በስፋት እየሰራ ይገኛል፡፡ በዘርፉ ለውጦች እየታዩ ያሉትም ይህንኑ ተከትሎ ነው፡፡ በግብር ገቢ አሰባሰቡ ላይ አሁንም የተጠናከረ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

በግብር አሰባሰብ ላይ የበለጠ ውጤታማ ለመሆን ሥራ ላይ ውለው ውጤታማ ማድረግ ያስቻሉትን አሰራሮች ማስቀጠል፣ የማኅበረሰቡን የግብር ግንዛቤ ማስፋት፣ ዜጎች በፈቃደኝነት ግብር መክፈል ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ላይም መስራት ሁሌም ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባሮች ናቸው፡፡ በሕገወጦች ላይ ርምጃ እየተወሰደ ባለበት ሁኔታ ችግሩ እንዴት ሊቀጥል እንደቻለ በጥናት በመለየት ሌሎች መፍትሔዎችን ማመላከትም ይገባል፡፡

ለህቀኛ ግብር ከፋዮችና የግብር ሰብሳቢ ሠራተኞች የሚሰጠውን እውቅና ማስፋት፣ ለአጠቃላይ ግብር ከፋዩ የሚያበረታታ ሥርዓት በስፋት መዘርጋት፣ እንደ ጎዳና ነጋዴዎች ያሉት በሕጋዊ መንገድ ሊሰሩ የሚችሉበትን ሁኔታ በስፋት መፍጠር፣ ወደ ግብር መረብ መግባት ባለባቸው ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ በትኩረት መሥራት የግብር ገቢውን ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡

በተለይ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ከሀገር ውስጥም አልፎ ከውጭ ድርጅቶች ጋር መሥራት የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል፡፡ በዚህ ሥራ ላይ ያሉት ዜጎች ግብር እንዲከፍሉ እንዲሁም ዘመኑን የሚመጥን ግብር አሰባሰብ እንዲኖር ለማድረግ የውጪ ተሞክሮን መቃኘትም ያስፈልጋል፡፡

የገቢ ፍላጎቱ እየጨመረ መምጣት፣ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ተገቢውን ግብር መሰብሰብ የሚገባ መሆኑ እንዲሁም የአፍሪካ ሀገሮች ተሞክሮ ሲታይ በገቢ አሰባሰብ ላይ ከቀደሙት መንገዶችም በላይ አዳዲስ የገቢ አሰባሰብ መንገዶችን መማተርን የግድ እንደሚል አውቆ መሥራት ቀጣዩ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል፡፡

የልማት ፍላጎቱ፣ ለልማቱ የሚያስፈልገው ሀብት ከፍተኛ እየሆነ በመጣበት በዚህ ዘመን እነዚህን ሁሉ የሚመጥን ርምጃ መውሰድ የግድ ይሆናል፡፡ ለዚህም በግብር አሰባሰባቸው ውጤታማ የሆኑ እንደ ሞሮኮ ያሉ ሀገሮችን ተሞክሮ ጠጋ ብሎ መመልከትና ለሀገር የሚጠቅሙ አሠራሮችን በመቅሰም ፈጥኖ መተግበር ወሳኝ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## "እኔ እማውቀው አለማወቄን ነው"

ግርማ መንግሥቴ

ጽሑፋችንን በተጠቃሽ ብቻ ሳይሆን ዘመን ተሻጋሪ፤ ዓለም አቀፍ ብቻ ሳይሆን ዩኒቨርሳል (ሁለንታዊ) በሆነ፤ አብዝቶም ታዋቂና እልፍ አእላፍ ጊዜ ተጠቃሽ በሆነ ጥቅስ (ኮቴብል ኮት) ስንጀምር ያለ አንዳች ምክንያት ሳይሆን፣ "ምናልባት" እንዲሉ፣ ምናልባት አንዳች የሚለው ነገር ካለ ይል ዘንድ በማሰብ ነው።

ይህ፣ ዛሬ ወደዚህ ገጽ ያመጣነው "እኔ እማውቀው አለማወቄን ነው" ተጠቃሽ ጥቅስ አዲስ አይደለም ("አዲስ አይደለም" ማለት "ተረድተነዋል" ማለት ባይሆንም)። አዲስ ላለመሆኑ ማስረጃው ደግሞ ካልጠቀሱት የጠቀሱት ምሁራን፤ ካላካተቱት ያካተቱት ጥናቶች፤ በእለት ተእለት ሕይወታቸውና ሥራዎቻቸው ውስጥ ከማያዘወትሩት የሚያዘወትሩት ወዘተ መብዛታቸው ብቻ ሳይሆን፤ በየትምህርት ተቋማት በሮችና ግድግዳዎች፣ በጋዜጦችና መጽሔቶች አናት ላይ በብዛት አለመታጣቱም ጭምር ነው።

"እኔ እማውቀው አለማወቄን ነው" ለህሊና ማንቂያነት፤ ለአስተሳሰብ መግሪያነት፤ ለሃሳብ ማጠናከሪያነት፤ ለትሁት ባህርይ መገለጫነት፤ በአቋራጭ (በአጭሩ) ማስተማሪያነት፤ ለእውቀት ወርድ፣ ጥልቀት፣ ስፋት ማሳያነት፤ ከመታበይ መፈወሻነት፤ የ"ከእኔ በላይ ላሳር" ባዮች ማስታገሻነት፤ የሥነ ምግባር ማፅኛነት መድኃኒት በመሆን ሥራ ላይ ከዋለ ዘመኑ የሰነበተ ሲሆን፤ ለስንባቴውም ፈጣሪ ባለቤቱ የጥንት ግሪክ ፈላስፋ እና አስተማሪ፤ የዕውቀቱን ድንበር እና ልክ አሳምሮ የሚያውቀው፤ የሚያውቀውን ብቻ ሳይሆን አለማወቁንም የሚያስተምረው፤ እንዲሁም የምዕራቡ ዓለም ፍልስፍና መስራች (ሶቅራጥስ (470 ዓ.ዓ. — 399 ዓ.ዓ.)) መሆኑ ነው።

ወደ ርእሳችን እንምጣ። ያለ ምንም ፍርሀትም ሆነ ኩራት (ማን ነበር "ፍራትም የለች፤ ኩራትም የለች" ያለው?) አንድ መናገር የምንችለው እውነት ቢኖር በአሁኑ ሰአት ሀገራችን የሶቅራጥስ አይነት ሰው የሚያስፈልጋት መሆኑን ነው። የሶቅራጥስ አይነት ሰው እንኳን ባታገኝ እሱ ያለውን የሚረዳላት ሰው፤ እሱ ይሆን ዘንድ የተመኘውን የሚያደርግላት ሰው፤ "እኔ እማውቀው አለማወቄን ነው" የሚል(ላት) ሰው የሚያስፈልጋት መሆኑን ነው። ይህንን ያለ ምንም ኩራትም ሆነ ፍርሀት መናገር ይቻላል።

እዚህ ላይ የዚህ ጽሑፍ አላማ በቀድሞው ዘመን በዚሁ ጸሐፊ የልጅነት እድሜ ወቅት "ሁሉ አውቃለሁ ባይ፤ ሁሉ ተቺ፤ ሁሉ ❈ ❈ ❈፤ ሁሉ ❈ ❈ ❈" የተባለውን፤ እውነትም ይሁን ሀሰት፤ ተክክልም ይሁን ኢ-ትክክል ወዘተ ለማስታወስ አለመሆኑን ከወዲሁ ማስታወስ ያስፈልጋል። ወቅቱ፣ ርእዮቱና ስርአቱ የተለያየ ነውና ያንን እዚህ ማምጣት ምናልባትም ነገር መደባለቅ ብቻ ሳይሆን መደበላለቅ ሊሆን ስለሚችል በ"እኔ እማውቀው አለማወቄን ነው" ማለፉ የተሻለ ይሆናል።

ሰውየው አስቀድሞ እንዳለው፣ ተከታዮቹም ሆኑ ደቀ መዛሙርቱ እስከዛሬና እስከ ማእዜኑ እንዳስተጋቡለትና እንደሚያስተጋቡለት "ሁሉን አወቅ" ሰው የለም። ዛሬ ዛሬ ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን እንጂ ሁላችንም ኢትዮጵያን አናውቃትም። ሁላችንም ኢትዮጵያዊያን ነን እንጂ ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ አናውቅም።

ሁላችንም የኢትዮጵያ ዜጎች እንሁን እንጂ ስለ ኢትዮጵያ ሲባል በአያት ቅድመ አያቶቻችን፤ እናት አባቶቻችን የተከፈለውን መስዋእትነት (የፈሰሰውን ደም እና የተከሰከሰውን አጥንት) አናውቅም። ምንም አይደለም፤ "ሁሉን አወቅ" አለመሆን አያስጠይቅም፣ አያስወቅስምና፤ "ሁሉን አወቅ" መሆን አይቻልም (ከእሱ፣ ከላይኛው በስተቀር) እና ከሳሽም ተከሳሽም የለም፤ ሊኖርም አይችልም።

ዛሬ ኢትዮጵያን ባለማወቃችን ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ እያደረስነው ያለው ጉዳት ጉዳቱ ከዛሬ ይበልጥ ነገ የሚሰማን ይመስላል። ከምናውቀው የማናውቀው እንደሚበልጥ ባለማወቃችን ምክንያት ለማወቅም ይሁን ለመተዋወቅ የምናደርገው ጥረት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፤ ቀጫጫ ነው። ከብርሀኑ ይልቅ ጭለማውን አግዝፈን፤ ከፍቅሩ ይልቅ ጥላቻውን አፍቅረን አለማወቃችንን እያሳወቅን ሲሆን፤ ችግሩ አለማወቃችንን እራሳችን አለማወቃችን ነው።

ነፍሳቸውን ይማረውና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ከሚያዘወትሯቸው አገላለፆች መካከል አንዱ ድንቁርና እጅግ ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን የሚገልፁባት መንገድ ነበረች። "ሌላው ሀገር ስልጣን ከእውቀት ይመነጫል፤ እኛ ሀገር እውቀት ከስልጣን ይመነጫል።" የምትል። ሰውየው ምን ለማለት እንደ ፈለጉ አንባቢ በየቤቱ እሚለውን ይል ዘንድ ትተንለት ወደ "እኔ እማውቀው አለማወቄን ነው" እንመለስ። (ካስፈለገም፣ "እያወቁ በሄዱ መጠን አለማወቆትን ይረዳሉ" ያለውን ሰው ፈልጎ ለምን እንዳለው መጻፍ ይቻላል።)

> **አለማወቅ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ችግር ሆኖ አያውቅም፤ ችግር ሆኖ የሚያውቀው አለማወቅን አለማወቁ ነው**

እውነት፣ እውነት — አለማወቃችንን አለማወቃችን እንጂ ብናውቃት ኖሮ ኢትዮጵያ ምን አጥታ ነው ይሄ ሁሉ ጥል፤ ይሄ ሁሉ እሰጥ አገባ፤ ይሄ ሁሉ ረብሻ፤ ይሄ ሁሉ ንጥርቂያ፤ ይሄ ሁሉ መቧቋስ፤ ይሄ ሁሉ መካካድ፤ ከሁሉም በላይ ይሄ ሁሉ መገዳደል። ይሄ ሁሉስ የብሔር ከረጢት ለምን አስፈለገ? "እኔ እማውቀው አለማወቄን ነው" ማለትን ፈርተን እንጂ አለማወቃችንን አውቀን ለማወቅና መተዋወቅ ብንጣጣር "ሁሉ በጃችን፤ ሁሉ በደጃችን" ሆኖ አናገኘውም ነበርን? ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ብቻ ከአንድ የአፍሪካ ሀገር ስፋት በላይ የሆነ ታራሽ መሬት (ማእድኑን ዝም ነው) መኖሩን እናውቃለን፤ ካላወቅንስ አለማወቃችንን አውቀን ለማወቅ እንጥራለን?

በሀገራችን የመጀመሪያው የብሔረሰቦች እኩልነት አቀንቃኝ ገጣሚ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን "ይድረስ ለወንድሜ ለማላውቅህ" በማለት ያሰፈረው ዘመን ተሻጋሪ ግጥም የገጣሚውን አለማወቁን አስቀድሞ ስለማወቁ የማይናገረው የለምና አለማወቅን ማወቅ የበርካታ ችግሮች መፍትሔ ማፈላለጊያ መንገዶች ስለመሆኑ ማሳያ ነው።

ከበቂ በላይ እንደ ተባለው፣ በብዙዎች ጥናትና ምርምር ስራዎች በደማቁ እንደ ተሰመረበት "እኔ እማውቀው አለማወቄን ነው" የሚለው ፍልስፍናዊ አተያይ ለመጠየቅ (ለጥያቄ) ቀስቃሽ ነው። ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉትን የሚፈጥር ጓጓጭ ነው። አለማወቁን ከማያውቅ በተቃራኒ አለማወቁን የሚያውቅ ሰው ለማወቅ ይቆፍራል፤ ይጠይቃል፤ ያጠያይቃል።

አለማወቁን የሚያውቅ ከአለማወቁን ከማያውቀው በተቃራኒ እንደ በሬ ሽንት ወደ ኋላ ሳይሆን ጉዞው ወደ ፊት ነው፤ አለማወቁን ከማያውቀው ይልቅ ለሚያውቀው መጪው ዘመን ብሩህ ነው። አለማወቁን የሚያውቅ ሰው ለውይይት ክፍት ነው።

አለማወቅ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ችግር ሆኖ አያውቅም፤ ችግር ሆኖ የሚያውቀው አለማወቅን አለማወቁ ነው። በአሁኑ የፖለቲካል-ኢኮኖሚ ዘመን የጥፋት ሁሉ፤ የወንጀል ሁሉ፤ የግጭቶች ሁሉ ወዘተ አለማወቅ ሳይሆን አለማወቅን እራሱ አለማወቅ ነውና፤ አለማወቅን በማወቅ እስካልተካን ድረስ ኑሯችን በጭለማ ውስጥ ከመሆን አያመልጥም። አለማወቃችንን አውቀን ለመፍትሔ ካልተንደረደርን በስተቀር ጉዟችን የኋልዮሽ መሆኑ የማይቀር ነው። ዓለም አወቅ ዋጋ ማስከፈሉ የግድ ነው።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^ለስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## የክረምት ጫንቃዎች

መልካምሥራ አፈወርቅ

ብዙዎች የሰኔን መምጣት በጉጉት ይጠብቃሉ:: ይህ ወር የክረምቱ መግቢያ በር ነውና የቸርነት እጁ ሰፊ ነው:: ወቅቱን ብርቱ ገበሬ ለእርሻው፣ተማሪው ለውጤቱ፣ ሰፊዋ መሬት ደግሞ ለውሃ ጥሟ ይሹታል::

በዚህ ክረምት በርካቶች ለፍሬያቸው ይተጋሉ፣ ጊዜውን ተጠቅመው ጎዶሏቸውን የሚሞሉ፣ ቤታቸውን የሚደጉሙ፣ ኑሯቸውን የሚለውጡ ብዙ ናቸው:: እርግጥ ነው . ክረምት የራሱ የሚባል ችግር አለው፣ ድንገቴው ጎርፍ፣ ብዙ ያጠፋል፣ ጭቃው ማጡ ያሰለቻል፣ ብርድ ቆፈኑም ይከብዳል:: እንዲያም ሆኖ ክረምቱ ጸጋው የበዛ፣ ሲሳይ ቱርፋቱ የበረከተ ነው::

### ዘይነባ...

ማለዳውን ሻይ ቡናዋን ይዛ ከመንገድ ዳር የምትገኘው ዘይነባ ያለፉት በርካታ ክረምቶች ለእሷ መልካም ሆነው አልፈዋል:: በነዚህ ጊዜያት የአቅሚን ያህል አላጠችም:: በቀን ውሎዋ የምታገኘው ገቢ ለቤቷ ሙሉ ነበር:: ለትርፍ ባትሰራም፣ለወር ዕቁብ አታጣም:: ካላት ቆጥባ ከእጇ አብቃቅታ እንደራሷ ታድራለች::

ካገሯ ወሊሶ ከወጣች ሁለት አስርት ዓመታት የዘለለችው ወይዘሮ በአዲስ አበባ ኑሮ ያላየችው፣ ያልሞከረችው የለም:: በሰው ቤት ሰራተኝነት ዓመታትን ዘልቃለች:: በቀን ስራ ውሎ ጉልበቷን ከፍላለች፤ከፉ ደግ ያየችበት የትዳር ህይወት በቀላሉ ‹‹እንዲህ ነው›› የሚሉት አይደለም::

በቤት ኪራይ እንግልት፣ልጅ በማሳደግ ግዴታ ፣አብሮ በመኖር ጣጣ የከፈለችው ዋጋ ቀላል አይባልም:: ዛሬም ኑሮን ለማሸነፍ ከጎዳና ውላ ታመሻለች::ከብስኩት፣ ከአምባሻው አምስት፣ አስር ብላ የምትቆጥረው ገቢ አንዳንዴ የመጣበትን በወጉ አይመልስም:: ብክን፣ብትን ይልባታል:: የውሀ ቅዳ መልስ ህይወትን ለመቋቋም ስራ ባለበት መፍጠን፣ መሮጥ ልማዷ ነው::

አንዳንዴ ብስኩት አምባሻውን ተወት አድርጋ ከልብስ አጠባው ትገኛለች:: ድግስ ባለበት ሰፈር ሁሌም የወጥ ሰሪዎች ረዳት መሆን ብርቋ አይደለም:: ይህኛው ክፍያ ወዲያው ስለሚሰጣት ከሰራው መገኘት ምርጫዋ ነው:: የልብስ አጠባው ብር ቢዘገይም ባንክ እንዳለ ገንዘብ ትቆጥረዋለች::

የአጠባው ገንዘብ ጠርቀም ብሎ ሲደርስ ቀዳዳዎች ይሸፍናል::እንዲያም ሆኖ ስራው በቶሎ ላይገኝ ይችላል:: ሲገኝ ደግሞ ፈተና አያጣውም.ጉልበት ይጠይቃል፤ አቅምን ይፈትናል::በዚህ ስራ ሁሉም ጥሩና መጥፎ አይደለም:: አንዳንዶች ሲያሰሯት ከርመው ገንዘቧን ሊያዘገዩ፣አልያም ላይሰጡ ይችላሉ:: እንዲህ ሲገጥማት ሆድ ይብሳታል፣ ሀዘኗ ይልቃል::

አብዛኞች ግን እንዲህ አይደሉም:: ኑሮዋን ይረዳሉ፣ሸክሟን ያቀላሉ:: ካለችው በላይ ሰጥተው፣ለቤት ለልጇ የሚበጀውን ቋጥረው ይሸኟታል::ለእንዲህ አይነቶቹ ዘይነባ በእጅ በእግሯ ብትሰራ ቅር አይላትም፣ከተባለችው በላይ ፣ ስትታዘዝ ከልቧ ደስ እያላት ነው::

ብዙ ደንበኞቿ በእሷ ላይ ዕምነት ጥለዋል:: ልብስ ስታጥብ ከኪስ የምታገኘውን ገንዘብና ውድ ዕቃዎች ወደ ጉያዋ አትደብቅም:: በታማኝነት ይዛ ለባለቤቶቹ ትሰጣለች:: ይህ ማንነቷ መልካም ስም አሸልሟት ከደንበኞቿ አዝለቋታል::

ዘይነብ ከአንድ ዓመት በፊት መኖሪያዋ ከከተማው ወጣ ይል ነበር ::አካባቢው ከሌሎች ቦታዎች ለቤት ኪራይ የተሻለ ነው::ለእሷ አቅም ቀላል ባይሆንም ኑሮን በጉልበቷ ፣ በላቧ ወዝ ለማሸነፍ አስችሏታል:: የመንደሩ በረከት ለእሷና ለአንድዬ ልጇ ጉሮሮ አሳጥቷት አያውቅም:: ባላት ገዝታ ፣ ቤቷን ሞልታ ለማደር አቅም ሆኗት ዘልቋል::

ከአንድ ዓመት ወዲህ የዘይነባ ህይወት ካለፉት ዓመታት የተለየ ሆኗል:: የኖረችበት ሰፈር በልማት ምክንያት ከፈረሰ ወዲህ ወደመሀል ከተማ ልትመጣ ተገዳለች:: እንዲህ መሆኑ ለእሷ ቀላል አልሆነም:: በአቅሟ የቤት ኪራይ ማግኘት ፣ለስራዋ ቦታ መፈለግ ገቢዋን ማመጣጠን ሁሉ ፈትኗታል::

ከሁሉም በላይ የአንዲት ልጇ ጉዳይ ዕንቅልፍ

> **‹‹ዘንድሮ ደግሞ ከመጪው ክረምት ልትጋፈጥ፣ከብርድ ከጭቃው ልትታገል ቀን መቁጠር ይዛለች::እንደ አምናው ሁሉ ፈተና እንደሚገጥማት አልጠፋትም:: ከጀመረችው ሥራ ‹‹ይብቃኝ›› ብላ አልቆመችም::አሁንም አማራጭን ፍለጋ ትተጋለች:: ዛሬም ስለመኖሯ ትሮጣለች››**

ይነሳታል::ከአባቷ ጋር እሷ ከተወለደች ጥቂት ጊዜያት በኋላ ተለያይተዋል:: ጥሏት ከሄደ ወዲህ ለአንዲትም ቀን ዓይኗን አላየም:: በእሷ ትከሻ ብቻ የምታድገው ህጻን አሁን ሰድስት ዓመት አልፏታል:: እናት ለስራ በየሄደችበት ይዛት ትዞራለች:: ልብስ ስታጥብ፣እንጀራ ስትጋግር፣ብስኩትና ሻይ ስትሸጥ ሁሉ ከጉያዋ አትርቅም::

ዘይነባ ለአዲስ ኑሮ መሀል ከተማ ከገባች ጀምሮ ለልጇም ሆነ ለእሷ ህይወት አልቀለለም::ስለመኖር ብዙ ሞክራለች:: ድንች ቅቀላ፣በሚጥሚጣ ለመሸጥ ተቀምጣለች:: ስራውን ቀድመው ሌሎች መያዛቸው ግን ለገበያዋ አላመቻም:: እንደነሱ ጥሩ ቦታ ማግኘት፣ ደንበኞችን ማበራከት አልሆነላትም::

እሱን ትታ ደግሞ ብስኩትና አምባሻ፣ መሸጥ ጀመረች ::ሻይና ቡና በፔርሙስ ሞልታ ተጠቃሚውን ናፈቀች:: ለጥቂት ቀን ብትቸገርም ከሌላው ስራ የተሻለ ሆነላት::ለሊት ተነስታ የውሎዋን ለመሙላት ተፍ ተፍ ትላለች:: ዘይነባ እንዲህ ስታደርግ በየዕለቱ መሳቃቋ አልቀረም::ያለሰአቱ የምታበራው የአከራዮቿ አምፖል ፣ በየጊዜው የምታቀጣጥለው የከሰል ጭስ ከቀናት በአንዱ ጥያቄ እንዳያስነሳ ትሰጋለች:: ለመኖር ምርጫዋ ይህ ሆኗል:: ምንአልባት የእሷ ኑሮ ለሌሎች ከጎረበጠ ቀጣይ ዕጣ ፈንታዋን አታውቅም::

### ባለሻይ...

አሁን ዘይነባ ሻይ ቡናዋን ይዛ ብስኩት አምባሻ ትሸጣለች:: ልክ እንደእሷ መተዳደሪያቸውን በዚህ ስራ ያደረጉ ቀድመው ለመሸጥ ይፎካከሯታል:: እንደእነሱ ቀድሜ ለመገኘት መሮጥ፣መፍጠን አለባት::ይህ እንዳይሆን የትንሽ ልጇ አቅም የሚፈቅድ አይሆንም::

እሷ በተጠራችበት ስትሮጥ ህጻኗ ከኋላዋ ትከተላለች:: እናት ልጇን ‹‹አደራ››ብላ የምትውልበት ምቹ ቦታ የለም:: ልጅቷ ግን ስለእሷ ህይወት የሚከፈለው ዋጋ የገባት ይመስላል:: እንደልጅ አትረብሽም፣አትቀብጥም::ቢርብ ፣ ቢጠማት ‹‹ስጭኝ›› ብላ አትጠይቅም:: የተሰጣትን ቀምሳ ውላ ታመሻለች:: ከማለዳ እስከምሽት ከእሷው ጋር ውላ ስትገባ ከበዛ ድካም ጋር ነው:: ጎዳና ውላ ማምሸቱን የለመደችው ህጻን ይህን ኑሮ እንደ ውዴታ ተቀብላ መኖርም ይዛለች::

አሁን የሰኔ ወር ሊሰናበት ጥቂት ቀናት ቀርተውታል:: እስካሁን ጅማሬው ለእሷ እንደ ክረምት አልጨከነባትም:: ጥቂት ዘንቦ ብልጭ የምትለው ጸሀይ ተስፋዋን እየሆነች ቀን አሻግራታለች:: ክረምቱ ሲገፋ፣ ውርጩ ሲበረታ ግን ሁሉም ያሳስባል ፣ጭቃ ማጡ ፈተና ይሆናል:: በተለይ እንደ ዘይነባ ቋሚ የስራ ቦታ ለሌለው ፣ሮጦ ተባሮ ለሚያድር ተስፈኛ ክረምት ዝናብ ብቻ አይደለም::

ዘይነባ ጓዟ ብዙ ነች::ስራ ለመሄድ ስታስብ ልጇን ጨም ሮ በርካታ ዕቃዎችን ተሸክማ ነው::ሳንቲም ለመቆጠብ ስትል በጋሪና በባጃጅ መሄድ ያለባትን መንገድ በእግሯ ትጓዛለች::እንዲህ ባደረገች ቁጥር ሰአት ይረፍዳል:: ድካምና ዝለትን ይዛ ስራ ቦታዋ ስትደርስ አዲስ ጉልበት ትጨምራለች:: የእጇን ለመሸጥ፣ እዚህም እዚያም መሮጥ ግዴታዋ ነው::

### ክረምቱን...

ዘይነባ ክረምቱ አምርሮ የሚገባበትን የሀምሌ ነሀሴን ወር አስቀድማ ፈርታዋለች:: አምና ላይ በስራዋ መቀጠል ቢከብዳት እሸት በቆሎ እየቀቀለች፣ለመሸጥ ሞክራለች:: በቆሎውን ለመረከብ ፣ ጉልበት መክፈል ግድ ይላታል:: ጅማሬዋ እንዳሰበችው ባልሆነ ጊዜ ሁሉን ትታ ልብስ ማጠብ ጀምራ ነበር::

ዘንድሮ ደግሞ ከመጪው ክረምት ልትጋፈጥ፣ከብርድ ከጭቃው ልትታገል ቀን መቁጠር ይዛለች::እንደ አምናው ሁሉ ፈተና እንደሚገጥማት አልጠፋትም:: ከጀመረችው ስራ ‹‹ይብቃኝ›› ብላ አልቆመችም::አሁንም አማራጭን ፍለጋ ትተጋለች:: ዛሬም ስለመኖሯ ትሮጣለች::

ሁሌም በመንገዱ ዳርቻ ስለመኖር፣ የሚተጉ ፣ስለነጋቸው የሚያልሙ ነፍሶች ቀን ተሌት ንቁ ናቸው ::እነሱ በየግዜው መስራት መሮጥ ካልቻሉ ኑሮን አይገፉትም:: አብዛኞቹ ራሳቸውን የሚስተዳድሩ ወጣቶች መሆናቸው ሁኔታቸው ይለያል::

ሁሉም በሚባል መልኩ የተሻለ ህይወትን ፍለጋ ከትውልድ ሀገራቸው ወጥተዋል::እንዲህ ከሆነ በኋላ የእናት አባትን ምርቃት እንጂ ጥቅምን ማግኘት ዘበት ነው:: እንደውም ሰርተው ከሚያገኙት ለቤተሰብ መርዳት፣ማገዝ ግዳታቸው መሆኑን አውቀዋል::

### ጫማ አሳማሪው...

ወጣት ማቲዎስ ዓለም ከትውልድ ሀገሩ ወላይታ አዲስ አበባ የገባው በዕድሜ ትንሽ ሳለ ነበር:: ገና ህጻን ሆኖ ከሰፈሩ ልጆች በዛ የሚሉት ወደከተማ እንደሚተሙ ሲሰማ ቆይቷል:: የልጅነት አእምሮው የእነሱን ለውጥና ዕድገት አበክሮ ይከታተል ነበር::

ጥቂት ከፍ እንዳለ በዕድሜ የሚያንሱት ጭምር አዲስ አበባ እየሄዱ መኖራቸውን አረጋገጠ:: ማቲዎስ በየቀኑ የሚሰማው የእናቶቻቸው ጨዋታ ለጆሮው ተለየበት:: ሁሌም የሚያወሩት ስለልጆቻቸው ጥሩ መኖር ፣ መብላትና መልበስ ነው::አንዳንዴ የሚታዘበው እውነትም ይህን ሀቅ ሲያረጋግጥለት ቆይቷል::

ማቲዎስ አንድ የዘመድ ልጅ ቤተሰቦቹን ጥየቃ ከሰፈራቸው ከርሞ መሄዱን ካየ ወዲህ ልቡ ይበልጥ ተነስቷል:: ዕድሜው ከእሱ የሚያንስ ቢሆንም ካሰበው ሲደርስ ምንም እንደማያቅተው ለውስጡ ነግሮታል:: እንደ እኩዮቹ አለመማሩ ከወላጆቹ አላራቀውምና :: ከእርሻና ከቤት ይውላል::

### የልብ ሃሳብ...

አንድ ቀን ማቲዎስ የልቡ ሞላለት::በድንገት ከሰፈር ልጆች ተቀላቅሎ ከአካባቢው ራቀ:: የመንገዱ ፍጻሜ መዳረሻውን አዲስአበባ አደረገው:: ከማቲዎስ ጋር የነበሩ ልጆች መሀል ከተማ ሲገቡ በየአቅጣጫው ተበተኑ :: አብዛኞቹ ተቀባይ ዘመድ ነበራቸው::ከቆይታ በኋላ እሱና ሌላ አንድ ልጅ ብቻቸውን እንደሆኑ አወቁ::

ምሽቱ ገፍቶ ጨለማው ሲበረታ ሁለቱ እንግዳ ልጆች በጭንቀት ተዋጡ:: በዚህ ሥፍራ የሚጠሩት ዘመድ፣ የሚገቡበት ቤት የለም::በመፋጠጥ ሰአታት ተቆጠሩ ::አጋጣሚ ሆኖ ቋንቋቸውን የሰማ አንድ የሀገራቸው ልጅ ጠጋ ብሎ አዋያቸው:: እውነቱን ሳይደብቁ ከቤት ጠፍተው መምጣታቸውን ተናገሩ:: ልጁ ስሜታቸውን ለመጋራት አልዘገየም:: እሱም ከወራት በፊት ካገሩ የወጣው በተመሳሳይ አጋጣሚ ነበር::

የዕድል ጉዳይ ሆኖ የልጁ ኑሮ ከአንድ የጎዳና ጥግ ነው::ቀን ሲሮጥ ውሎ ማታ ጎኑ የሚያርፍበት ስፍራ አለው:: ዛሬ ደግሞ ከጓዳው፣ እንግዶችን ተቀብሎ ሊያስተናግድ ነው:: በዚህ መልኩ የጀመረው የአዲስ አበባ ህይወት እንደዋዛ ከወራት ተሻገረ::

### እንግድነትን በብርታት ...

ማቲዎስ ከተማውን ሲያውቅ፣መውጫ መግቢያው አልጠፋውም:: ለግዜው ለዕለት ጉርሱ ከመንገድ ቆሞ ሳንቲም መለመን ጀመረ:: ልጅነቱን ያዩ አልጨከኑበትም:: በሚያገኘው ገንዘብ ርሀብ ጥማቱን እያስታገሰ ቆየ:: በኋላ ግን የእሱ እኩዮች ጥንካሬ ውሰጡን ማረከው::

ያገኘውን እየሰራ ለብዙዎች እየታዘዘ ሳንቲም መያዝ የጀመረው ማቲዎስ :: ከሆቴል የሚያገኘውን ትራፊ እየጎረሰ የሊስትሮ ዕቃዎች ገዝቶ ያዘ:: ይህን ብርታት ያዩ አንዳንዶች የጎደለውን ሞልተው ‹‹አለንልህ›› አሉት::ደንበኞችን አብዝቶ ለማግኘት አፍታ አልዘገየም::ትናንትናን በልመና የሚያውቁት በርካቶች ስራውን በይሁንታ መረቁለት::

ትንሹ ልጅ ካገሩ የወጣበትን ምክንያት ዘንግቶት አያውቅም:: አገሩ ሳለ አዲስ አበባ ቆይተው በየመንደሩ የሚዘልቁ ሰዎች ገጽታ ትዝ ይለዋል:: እሱ ዛሬ ከቦታው ደርሶ ይህን ታሪክ ፈጥኖ አላገኘውም:: ትዝታው ግን አብዛኞቹ ራሳቸውን ለውጠውና በአለባበስ ዘንጠው ሲንጎማለሉ ያሳየዋል::

ይህ እውነት አብሮት ቢዘልቅ ያሰበውን ከማድረግ ወደ ኋላ አላለም:: የአቅሙን አጠራቅሞ ወላጆቹን ለማገዝ፣ራሱን ለማስደሰት ሞክሯል::ከጎዳና ኑሮ ወጥቶ ቤት መከራየት ከጀመረ ወዲህ ስለነገ ያላው ምኞት በእጅጉ በርትቷል::ቀለም ቡሩሹን ይዞ ጫማ ሊያሳምር ሲወጣ ደንበኞቹን ያከብራል:: ከብዙዎች ይግባባል::

### ከዓመታት በኋላ...

እነሆ ! ዓመታት ነጉዱ::ማቲዎስ ልጅነቱ አልፎ ጉርምስናው ተተካ::ይህኔ የግራ ጎኑ አጋርነት አስፈለገው:: እንዳሰበው ሆነለት ::አቻውን አላጣም:: ሚስት አግብቶ ባለ ትዳር ሆነ:: ጥንዶቹ ዓላማቸው አንድ ቢሆን ጎጇቸው ሞቀ፣ደመቀ:: የሶስት ጉልቻን ወግ ሲጀምሩ መተሳሰባቸው ትርጉም ኖረው::

ማቲዎስ ለዓመታት እሱን ከመሰሉ ወጣቶች ጋር በአንድ ሆኖ ጫማ ሲያሳምር ቆይቷል:: እግረ መንገዱን የሚያገኘው ድለላም ገቢ ሲያስገኝለት፣አቅሙን ሲደጉምለት ነበር:: አሁን እንደ ቀድሞ ብቻውን አይደለም:: ሚስቱን ጨምሮ ሁለት ልጆችና አንድ ራሱን በኃላፊነት ይመራል::

### ክረምትን በፍራቻ...

ማቲዎስ የዘንድሮውን ክረምት የፈራው ይመስላል::ቀድሞ ክረምት ‹‹መጣሁ ባለ ጊዜ ደስታው ልዩ ነበር:: ከበጋው በተለየ ደንበኞቹ ይጎበኙታል፣ጉርሻና ገበያው ይደራል፣አንገቱን ደፍቶ ጫማውን ሲጠርግ፣ሲያስምር ምሳ ለመቅመስ ጊዜ አልነበረውም::ይህ ወቅት ለድሀ ጎጆው በረከት የሚሰጠው ተናፋቂ ጊዜ ነበር::

ሊስትሮው ማቲዎስ አሁን ያለበት የስራ ቦታ የቀድሞው አይነት አይደለም::ፒያሳና አካባቢው በልማት ከተነሳ በኋላ ከደንበኞቹ ተለያይቶ አካባቢን ቀይሯል::ዛሬ ቋሚ ቦታ ማጣቱ ስራውን አዳክሞታል::እንደበፊቱ ጊዜና ሰአት አንሶት አያውቅም ::እንደምንም ተባርሮ የሚያገኘው ስራ ከሌሎች እያጋፋ ሲያገላምጠው ይውላል::

ልክ እንደዘይነባ ሁሉ ክረምቱን እያሰበ የሚጨነቀው ወጣት በመጪው ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለበት አላቀደም:: እንደበፊቱ ቢሆን የክረምቱ መድረስ እንደዝናቡ በረከቱ ነበር:: ደንበኞችን ያፈራል፣ ስራውን አብዝቶ፣ ገቢውን ይጨምራል::

አሁን ማቲዎስ ‹‹ሊስትሮ›› ነኝ ቢልም ስለሚሆነው ሁሉ እርግጠኛ አይደለም:: በፍቅር የሚወደውን የሊስትሮ ሙያ እንደዋዛ መተው ባይሻም አሁን ውስጡ ከሌላ ዕቅድ እያደረሰው ነው:: ያገኘውን ለመስራት ወደኋላ አይልም::ከእሱ ልፋት በስተጀርባ እጁን የሚጠብቁ ሚስትና ልጆቹ በእሱ ጫንቃ ሲያድሩ ቆይተዋል::

ዛሬ ደግሞ የክረምቱ ጫና ከጫንቃው የተጫነ ያህል ቢሰማው ዛሬን ለመኖር ከሸክሙ፣ከጥበቃው፣ ከመላላኩ ስራ ተገኝቷል:: ጥሩው ነገር ተግባቢውን ማቲዎስ ፊት የሚነሳው የለም:: ለአዲሶቹ ስራዎችና ለአካባቢው እንግዳ ቢሆንም መልካምነቱን የሚያውቁ ሁሉ ‹‹አለንህ›› ይሉታል::

### ተመሳስሎን በመፍትሄ ...

ዘይነባንና ማቲዎስን የመሰሉ፣ህይወት እንጀራቸው ከጎዳናው ሲሳይ የተጣመረ ነፍሶች በአንዳንድ አጋጣሚ ከኑሯቸው ሽርተት የሚሉበት ሰበብ አይጠፋም:: እንዲህ አይነቶቹ ብርቱዎች ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን የሚያኖሩ ናቸውና የመልካም ሰዎች በጎ ዓይኖች ሊያዩ ፣ሊጎበኙዋቸው ይገባል::

# መሠረተ ልማት

# ለኮንስትራክሽን ዘርፉ የሥራ ላይ ደህንነትና ጤንነት

**በኃይሉ አበራ**

የኮንስትራክሽን ዘርፉ ለኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ዘርፉ ከዓለም የሰራተኛ ኃይል ሰባት በመቶ ያህሉንም ይይዛል። ይህ ዘርፍ ከስራ ጋር በተያያዘ በሚከሰቱ አደጋዎችም ዘርፉ ይጠቀሳል፡፡

መረጃዎች እንደጠቆሙት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከስራ ጋር ተያይዞ በሚያጋጥሙ አደጋዎች በዓመት በአማካይ ሁለት ነጥብ 78 ሚሊዮን ያህል ሰዎች ለሞት ይዳረጋሉ። ከዚህ ውስጥም 17 በመቶ የሚሆነው ሞት የሚከሰተው ከኮንስትራክሽን ጋር በተያያዙ ከባድ አደጋዎች ነው።

በኢትዮጵያም የኮንስትራክሽን ዘርፉ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት የጎላ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ሲሆን፣ ከግብርናው ቀጥሎ ከፍተኛ መጠን ያለው የሰው ሀይል እንደሚይዝም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዘርፉ በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ በሚከሰቱ አደጋዎች ጋርም ስሙ ይነሳል፡፡ በዚህም ሰራተኞች፣ በግንባታ አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች፣--- ወዘተ ህይወት ይጠፋል፤ አካል ይጎድላል፤ ሌሎች የጤና ችግሮች ይከሰታሉ፡፡

ግንባታዎች በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ የግንባታ ተረፈ ምርቶች ተከማችተው ይታያሉ። የግንባታ ጥራት ጉድለት፣ የግንባታ መወጣጫዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆን፣ ወዘተ ሌሎች የአደጋ መንስኤ በመሆን ይጠቀሳሉ፡፡ የዘርፉ አለመዘመንና የተቋራጮች ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት አለማደግ ሌሎች ለአደጋዎቹ መከሰት ምክንያት ተደርገው ይጠቀሳሉ፡፡ይህ ሁሉ በኮንስትራክሽን ባለሙያው ላይ ብቻ ሳይሆን አገልግሎት በሚያገኙ እንዲሁም በግንባታው አካባቢ በሚንቀሳቀሱ ሰዎች ላይ አደጋዎችን ሊያስከትል ይችላል።

በሀገሪቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዘርፉን ለማዘመን እና ጥራቱን ለማስጠበቅ በሙያ ደህንነት እና ጤንነት ላይ መሻሻሎችን ለማምጣት ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። ዜጎችን ከአደጋዎቹ ለመጠበቅ ብቻም ሳይሆን፣ የኮንስትራክሽን ዘርፉን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በተለይ የስራ ላይ ደህንነት እና ጤንነት ሰርተፊኬት እንደ አንዱና ዋነኛ መስፈርት ተደርጎም እየተሰራበት ነው። በመንግሥት በኩል አስገዳጅ የሆኑ የሕግ ማዕቀፎች ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል። ለህንጻ ተቋራጮች የተለያዩ ስልጠናዎች እየተሰጡ ናቸው።



በአምስት ዙር ለ194 የኮንስትራክሽን ሙያተኞች ስልጠና ተሰጥቷል



ለኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጮች ሰርተፊኬት ሲሰጥ

ከሰሞኑም የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማህበር እና ከኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ባዘጋጁት ስልጠና ለ194 የኮንስትራክሽን ሙያተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ሰልጣኞቹ ከማህበሩ የተለያዩ አባል ድርጅቶች የተውጣጡ ናቸው፡፡

የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማህበር ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ግርማ ሀብተማርያም በዚህ ወቅት እንዳስታወቁት፤ የሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት እንዲኖረው ለማድረግ ከሚጠበቅበት መስፈርቶች አንዱ የኮንስትራክሽን የሙያ ደህንነት እና ጤንነት ጉዳይ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ በመንግሥት በኩል እርምጃ መጀመሩ፣ መንግሥት ዘርፉ ደረጃ በደረጃ እያደገ እንዲሄድና ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ ያለውን ጥረት ያሳየ ነው ሲሉ ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል።

በሀገሪቱ በተለይ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እድገት አሳይቷል የሚሉት ኢንጂነር ግርማ፤ ይሁንና ሀገር በቀሉ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ከዘርፉ እድገት አልተቋደሰም ሲሉ ያመለክታሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ ለዚህም ከሚጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ እና በበርካታ የዘርፉ ተዋናዮች የሚታመንበት ምክንያት ግልፅ የሆነ የእድገት ፍኖተ ካርታ አለመኖሩ ነው።

ይህም በመንግሥት በኩል ትኩረት እንደሚሰጠው እና ወደ ተግባር ሊገባ እንደሚችል ተናግረው፣ ለተግባራዊነቱም እንቅስቃሴ እንደሚጀመር ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴዎች እየታዩ ነው ብለዋል። ማህበሩም እንደ አንድ የኢኮኖሚው ባለድርሻ አካል ለአሰራር ስርዓቱ ተግባራዊነት የበኩሉን በማበረከት ሀገራዊ ኃላፊነቱን እንደሚወጣም አረጋግጠዋል።

በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት፣ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን እና በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማህበር በኩል የሶስትዮሽ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ መደረጉን አስታውሰው፣ በዚህ ስልጠናም የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት የላቀ የባለቤትነት ድርሻ እንደነበረው ጠቁመዋል። ፕሬዚዳንቱ ስልጠናውን በአምስት ዙር አጠናክሮ በማስቀጠል የኮንስትራክሽን የሙያ ላይ ደህንነት እና ጤንነትን በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው አሰራር ስርዓት እንዲሆን የበኩሉን ሚና እንደሚወጣ አስታውቀዋል።

የኮንስትራክሽን የሙያ ላይ ደህንነት እና ጤንነት በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ እንዲውል እየተደረገ ባለው የሙያ ብቃት እና ማረጋገጫ መመሪያ ላይም እንደ አንድ አስገዳጅነት ያለው መስፈርት ሆኖ መቀመጡ፣ ጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው እና አቢይ አጀንዳ መደረጉን ማየት ችለናል ብለዋል። በኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጮች ማህበር በኩልም ሙያተኞቹን ለስልጠና በመላክ እና ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመሩን አመላክተዋል። በመንግሥት በኩልም አስገዳጅ መመሪያ እንዲወጣ ከመደረጉ ቀደም ብሎ የሶስት ዓመታት የዝግጅት ጊዜ እንዲኖር መደረጉ መንግሥት በኃላፊነት ስሜት ሊመራው ማቀዱን ያሳየ መሆኑን ገልጸዋል።

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ታምራት ሙሉ በበኩላቸው የኮንስትራክሽን የሙያ ደህንነት እና ጤነነት ስልጠና እና አጠቃላይ የአሰራር ስርዓቱን አስመልክተው ሲያብራሩ እንደገለጹት፤ ሀገሪቱ ለካፒታል በጀት ከምትመድበው ትልቅ ሀብት 60 በመቶ ያህል ለኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚመደብ ነው። በሀገሪቱ በርካታ የሚታዩ የልማት ስራዎችም የዘርፉ ውጤቶች ናቸው። የኮንስትራክሽን ዘርፉን አቅም ማሳደግ ሀገርን ማልማት ነው በሚል እየተሰራ ነው። በዚህ መሰረት የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ይሰጣል።

የኮንስትራክሽን የሙያ ላይ ደህንነት እና ጤንነት ጉዳይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት የሚስብ ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢንስቲትዩቱም በዚህ ላይ ስልጠናዎችን በትኩረት እየሰጠ መሆኑን ገልጸዋል። በሙያ ደህንነት እና ጤንነት ላይ ተሰራ ማለት አምራች ኃይሉን መጠበቅ ማለት ነው ሲሉም አስገንዝበዋል።

ኢንጂነር ታምራት እንደተናገሩት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከስራ ጋር ተያይዞ በሚያጋጥሙ የደህንነት እና ጤንነት አደጋዎች በአማካይ በዓመት ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን አካባቢ ሰዎች ለሞት ይዳረጋሉ። ከዚህ ውስጥ የ17 በመቶው ሞት ምክንያት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መሆኑን የዓለም የሰራተኞች ድርጅት መረጃ ያመለክታል።

የስራ ላይ ደህንነትና ጤንነት ላይ ከተሰራ ይሄንን አምራች ኃይል መጠበቅ ይቻላል። አደጋው በሰው ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት በተጨማሪ በሀብት እና በገፅታ ላይ የሚያሳድረው ጉዳት ከፍተኛ ነው ሲሉም አስታውቀው፣ ይህን ችግር ለመፍታት ኢንዱስትሪው በደህንነት እና ጤንነት ላይ በትኩረት መስራቱ ተገቢ መሆኑን አመላክተዋል።

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩትም ከዚህ አንፃር ለደህንነት እና ጤንነት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው። በዚህ ላይ ዋነኛ የፊት ተዋናይ የሆኑትም የስራ ተቋራጮች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ስልጠናውን ለስራ ተቋራጮች ለመስጠት ጥረት ሲደረግ መቆየቱን አስታውሰዋል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ስልጠናውን አስመልክቶ አነስተኛ ፍላጎት እንደነበር ጠቅሰው፣ ከተወሰነ ጊዜ ወዲህም ግን በተለይ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማህበር ከኢንስቲትዩቱ ጋር ለመስራት ባለው ቁርጠኝነት የተነሳ ስልጠናዎችን በስፋት ለመስጠት ተችሏል ብለዋል። በአምስት ዙርም 194 ባለሙያዎችን ለማሰልጠን መቻሉን ተናግረዋል።

ኢንጂነር ታምራት እንዳስታወቁት፤ የኮንስትራክሽን ተቋራጮች የሙያ ላይ ደህንነት እና የጤንነት ሰርተፊኬት ለሀገር ውስጥ ገበያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትም ወሳኝ ነው። አሁን ባሉ ዓለም አቀፍ ጨረታዎች ላይ እንደ አንድ መስፈርት የሚታይም ነው። ደህንነት እና ጤንነት ላይ ሰርቲፋይድ መሆን፣ በአይኤስኦ ሰርቲፋይድ መሆን፣ ዓለም አቀፍ መስፈርት ናቸው። አሁን ያለው ፍላጎት ደግሞ የኛ ስራ ተቋራጮች በሀገር ውስጥ ብቻ እንዲቆዩ ሳይሆን፤ በአስር ዓመቱ የዘርፉ እቅድ ቢያንስ 25 በመቶ ገበያው ላይ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ነው ብለዋል።

የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮችም ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የውስጥ አሰራር ስርዓታቸውን ማዘመን አለባቸው ሲሉ ገልጸው፤ ለዚህም ሲባል ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቀ የአሰራር ሥርዓትን መጠበቅ የሚያስችሉ ስልጠናዎች ለተለያዩ ስራ ተቋራጮች መሰጠቱን አስታውቀዋል።

የኮንስትራክሽን ዘርፉን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የፕሮጀክት ማናጀሮችን በማብዛት እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፣ ፕሮፌሽናል ማናጀሮች በስፋት ሲኖሩም ፕሮጀክቶችን በአግባቡ የመምራት አቅም ይኖራል፤ ብክነቶች ይቀንሳሉ፤ የስራ ላይ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም ሌሎች የሚፈለጉ መስፈርቶችን በአግባቡ መምራትም ይችላሉ ሲሉ አብራርተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ መንግሥት በያዘው አቅጣጫ መሰረት የኮንስትራክሽን ዘርፉን ፍትሃዊ ከማድረግ አንፃር ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባት እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። ለዚህም ችግሮችን አስቀድሞ ለመለየት የሚያስችሉት እንደ ቢም ቴክኖሎጂ በመሳሰሉት ላይ ስልጠናዎች በስፋት እየተሰጡ ናቸው፡፡ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ስልጠናዎች፣ በጥራት፣ በደህንነት፣ በባለሙያ ቅጥር፣ በኮንትራት አስተዳደር፣ በዋጋ አስተዳደር፣ በፋይናንስ አስተዳደር፣ ስልጠናዎች እየተሰጡ ይገኛሉ። በኢንዱስትሪው ውስጥ ተወዳዳሪ ሆኖ መቀጠል ከተፈለገም እነዚህን ስልጠናዎች መውሰድ የተሰጠውንም ነፃ የስልጠና እድል መጠቀም እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለኢኮኖሚው በአጠቃላይ ለሀገር እድገት በየትኛውም መስክ ካሉት ኢንዱስትሪዎች ይልቅ በጣም ተወዳዳሪ እና ተጨባጭ ውጤት መምጣት የሚያስችል ኢንዱስትሪ ነው።

ኢንዱስትሪው ጊዜያዊ የሆኑ ፈተናዎች በተለይም ከሙያ ክፍተት ጋር የተያያዙ ማነቆዎች ይታዩበታል፡፡ በተለይ ከትምህርት ስርአቱ ጋር ተያይዞ ያለው እና ንድፈ ሀሳብ ላይ ብቻ ያተኮረ ትምህርት ወደ ተግባር ሲወጣ መደነጋገር ሲፈጥር በየቀኑ የስራ ውሎ ላይ በግልጽ ይታያል።

ከግብዓት ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ፍኖተ ካርታ ማህበረሰቡን እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን በማሳተፍ ወደ ማፅደቅ ሂደት እየተገባ መሆኑን ጠቁመዋል። ዘርፉ በሁለንተናዊነት ከየት ወዴት እንደሚደረስ ፍኖተ ካርታው ያሳየናል ሲሉም ጠቅሰው፤ ይህ ብቻውን ግን በቂ እንዳልሆነ ተናግረዋል፡ ፡ ለተግባራዊነቱም ሁሉም በኃላፊነት ስሜት መስራት እንደሚገባው አመላክተዋል።

ሚኒስትሯ እንዳስገነዘቡት፤ በተለይ የስራ ላይ ደህንነትና ጤንነት ከኮንስትራክሽን ዘርፍ ጋር በቀጥታ የሚያያዝ ስለሆነ እያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ እና የዘርፉ ባለሙያ ወደሚሰራባቸው ሳይቶች ተመልሶ ማየት ይገባዋል። ጥንቃቄ አድርጉ የሚል ፅሁፍ መጻፍ ብቻ በቂ አይደለም። ሄልሜት ብቻ ካለው በቂ ነው ብሎም የሚያስብ አለ።

መንግሥት አሁንም አንድ እርምጃ ወደፊት እየሄደ በዓለም አቀፍ ደረጃ አድናቆት የሚሰጣቸውን እንደ ቢም ቴክኖሎጂ ባሉት ላይ ጨምሮ በነፃ ስልጠና እየሰጠ መሆኑን አስታውቀዋል። ዜጎች በስራ ቦታቸው ላይ አደጋ እየደረሰባቸው መሆኑን ጠቅሰው፣ በስራው ላይ በቀጥታ የሚሳተፉት ብቻ ሳይሆኑ የአገልግሎት ተጠቃሚውም ጭምር አደጋ እየደረሰበት ነው ሲሉም አመልክተዋል፡፡ ለዚህም በተለይ አስገዳጅ የሆኑ የሕግ ማዕቀፎችን በቅርቡ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ይህም ዘርፉ በሀገር ውስጥ ተወዳዳሪ መሆን ብቻ ሳይሆን ወደ ሌሎች ጎረቤት ሀገራት ከተሳካም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ዘርፍ መሆን አለበት ሲሉ ጠቁመው፣ በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ የሚፀድቀው የኮንስትራክሽን የስራ ላይ ደህንነት አስገዳጅ ህግ ሆኖ እንደሚወጣም ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በአንድ ስፍራ ላይ ኮንስትራክሽን አለ ከተባለ የግንባታው ብቻ ሳይሆን አካባቢው በሙሉ በግንባታ ተረፈ ምርት እየተጥለቀለቀ ከፍተኛ ጉዳትም እየደረሰ ነው። በከተሞች በሚሰሩ ሜጋ ፕሮጀክቶች፣ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ የውሃ መፍሰሻ ቱቦዎች፣ በእያንዳንዱ በኮንስትራክሽን ግብዓት ተረፈ ምርቶች እየተሞሉ ናቸው። እነዚህን ዘርፉን የማይመጥኑ ብልሽቶች በሕግ ማዕቀፍ ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

ፈተናዎች ቢኖሩም ከተማንም ከተማ ለማድረግ ሀገርንም ሀገር ለማድረግ እና የሀገርን የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ትልቅ ሚና እንዳለው ጠቅሰው፣ ተቋራጮች ተወዳዳሪነታቸውን እንዲያሳድጉ የሚሰራው የግንባታ ስራ ሁሉ ቀጣዩን ትውልድ ታሳቢ ማድረግ እንደሚገባው ጠቅሰው፣ ለዚህም መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አረጋግጠዋል።

# ስፖርት





# የሻምበል አበበ ቢቂላ ማራቶን ነገ በሃዋሳ ይካሄዳል

ዓለማየሁ ግዛው

የታላቁ አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ መታሰቢያ የሆነው የማራቶን ውድድር ነገ ለ40ኛ ጊዜ በሃዋሳ ከተማ ይካሄዳል። ስመጥር እና ጀማሪ አትሌቶች በሚሳተፉበት ውድድር ለአሸናፊነት የሚደረገው ትንቅንቅ ይጠበቃል።

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከሚመሩ ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው የታሪካዊው አትሌት ሻምበል አበበ በቂላ የማራቶን ውድድር በየዓመቱ የጀግንነትና አሸናፊነት ታሪኩን ለመዘከር ታስቦ ይካሄዳል። ውድድሩ ነገ ሰኔ 30/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 12:00 ሰዓት ጀምሮ ለ40ኛ ጊዜ በርካታ አትሌቶችን በማሳተፍ ይካሄዳል። ውድድሩን ለማካሄድ የሚያስችለው ቅድመ ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን፤ መነሻውንና መድረሻውን ሃዋሳ ፒያሳ ገብርኤል አደባባይ በማድረግ 42 ነጥብ 195 ኪሎ ሜትሩ በሁለት ዙር የሚሸፈን ይሆናል።

አበበ ቢቂላ በዓለም መድረክ በባዶ እግሩ ሮጦ በአፍሪካ ደረጃ ፈር ቀዳጅ ድልን በመቀዳጀት ለአፍሪካውያን ስፖርተኞች ተምሳሌት መሆኑ ይታወቃል። አርዓያነቱን በመከተልም እልፍ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ታሪኩን ደጋግሞ በመጻፍ ስሙ እንዲታወስ አድርገዋል። መነሻቸውን ከጀግናውና አይበገሬው አትሌት የመታሰቢያ ውድድር ላይ ያደረጉትም ቀላል የማይባሉ ናቸው:: አንጋፋ የማራቶን ውድድር እንደመሆኑ ለዓመታት ለተተኪ አትሌቶች የሀገር ውስጥ የውድድር እድልን ከመፍጠርም በላይ የአንጋፋውን አትሌት ወኔ በማላበስም ወደር አይገኝለትም።




የሻምበል አበበ ቢቂላ ማራቶን በርካታ ተተኪ አትሌቶችን በማፍራት ላይ ይገኛል፤

ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚደረጉ ውድድሮች በትልቅነቱ ከቀዳሚዎቹ አንዱና በአትሌቶች መካከል ጠንካራ ፉክክርን ከሚያስመለክቱት ተርታም የሚመደብ ነው። ዘንድሮም ትልልቅና ልምድ ያላቸውን አትሌቶች ከማሳተፉም በላይ ቀጣይ ሀገርን የሚወክሉ አትሌቶችን በፉክክር አጅቦ እንደሚያስመለክትም ይጠበቃል። ከታዋቂ አትሌቶችም መካከል በሴቶች በማራቶን እና 30 ኪሎ ሜትር ሩጫ ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ሩቲ አጋ እና በሻንቂ ሙሼ ከሲዳማ ፖሊስ፣ ትዕግስት አባይቸው እና ሔቨን ኃይሉ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የሺ ካላዩ እና ጽጌ ኃይለስላሴ ከአትዮ ኤሌክትሪክ ይካፈላሉ። በወንዶች ደግሞ በላይ ጥላሁን እና ኃይለማርያም ኪሮስ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ጽዳት አበጀ እና ጸጋዬ ጌታቸው ከኢትዮ ኤሌክትሪክ፣ ጫሉ ዴሶ፣ ለሚ ብርሃኑ እና ጸጋዬ መኮንን ከኦሮሚያ ፖሊስ፣ ካሌብ ካሼቦ ከመቻል፣ ደባቦ ደቃሞ ከሲዳማ ፖሊስ እንዲሁም አዲሱ ጎበና ከፌዴራል ፖሊስ ከሚሳተፉ ወንድ አትሌቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

ከአንድ ክልል፣ አንድ ከተማ አስተዳደር እና 17 ክለቦች የተውጣጡ አትሌቶችን ጨምሮ አንጋፋ አትሌቶችና በርካታ የግል ተወዳዳሪዎችም ይሳተፉበታል። በሴቶች 91 እና በወንድ 283 በድምሩ 374 አትሌቶች ለአሸናፊት እንደሚፎካከሩም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አስታውቋል:: በውድድሩ ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ለሚያጠናቅቁ አትሌቶች ከሜዳሊያ በተጨማሪ እንደየደረጃቸው የገንዘብ ሽልማት የተዘጋጀላቸው ሲሆን በሁለቱም ጾታ አንደኛ ሆኖ የሚያጠናቅቅ 50 ሺ. ብር፣ ሁለተኛ 25 ሺ. ብር እና ሶስተኛ ደረጃ የሚወጣ አትሌት ደግሞ 20 ሺ. ብር ይበረከትላቸዋል። ሽልማቱ እስከ ስምንተኛ ደረጃ የሚሰጥ ሲሆን ከ18 ሺ. ብር እስከ 10ሺ. ብር በቅደም ተከተሉ መሠረት የሚሸለሙም ይሆናል።

በአንጋፋ አትሌቶች መካከል የሚደረገው ፉክክር ደግሞ ከ50 ዓመት በላይ እና በታች በወንዶች፣ ከ50 ዓመት በታች በሴቶች መካከል ይካሄዳል። ሽልማቱ በዚህ ዘርፍም የተዘጋጀ ሲሆን፤ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ደረጃ ለሚወጡ አትሌቶች ከ12 ሺ. ብር እስከ 2 ሺ. ብር በቅደም ተከተል ያገኛሉ:: በአጠቃላይ ለሽልማት የተመደበው ገንዘብም 426 ሺ. ብር እንደሆነም ለማወቅ ተችሏል።

የኦሊምፒክ ጀግናው አትሌት አበበ ቢቂላ የማራቶን መታሰቢያ ውድድር ማካሄድ የጀመረው በ1974 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ሲሆን በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞችም እየተካሄደ ዘንድሮ 40ኛው ላይ መድረስ ችሏል። ለመጀመርያ ጊዜ በተካሄደው ውድድር ኢትዮጵያን ጨምሮ ሶስት ሀገራት (ኢትዮጵያ፣ ሶቭየት ህብረት እና ጂቡቲ) ተካፍለው ነበር። ውድድሩ የአበበ ቢቂላ ዓለም አቀፍ ማራቶን የሚል ስያሜን በመያዝ የውጭ ሀገራት አትሌቶችን እያሳተፈ የቆየ ቢሆንም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሀገራዊ ስያሜን በመያዝ የሻምበል አበበ ቢቂላ ማራቶን ተብሎ እየተካሄደ ይገኛል። በመጀመርያው ውድድር 51 አትሌቶች ተሳትፈው 27ቱ ብቻ ውድድራቸውን እንዳጠናቀቁም መረጃዎች ይጠቁማሉ። አንጋፋው አትሌት አበበ መኮንን ደግሞ በባዶ እግሩ ሮጦ 5ኛ ደረጃን በመያዝ ጀግናውን አትሌት መዘከር ችሎም ነበር።


# ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ለጅግጅጋ ቅርንጫፍ ከዚህ በታች በተጠቀሰው ክፍት የሥራ መደብ መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾችን አወዳድሮ በቋሚነት ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ተፈላጊ ችሎታዎች | | የሥራ ልምድ በዓመት | ደረጃ | የደመወዝ መጠን | የቤት አበል | የሀላፊነት አበል | ብዛት | የስራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የትምህርት ደረጃ | የትምህርት ዓይነት | | | | | | | |
| 1 | የፋይናንስ ቡድን መሪ III | የመጀመሪያ ዲግሪ | አካውንቲንግ፤ አካውንቲንግ ኤንድ ኦዲቲንግ፣ አካውቲንግ ኤንድ በጀት፤ ባንኪንግና ፋይናንስ፣ ኮምፒዩተራይዝድ አካውንቲንግ፣ ኮኦፐሬቲቭ አካውንቲንግ ፤ አካውንቲንግና ፋይናንስ፤ ፋይናንሻል አካውንቲግ፣ ፐብሊክ ፋይናንስ፤ አካውንቲንግና ፐብሊክ ፋይናንስ፣ ኮኦፐሬቲቭ አካውንቲግ ኤንድ ኦዲቲንግ፣ አካውንቲንግና በጀት ስርቪስ፤ ፐብሊክ ሴክተር ፋይናንስ፣ አካውንቲንግና በጀት ሳፖርት፣ ኮሜርስ አካውንቲንግ፤ ፋይናንስ ዲቬሎፐመንት ኢኮኖሚክስ፣ ፋይናንሻል ማኔጅመንት፣ ፐብሊክ ፋይናንሻል ማኔጅመንት፤ መንግስት ፋይናንስ አስተዳደር፣ ሰርቲፋይድ አካውንቲንግ፤ ታክስ አስተዳደር፣ ታክስና ከስተም አድሚኒስትሬሽን፤ | 9 ዓመት ቀጥታ አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ | XV | 10,150 | 6,000 | 3,500 | 01 | ጅግጅጋ |

**ማሳሳቢያ፡-**

*ፆታ አይለይም፤ ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ፡፡ በምዝገባ ወቅት አመልካቾች የትምህርት ማስረጃ ዋናውን እና የማይመለስ አንድ ኮፒ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። አመልካቾች የትምህርት ማስረጃ ሲያቀርቡ ስቱደንት ኮፒ ማያያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡*

*የመመዝገቢያ ቀንና ሰዓት ማስታወቂያው በጋዜጣ ላይ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ባሉት 7/ሰባት/ ተከታታይ የሥራ ቀናት አመልካቾች በEmail አድራሻ pfsahr@gmail.com በPDF format merge በማድረግ መላክ ይኖርባቸዋል።*

*መንግስታዊ ካልሆኑ መ/ቤቶች የሚቀርቡ የሥራ ልምድ ማስረጃዎች በደንቡ መሠረት የገቢ ግብር የተከፈለባቸው መሆኑን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡*

*አድራሻ፡- ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ፊትለፊት*

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የመድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት